

# ሕያሴ መዝሙራት

ስለ መዝሙሮች ሕጸጾች የቀረበ ሒስ

© ዕዝራ የሥነ ጽሑፍ አገልግሎት / ዘላለም መንግሥቱ

ezralit@gmail.com

# ይድረስ ለዘማሪዎች

## ቅጽ አንድ

(ይህ ሥራ በመጀመሪያ በኦዲዮ የተዘጋጀና የተሰራጨ ነው።)

በማስተዋል ዘምሩ። መዝ. 47፥7

አንድ ወንድም ስለ መዝሙሮች ምን እየሆኑ መምጣት ሲናገር እንዲህ አለ፥ “የዘመኑ መዝሙሮች ጧት ተነብበው ማታ እንደሚጣሉ የጎዳና ጋዜጦች እየሆኑ ናቸው፤ አንዴ ተሰምተው ከዚያ በኋላ የማይሰሙ፥ የማይደመጡ ከሆኑ ቆዩ አለ።

ሌላው ደግሞ፥ “ዱሮ በጣት የሚቆጠሩ ዘማሪዎች ናቸው የነበሩን፤ አሁን ግን በሙቶዎች ስለተቆጠሩልን በዝማሬና በዘማሪዎች ተባርከናልና እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን” አለ።

አንድ ራሱም የመዝሙር አገልጋይ የሆነ ወንድም ደግሞ፥ “በዚህ ዘመን እየወጡ ያሉ የመዝሙር ካሴቶችና ሲዲዎች ከላይ ስድስት ከታች ስድስት ዳቦ ኖሮት መሐል ላይ ደግሞ አንዲት እንቁላል የተደረገበት ሳንድዊች ይመስላሉ። ያቺን አንዷን እንቁላል ለመብላት አገጫችን ደረታችንን እስኪነካ ድረስ አፋችንን መክፈትና መጉረስ እየኖረብን ነው” አለ።

ሦስቱም አስተያየቶች እውነት ናቸው። መዝሙሮች እየበዙና በብዙ እየተባዙ መምጣታቸው እውነት ነው። ይህ መልካም ነው። ከብዛታቸው የተነሣ እንዲያውም ከአማካዩ ክርስቲያን ካሴት ወይም ሲዲ የመግዛት አቅም አልፈዋል። የዚያኑ ያህል ግን ብዙዎቹ የወረት ዝማሬዎች ብቻ እየሆኑ መምጣታቸውም የማንክደው እውነት ነው።

በዚህ ዘመን መዝሙሮች እየበዙልንና እየፈሰሱልን ከመሰለን እጅግ ብዙዎቹ መዝሙሮች በእሳት የተለበለቡ እንጂ የበሰሉ አለመሆናቸውንም ማወቅ አለብን። ጥሬ ናቸው። ግርድፍ እንጂ የተሰለቁ አይደሉም። ሽርክት እንጂ የላሙ አይደሉም። እንደ መልካ ወንዝ ያሉ ናቸው እንጂ ጥልቀት የላቸውም። <u>ደግሞም ብዙ ስሕተቶች አሉባቸው።</u>

## ዜማ

ይህ የዜማውን ጣዕምና ውበት ሳናወሳ ነው። የዜማና የቅላጼ ጣዕም ከሰው ወደ ሰው የመለያየት ጠባይ አለውና ዜማን ማሔስ ኅሊናዊ ብቻ ሊሆን ይችላል። በርካታ ቅኝቶች አሉንና ዜማ ያንን ተከትሎ ስለሚለያይ በዜማ መዝሙሮችን መፈረጅ ይከብዳል። ይሁን እንጂ የአንዳንድ መዝሙሮች ዜማ ዜማ ከሚባል ይልቅ ድምጽን ከፍና ዝቅ፥ ፈጠንና ቀርፈፍ እየተደረገ የተነበበ ንባብ ነው ቢባል ይሻላል። ዜማ ነው ከማለት ንባብ ነው እንጂ ዜማ ነው ባይባል ይሻላል። ከንባብ ምንም አይለይም። የሙዚቃ ዳራ ተደርጎለት ቢነበብ እንዲያውም ሳይሻል አይቀርም።

## የሙዚቃ መሣሪያና ድምጽ

ከዜማ ሳንርቅ መወሳት ያለበት የሙዚቃ መሣሪያ ነው። አንድ የሙዚቃ ሰው የሆነ የቤተ ክርስቲያናችን ሰው፥ "እስኪ የአገራችሁን መዝሙሮች አሰማኝ" አለኝና ከተለያዩ ካሴቶች አንዳንድ ለቃቅሜ በአንድ ሲዲ አድርጌ ሰጠሁት። ሰማና፥ "እንዳሰብኩት አይደለም፤ ቆንጆ ነው። ግን ከሲንተሳይዘር ሌላ መሣሪያ የላቸውም?" ብሎ ጠየቀኝ። ለዚያን ጊዜ በሙዚቃ የሚደመጥ ምላሽ አልነበረኝም። ቀድሞውኑ ማድረግ የነበረብኝ ከቀድሞዎቹ ከነደረጀ፥ ሥዩም፥ ሽዋዬ፥ ሌሎችም በዘመናዊም በባህላዊም መሣሪያ የታጀቡትን ማስደመጥ ነበረብኝ።

መዝሙር ከአገልግሎትነቱ ጋር እንደ ኪን ወይም እንደ ጥበብ ሊታይ ይገባዋል። ከሆነ ታዲያ፥ ለምን ነው ሲንተሳይዘር ብቻ የአገሪቱን ጠቅላላ መዝሙሮች የማጀብ የአንበሳ ቅርጫ የሚወስደው? ለዚያውም እስከሚቀራረብና የአንዱ ከሌላው ጋር እስከሚነካካ ድረስ። እስኪ ባለፉት በርካታ ዓመታት ስንት መዝሙር ነው በሳክሰፎን ወይም በክራር ወይም በዋሽንት የተዘመረው? መሣሪያዎች ከኖሩን ዓይነትና ቅንብር ለምን ጠፉ?

አንድ [እኔም የነበርኩበት የመዘምራን ቡድን] የዝማሬ መሪ የሆነ ሰው ይህ ቅንብር ለምን እንደማይሆን ስጠይቀው፥ "ቅንብርና ኅብር ካልክማ የጊዜ መስዋዕት ሊጠይቅ ነው። ገንዘብም ጥበብም ሊጠይቅ ነው። አሁን እየተደረገ ያለው እኮ ሽክን እንዳለ ወጥ ጊዜ ተወስዶ የተሠራ ነገር ማቅረብ ሳይሆን ልክ እንደ ንፍሮ የመሰለ ነገር ነው። ንፍሮ ደግሞ ብዙ ገንዘብም፥ ጊዜም፥ ጥበብም አይጠይቅም" አለኝ። ይህ ነው እንግዲህ በእሳት ተለብልቦ የበሰለ የመሰለ ግን ጥሬ መብል ያልኩት።

ከሙዚቃ መሣሪያ ሳንርቅ መነሣት ያለበት ነጥብ ደግሞ፥ እሺ ይሁን፤ አንድ መሣሪያ ብቻ ይንቻቻ። ግን የሙዚቃ መሣሪያ ድምጽና ጫጫታ የመልእክቱን ድምጽና ይዘት የሚውጥባቸው ጥቂት ያልሆኑ የካሴቶች መዝሙሮች መኖር ነው። ይህም መጤን ያለበት ነገር ነው። ምንም

የሙዚቃ መሣሪያ ውበት ቢሆንም መተኮር ያለበት ቅርጹ ላይ ሳይሆን ይዘቱ ላይ ነው፤ መልእክቱ ላይ ነው። መልእክቱ በድምጽ ወይም በሙዚቃ መሣሪያ መሸፈን የለበትም። የጥንቶቹን፥ ያየኖል ወይ፥ እጓዛለሁ በሰማይ ብርሃን ጮራ፥ ኮብልላ ነበረች ነፍሴ ከእግዜር መንገድ ወዘተ፥ እነዚህን መዝሙሮች ስንሰማ እነዚህ ባለ አንድ ወይም ባለ ዜሮ መሣሪያ ናቸው። የሙዚቃ መሣሪያ ወይም ተጫዋቾች ስላልነበሩ ነው? አይደለም። መሣሪያም የሰከኑ ተጫዋቾችም ነበሩ በዘመኑ። የአትኩረት ዒላማው ግን የት መሆኑ ይታያል።

## የድምጽና ድርሰት አራምባና ቆቦ/ግንባሩን ተኩሎ አፉን ተቀንድቦ

ከዚህ አያይዘን የደምጽና ድርሰትን መያያዝም ነክተን እንለፍ። አንዳንድ ክርስቲያኖች የገጣሚነት፥ የባለቅኔነት፣ ወይም የደራሲነት ዝንባሌ ስላላቸው ስንኞችን ይቋጥሩና የመዝሙር መልክ ይሰጡአቸዋል። የዜማ ተሰጥዖ ከኖራቸው ደግሞ ዜማ ጨምረውበት መዝሙር ያደርጓቸዋል። እንግዲህ ችግሩ ከዚህ በኋላ ነው የሚመጣው። እንዳይዘምሩ ድምጽ የላቸውም፤ እንዳይተዉት መዝሙር ጽፈዋል። ታዲያ ስለደረሱ ብቻ መዘመር ያለባቸው ይመስላቸውና እያማጡ ሲዘምሩ ይደመጣል። ይህ የእነርሱን ጉሮሮ ብቻ ሳይሆን የአድማጩን ጆሮም የሚያደክም ነገር ነው። አንዳንዶቹ ሊወልዱ የሚያምጡ ነው የሚመስሉት፤ ሌሎቹ ደክሞአቸው ዛፍ ስር ተቀምጠው የሚያንጎላጁ፤ ሌሎቹም መጫወቻውን ተቀምቶ የሚያለቅስ ሕፃን ይመስላሉ። እነዚህ ለግላቸው ይዘምሩ፤ ገበያ ላይ ለሚውል ካሴት ግን ጭራሽ ባይዘምሩ ይሻላል። ለእነርሱ ጥሩ የመሰላቸው ዝማሬ ሁሉ ለአድማጭም ይጥማል ብለው ገምተው ከሆነ ተሳስተዋል። መዝሙርን የሚመዝን እኮ አድማጭም ነው። ጥቂት አራጋቢዎች ሳይሆኑ ሰፊ አድማጭ። አድማጭ ይገምታል፤ ይገመግማል። እነዚህ እንግዲህ ድምጽ የለሽ የመዝሙር ደራሲዎች ናቸው።

ሌሎቹ ደግሞ ድምጽ አላቸው፤ ቆንጆ መረዋ ድምጽ አላቸው። ግን የመድረስና የመቀኘት ነገር አይሆንላቸውም። ታዲያ እነዚህ ደግሞ ድምጽ ስላላቸው ብቻ መዝሙር መድረስ ያለባቸው ይመስላቸውና ደፍረው የሆነ ነገር ይጽፋሉ። ደፋሮች ናቸው። እናም ቅጠል ቅጠል የሚል መዝሙር በቆንጆ ድምጻቸው ሲዘምሩ ይደመጣሉ። ሳር ሳር የሚል መዝሙር በቆንጆ ድምጽ። እነዚህ ሁለቱ ዓይነት ሰዎች መስጠትና መቀበል ቢችሉ፥ የመስጠትና የመቀበል ጸጋ ቢኖራቸው እንዴት ቆንጆ በሆነ ነበር! ያ ይደርሳል፤ ይህ ያርማል፤ ይህች ትዘምራለች። ውብ ነበር።

አንድ የመዝሙር ቡድን መሪያችን አንድ ጊዜ ሲያስተምረን ይህን ነገረን። አንድ የቡድኑ ዘማሪ መዝሙር ይዞ መጥቶ እንዲለማመዱ ሰጣቸው። መሪውም መዝሙሩን አየውና፥ "አስተካክለን በሚቀጥለው ሳምንት እንዘምረዋለን" አለው። መዝሙሩን ያመጣ ወንድምም፥ "ይህ ከጌታ የተቀበልኩት መዝሙር ነው፤ ወይ እንዳለ እንዘምረዋለን ወይም ይቀራል" አለው። [ከጌታ የተቀበልኩት የሚለው ሐረግ የዘማሪዎች የተወደደ ሐረግ ነው። አንዳንዶቹ ሲገልጡት ልክ

ከሰማየ ሰማያት ተጽፎ በፖስታ ታሽጎ የመጣላቸው ያስመስሉታል።] መሪውም፥ “ምን ከጌታ ትቀበላለህ? ከጌታ ብትቀበል ኖሮ መቼ ይኼ ሁሉ ስሕተት መቼ ይኖርበት ነበር? ይህ ከጌታ የተቀበልከው ሳይሆን እራስህ ቁጭ ብለህ የጫጫርከው ጭረት ነው፤ ቢበዛ የደረስከው ድርሰት ነው። ከጌታ የተቀበልኩት ብለህ አትመጻደቅ። ከወደድክ አርመህ አምጣው፤ ያለዚያ እኛ እናርመዋለን” ብሎ እቅጩን ነገረው። አንዳንድ የመዝሙር ደራሲዎች ራሳቸውን የማይታረም አድርገው ስለሚያዩ ከእነርሱ የተሻለ የሚመስላቸው ሰው እንዲያይላቸው አይሰጡም። ስለዚህ አንዳንድ መዝሙሮች ወይ ጥሬ ሳይሆኑ ወይ ሳይበስሉ እንዲያው ጠንዝተው ይኖራሉ።

## የደራው ገበያ - የዝማሬ ሙያነትና ንግድነት

በምዕራቡ ዓለም ክርስቲያናዊ ዝማሬ ከአገልግሎት ይልቅ ሥራና ንግድ ከሆነ ቆየ። እንደዚህ እየሆነ መምጣቱ ከፊት ይልቅ ገሃድ ከሆነም ከርሟል። እነዚህ ለንዋይ የሚዘምሩ ሰዎች አንዳንዶቹ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቢኖሩም አንዳንዶቹ በጌታ ቤትና በጌታ ውስጥ ጨርሶ የሉም። ቢኖሩም ለይስሙላ ነው። የእገሌ አገልግሎት ወይም ሚኒስትሪ እያሉ እንደ ፊኛ እየተፈነጠሩ ዛሬ አንድ ቦታ ነገ ሌላ ከተማ ናቸው። መዝሙሮች በአንደበታቸው አሉ፤ እነርሱ ግን የሚመገቡበትና ተጠያቂ የሚሆኑበት ቤተ ክርስቲያን የላቸውም። ታዲያ እነዚህ ሲዘምሩና ለገበያ ሲያመቻቹና ሲመቻቹ እየነገዱ እንጂ እያመለኩ አይደለም። ከጊዜያቸውና ከአሳባቸው የአንበሳ ቅርጫውን የሚወስደው ገንዘቡና የሰዎችን ስሜት እንዴት ማስደሰት መቻላቸው ነው። ብዙዎች የዝማሬውን አገልግሎት መኖሪያ እስኪያደርጉት ድረስና የአገልግሎትነቱ ጣዕም እስኪጠፋ አድርሰውታል። አገልግሎቱ የቡድን ከሆነም ሽኩቻና ግጭቶችም ይታያሉ። ከዚህ በላይ ደግሞ እነዚህ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ጥላ ስር ስላይደሉ መጋቢ የላቸው፤ በሥልጣን ስር አይደሉ፤ ለአመላለስና ለአኗኗራቸው ተጠያቂነት የላቸው፤ በአለሌነት ዘመናቸውን ይገፉሉ።

በምዕራቡ ዓለም ዘመነኞቹ መዝሙሮች በቤተ ክርስቲያን አምልኮ ወቅት ከተዘመሩ የባለቤትነት ዋጋ ወይም Royalty Fee ለዝማሬው ደራሲዎች እንዲከፈል ሕግ አስገድዶአል። ያለዚያ መዝሙሬን በጉባኤ ዘመሩብኝ፥ ነገዱብኝ፥ አተረፉብኝ፣ ብለው መክሰስ ይችላሉ። እንዲህ ሲሉ ራሳቸው ነጋዴና አትራፊ መሆናቸውን ማመንና መመስከራቸው ነው። ክስ የመሠረቱም ጥቂት አይደሉም። ቤተ ክርስቲያንን ነው የሚከስሱት። ቅዱሳን የጌታ ስጦታና ለእርሱ ሊሆን በተገባው መስዋዕት የቅዱሳን ባልሆነ ፍርድ ቤትና ፍርድ ሸንጎ ሲገኙ መቼም ያሳፍራል። የክሱና የፍርድ ቤቱ ነገር እስካሁን ጎልቶ ባይታይም የዝማሬ ሥራነትና ወይም ሙያነትና ንግድነት በአገራችን ዘማሪዎች ዘንድም ጎልቶ እየታየ ነው። ሥራ ወይም ሙያ ስል ከአገልግሎት መለየቴ ሲሆን ንግድ ስልም ከገንዘብና ከትርፍ ጋር ማቆራኘቴ ነው። ንግድ ባለበት ደግሞ አሻጥር አይጠፋም። ባይሆን ባይሆን አሻጥር እንኳ ቢቀር ቀጠንጠን ማድረግና የቶሎ ቶሎ ግርድፍድፍ ያለ ሥራ መሠራት ይኖራል። ልክ እንደ መርካቶ የመርዱፋ ጂንስ ማለት ነው። ሰማያዊ የካኪ ወይም የመርዱፋ ሱሪ ይሠሩና እላዩ ላይ Wrangler ብለው ልጣፍ ይሰፉበታል። ገበያ ሲደራ ወጡን

መረቅ እንደሚያደርጉት ዛሬ ዛሬ ሦስት አዲስ መዝሙር ላይ ስድስት አሮጌ ጨምረው እገሌ ቁጥር 4 እያሉ መሸጥ ትኩስነቱ የቀረ ልማድ እየሆነ ነው። ይህ የመዝሙር ችርቻሮ በእግረ መንገድ ቀረበ እንጂ የዚህ ዝግጅት ዋና ነጥብ ይህ አይደለም። ሆኖም፥ ለመዝሙሮች ቅጥንጥን እና ውኃ ውኃ እያሉ መምጣት ይህም የጎላ አስተዋጽዖ ስላለው መነሣት ስላለበት ነው። ማን ለአምልኮ እየታተረ፥ ማን ለገንዘብ እየማሰነ እንደሆነ የሰውን ልብ መመርመር የማይችል ሰው ማወቅ አይችልም። የሚታየውን ግን ለእርማት መናገር አስፈላጊ ነው።

እንግዲህ ዜማና ቅላጼ የግለ ሰብ ጣእም ከሆነና የዝማሬን ሥራነትና ንግድነት የአገልጋዮቹ ኅሊና ጉዳይ አድርገንም እንተወው <u>ካልን ማተኮር ያለብን አንድ መሪ ጉዳይ የመዝሙሮች ሕጸጽ ወይም ግድፈት ነው። ይህም ማለት፣ የመዝሙሮቹ ይዘትና የይዘቱ ወይም የተሠሩባቸው ነገሮች ስሕተት ላይ ይሆናል።</u> ይህንን የይዘት ግድፈት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች መድበን እንመለከታለን። እነዚህ ሦስት ዋና ዋና ነጥቦች፥

1፥ ስነ ጽሑፋዊ ውበት
2፥ ቋንቋዊ ይዘት
3፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ናቸው።

## 1፥ ስነ ጽሑፋዊ ውበት

መዝሙር ማለት በዜማ የተቀናበረ የመዝሙሩ ደራሲዎች የቋጠሩት ስንኝና የተቀኙት ቅኔ ነው። በግጥም የተጻፈና በዜማ የተላለፈ መልእክት ነው። የግጥም ጽሑፍን ከስድ ጽሑፍ ለየት የሚያደርጉት ባህርያት አሉ።

በርካታ ዘማሪዎች ከመዝሙሮቻቸው ሲደመጡ የግጥም ዋና ባህርይ ቤት መምታቱ እንደሚመስላቸው ይስተዋላል። እርግጥ ይህ የግጥም አንድ ባህርይ ነው፤ ዋናው ግን አይደለም። ዋናው የግጥም ጽሑፍ ባህርይ እምቅነት ነው።

## እምቅነት

ግጥሞች ከስድ ጽሑፍ ጋር ሲነጻጸሩ አጫጭር እና በጥቂት ቃላትና ሐረጎች ሰፋፊና ጥልቅ አሳቦችንና እውነቶችን የሚገልጡ ናቸው። እንግዲህ አጭርም ጥቂትም ሆነው ብዙ የመግለጥ

አደራ የሚጣልባቸው ከሆኑ ቃላቱ ምርጥና ጠንካራ፥ ገላጭና ስእላዊ መሆና አለባቸው። ይህ ነው እምቅነት።

የግጥም ቃላት ከመደዴ [ተርታ] ቃላት ወጣ ያሉ ናቸው። እንዲህ ከሆኑ ታዲያ ጊዜ ተወስዶ ቃላት ከቃላት ጋር ተያይተውና ተነጻጽረው ቀለል ያለው ተንሳፎ፥ ተንገዋሎ ሲቀር፥ ከበድና ኮራ ያለው፥ ምርጥና ጨዋ የሆነው የሚወሰድ መሆን አለበት ማለት ነው። ይህ በየትኛውም ቋንቋ የሚደረግ ሥርዓት ነው። ምሳሌያዊ አነጋገሮችንና ፈሊጣዊ አባባሎችን ብንወስድ ልክ እንደ ግጥሞችና ቅኔዎች በምርጥና ጥቂት ቃላት ተሠርተው [አንዳንዴም ራሳቸውም ግጥም ናቸው] ግን ሰፊና ግዙፍ አሳብ ወይም ጽንሰ አሳብን የሚገልጡ ናቸው። ለምሳሌ፥ “ሳይከካ ተቦካ” በሁለት ቃላት የተሠራ አጭር ፈሊጥ ነው። በሁለት ቃላት ብቻ። ግን ቢተረትሩት ረዝሞ የሚተረተር አሳብ አለው።

## ከገጣሚዎች እንቅብና መሶብ

የግጥሞችን የቃላት ምርጥነትና የተሰደረ አሰላለፍ ለማየት ከገጣሚዎች መጻሕፍት አንድ ሁለቱን አንሥቶ ማገላበጡ ብቻውን በቂ ነው። ዘማሪዎች ደግሞ ይህን ቢያደርጉ ይረዳቸዋል እንጂ አይጎዳቸውም። ከማውቃቸውና ከማደንቃቸው ገጣሚዎች አንድ ሁለት ምሳሌዎችን እንይ፤

*ሁላችን ሯጮች ነን፤ ሁሌ እንሮጣለን*
*ከእንጀራችን ኋላ*
*ምንም አሸንፈን ዋንጫውን ባንበላ።*

*ደረጀ በላይነህ የዕድሜ መንገድ፥ ሯጮች፥ ገጽ 53።*

*አንቺ ሰማይ ሆነሽ፥*
*እኔ መሬት ሆኜ፣*
*ስፋትሽ ሲሰፋ የኔም ስፋት ሰፍቶ*
*አያስደንቅሽም?*
*ሁሌ እየተያዩ . . .*
*መኖር ተለያይቶ።*

*ደረጀ በላይነህ የዕድሜ መንገድ፥ ሰማይና ምድር፥ ገጽ 29።*

ሌላ አንድ ልጨምር፤

*ፎከረሻል አሉኝ፥*
*እኔ እሱር አያርገኝ. . .*
*ሥጋውን ላሞራ*
*በትኜ ብልዘራ*

ነፍሱ በኪሣራ
ባትቦን እንዳቧራ
እኔ እሱን አያርገኝ

ጣድሽልኝ ይሉኛል - ድግስ የመከራ
መከረሽግል አሉ - ካግልክቱ ጋራ. . .

ምነው የኔን ኹነት
እንዲህ ዘነጋሽው?
ሕይወቴና ሞቴን
እንዴት አሳከርሽው?

ግዳይ ከናፈቀሽ
የሚሞት ፈልጊ ለኑሮው የቀና፥
እኔማ ለምኔ
የት አለሁኝና?

ወንድዬ አሊ *ውብትና ሕይወት፥ የት አለሁኝና፥* ገጽ 16።

በነገራችን ላይ፥ ወንድዬ ገጣሚ ብቻ ሳይሆን የተወደዱ መዝሙሮችም ደራሲም ነው። እነ *ድንቅ ብርሃን፥ አቤት ጥበብህ፥ ኃይሌም ዝማሬዬም፥ መቃብሩን ፈነቃቀለው፥* ሌሎችም በመቶዎች የሚቆጠሩ ውብ መዝሙሮች ደራሲም ነው። የስንኞቹን ውበት ከነዚህ ከተጠቀሱት መዝሙሮች ብቻ እንኳ ማየት ይቻላል። ወደ ነጥባችን ስንመለስ፥ የግጥም ስነ ጽሑፋዊ ጉልበት ያለው እምቅነቱ ላይ ነው። እምቅነት ደግሞ ከቃላት መካከል ብተመረጡ ቃላት ውስጥ የሚገኝ ንጥረ ነገር ነው። ከላይ እንዳየነው ሁለተኛው ግጥም፥ ሰማይ፥ ምድር፥ ርቀት፥ መተያየት፥ መለያየት። አንድ ላይ ሲለወሱ ቆንጆ ዳቦ የሚጋገርባቸው ቃላት ናቸው።

## ከቃሉ የቅኔ ገበታ

የመጽሐፍ ቅዱስን የራሱን አጻጻፍ ብንወስድ የስድ ጽሑፍም፥ የቅኔ ወይም የግጥሞችም ቅይጥ ነው። ከግጥሞቹ በከምችት ከምናገኘው ውስጥ መዝሙረ ዳዊት፥ ሰቆቃወ ኤርምያስ፥ እና መኃልየ መኃልይ ይገኙባቸዋል። ሌሎችም አሉ፥ እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ግን ቅኔ ወይም ግጥም ብቻ ሳይሆኑ መዝሙሮችም ጭምር ናቸውና ለዘማሪዎች የተለየ አብነት አላቸው። መኃልየ መኃልይ ማለት መዝሙረ መዝሙራት እንደማለት ነው። ሰቆቃወ ኤርምያስ ሰቆቃ ወይም እዬዬ ነው፤ ሙሾ ነው፤ የኀዘን እንጉርጉሮ። እነዚህ ግጥም ብቻ ሳይሆኑ መዝሙራትም ናቸው። የአይሁድ ስነ ግጥም ዋና ጠባይ ከእምቅነት ጋር የአሳብ አሰላለፍና አፈሳሰስ ነው እንጂ እንደኛ ግጥም የመጨረሻ ቃላት ድምጽ መስማማት ወይም ቤት መምታት አይደለም። ሌላው የአይሁድ ስነ ግጥም ዓይነተኛ ጠባይ ስዕላዊ ገላጭነት ነው።

## ሦስቱ ቅመሞች

ለዜማ የሚሆን ግጥም ለማግጠም ወይም ለዜማ የሚሆን ቅኔን ለመዝረፍ ቢያንስ ሦስት ነገሮች ያስፈልጋሉ ይመስለኛል። እነዚህም፥

ሀ፥ ስጦታና ተሰጥዖ
ለ፥ ቋንቋና እውቀት
ሐ፥ ጊዜ

## ሀ፥ ስጦታና ተሰጥዖ

ልክ የጸጋ ስጦታ ለመንፈሳዊ አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ ለአማኝ እንደሚሰጥ ሁሉ ገጣሚና የቅኔ ሰውም በተፈጥሮው ይህ ዝንባሌ ወይም ተሰጥዖ ያለው ሊሆን ይገባል። ይህ ማለት፥ ገጣሚ ሁሉ መዝሙር የሚወጣው ቅኔ ይደርሳል ማለት ሳይሆን፥ የመዝሙር ጸሐፊ ወይም ደራሲ ሁሉ ግን የቅኔና የግጥም ተሰጥዖ፥ ዝንባሌ፥ ችሎታ ሊኖረው ይገባል ማለት ነው።

## ለ፥ ቋንቋና እውቀት

የዝማሬ ቋንቋን ለብቻው ስለምመለስበት ይህንን ንዑስ ርእስ የቋንቋ እውቀት ልበለው። የመዝሙር ቃላት እምቅነትና ከብዙ ቃላት የተመረጡ መሆን ከኖረባቸው ገጣሚው ቃላትን ማማረጥ እስከሚችል ድረስ የዚያ የሚደርስበት ቋንቋ እውቀት ሊኖረው ያስፈልጋል። ያለዚያ ውጤቱ በተራ ብቻ ሳይሆን ከተራም ባነሱ ቃላት የተሠሩ መዝሙሮች ይሆናል። የሚዘመርበት ቋንቋ የግድ አንደኛ ወይም አፍ መፍቻ መሆን አለበት ማለት አይደለም። አማርኛ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ያልሆኑ ግን ውብ መልእክት የሚያስተላልፉ ዘማሪዎች አሉን። ከዚህ የሚያያዘው ደግሞ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነገር በቋንቋው ውስጥ ጠልቆ ሄዶ ለአድማጩ እንግዳ የሆኑ ቃላትን ከዚያ ቋንቋ ውስጥ እየፈለቀቁ አውጥቶ መራቀቅም አይደለም።

## ሐ፥ ለስነ ግጥም አስፈላጊ ከሚሆኑት ነገሮች 3ኛው ጊዜ ነው።

ተሰጥዖም፥ የቋንቋው እውቀትም ኖሮት የመዝሙር ግጥምን የጻፈ ሰው ከጻፈው በኋላም ጊዜ ወስዶ ማየት፥ ማንበብ፥ መከለስ ያስፈልገዋል። ይህንን ሲያደርግ ቃላቱን ብቻ ሳይሆን ይዘቱንም ለማረም እድል ያገኛል። ጸሐፊም ከላሽም አራሚም እርሱ ብቻ ከሚሆን ደግሞ ሌላ

ወይም ሌሎች ሁነኛ የሚላቸው በዚህ መስክ የተሰማሩ ሰዎች ቢያዩትም ይበልጥ ውብ ነው። በጊዜ ውስጥ ወደ ላይ የሚንሳፈፉም ወደ ታች የሚዘቅጡም ቃላት ይኖራሉ፤ በጊዜ ውስጥ። ስለዚህ ጊዜ መስጠት መልካም ነው።

በ1980ዎቹ መጀመሪያ አንድ ዘማሪ፥

ከፊቴ ዮርዳኖስ ከኋላዬ ፈርዖን
ምንም አስጨናቂ አስቸጋሪም ቢሆን
እንደ በትረ ሙሴ እጄን አነሣለሁ
ባሕር ይከፈላል እኔም አልፈዋለሁ

ብሎ ዘምሮ ነበር። ፈርዖንንና ዮርዳኖስን ምን አገናኛቸው? እራሱን ሳይሆን እስራኤልን ወክሎ ዘምሮ ከሆነ ማለት ነው። እስራኤል ዮርዳኖስ ሲደርሱ ያ ፈርኦን ከሠራዊቱ ጋር ወደ ባህሩ ገብቶ ከሆነ ከሞተ 40 ዓመት አልፎታል እንጂ ከኋላቸው አልነበረም። ከሁለት ዓመታት በኋላ ያው ዘማሪ ያንኑ መዝሙር ዘምሮት ሰማሁ፤ አሁን ግን አርሞና አስተካክሎት፣ *ከፊቴ ቀይ ባህር ከኋላዬ ፈርዖን* ብሎ ነበር የዘመረው። ግሩም እርማት ነው። ጊዜ መስጠት የሚያስፈልገው እንግዲህ እንዲህ ያሉ ግድፈቶችን ለማጥራት ነው። አውቆ የተደረጉ አይደሉም፤ በሚታወቁበት ጊዜ ግን ይጠራሉ፥ ይገረዛሉ። ይህንን የመሰሉ እርማቶች ከመዘመራቸው በፊት ኖረው ቢሆን ምንኛ ድንቅ ነበር! ብዙ ያልተሳሳቱ መዝሙሮችን እንሰማ ነበር፤ ወይም ብዙ የተሳሳቱ መዝሙሮች ከስሕተት በታረቁ ወይም በተስተካከሉ ነበር።

ዘማሪዎች መዝሙርን በደረሱበትና በሰለ ብለው ገበታ ላይ በሚያቀርቡበት ግዜ መሃል ቁጭ ብለው ጊዜ ወስደው ኮስተር ብለው የጻፉትን ቢያዩ ብዙ የሚያርሙት ነገር ያገኛሉ። ብዙው ስሕተት መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ካለማንበባቸው የተነሣ የሚመጣ ጣጣ ነው። አንዳንድ ዘማሪዎችማ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ መስጠት አይደለም መጽሐፍ ቅዱስ ያላቸውም አይመስሉም። እየተዋሱ አንብበው የሚመልሱና እንደገና ተውሰው የሚያነብቡ ነው የሚመስሉት። ዳዊት ጎልያድን በንድርነው ወንጭፎ መትቶ የገደለው? በድንጋይ ነው። ግን ስንት ዘማሪዎች ናቸው በጠጠር እንደገደለው የዘመሩልን? በጠጠርና በድንጋይ መካከል ልዩነት የለም? አለ፤ ቢያንስ የመጠን። ጠጠር ማለት ይህቺ ቅልቦሽ ወይም ገበጣ የሚጫወቱባት ብይ የምታህል ነገር ናት። ድንጋይ ከዚያ ይበልጣል። ወይስ ከተሜ ልጆች ወንጭፍ የሚሏት በባላ ባሊቾ ላይ በላስቲክ ተይዛ የምትወነጨፍ አለች፤ እርሷን እያሰቡ ይሆን የዘመሩት? ከሆነ እዚያች ላይ የሚደረገው ድንጋይ ሳይሆን ጠጠር ነው፤ [የዳዊት ወንጭፍ ግን ያ አይደለም።] ወይስ ከድንጋይዋ መጠን ቀነስ አድርጎ በእግዚአብሔር ክብር ላይ ጨመር ለማድረግ ይሆን? ቃሉ የትርጉም ልዩነት ከፈጠረ ለኛ የመሰለንን ሳይሆን የምጩን ቃል መጠቀም ነው ያለብን። የምንጩን ቃል መጠቀሙ ጥበብ ነው።

ሙሴ በትሩን ይዞ ሲኖር ሳያውቅ እባብ ነበር ይዞ ይዞር የነበረው?
ሙሴን ጠራና በትሩን አስጣለው

ለካስ እባብ ነበር አቅፎት የሚዞረው
ካባቴ የወረስኩት የጥንት ነው ያልኩት
የሚናደፈውን ሸሹሁ አመለጥኩት

ይህ ዘማሪ መሸሹና ማምለጡን ማወጁ መልካም ሳለ ሙሴን እባብ ተሸክሞ ዟሪ ማድረጉ ምንድርነው? ወይስ ታሪኩን በከፊል ብቻ ነው ዘማሪው ያነበበው? በትሩ ነው እኮ እባብ የሆነው፤ ለምልክት እንጂ ቀድሞ እባቡ በትር ሆኖ በእጁ አልነበረም። ደግሞስ አስጣለው ወይስ መልሶ አስጨበጠው? ያንን ክፍል ትክ ብሎ ማየቱ ብቻ በቂ ሆኖ ወደ እንዲህ ያለው የተሳሳተ ድምዳሜ ከመድረስ ሊያግድ ይችል ነበር። ከይድረስ ይድረስ ግጥም በኋላ ጊዜ መስጠት ተገቢ መሆኑ ወይም ሰባኪን ተከትሎ አለመድረስ ተገቢነቱ ለዚህ ነው።

እስካሁን የተመለከትነው ዋና ነጥብ ስነ ጽሑፋዊ ውበትን ነው። በውስጡ ንዑሳን ነጥቦች ቢኖሩም ዋናው አሳብ የመዝሙር ጽሑፉ ነው።

## 2፥ የመዝሙር ቋንቋ

ቋንቋ መግባቢያ ነው ወይም የመግባቢያ መሣሪያ ነው ሲባል ደጋግመን ሳንሰማ አንቀርም። እውነት ነው። በዘፍ. ፲፩ እንደምናገኘው ሰዎች አንድ ቋንቋ ነበራቸው፤ ተግባብተው ሥራ ጀመሩ፤ ተደበላለቀባቸው፤ ሥራቸው በጅምር ቀረ፤ እነርሱም ተበታተኑ። ቋንቋ መግባቢያ ነው።

እንግዲህ ቋንቋ መግባቢያ ከሆነና አንድ ዘማሪም የሚያዜመውን መዝሙር አድማጩ እንዲረዳው፥ እንዲገባውና እንዲተላለፍለት የሚፈልግ ከሆነ በመዝሙሩ ውስጥ ያሉትን ቃላት ግልጽና አሻሚ ያልሆኑ ሊያደርጋቸው ይገባል። የመዝሙር ቃላት የተመረጡ መሆን አለባቸው ማለት የተራቀቁና አድማጩ እነዚያን ቃላት ለመፍታት መዛግብተ ቃላት መበርበር አለበት ማለት አይደለም። ያ እንኳ ቢቀር፥ "እንዲህ ሲል ምን ማለቱ ነው?" ወይም "ይህን ስትል ምን ማለት ፈልጋ ነው?" ብሎ አድማጭ መጠየቅ የለበትም። እንደ በገና ደርዳሪዎች ሰምና ወርቅ እያዜሙ ከሆነ ያ ሌላ ነው። ካልሆነ ግን አሻሚ መሆን የለበትም።

በቀላል አነጋገር፥ አንድ ዘማሪ ሙሉ በሙሉ የማያውቀውን ቃል እንዲሁም በአድማጩ ማኅበረ ሰብ ዘንድ የማይታወቅን ቃል መዝሙር ውስጥ መሳግ የለበትም። ካስገባም አጥብቆ ማጤንና "በእርግጥ አስፈላጊ ነው?" ብሎ መጠየቅ አለበት። መዝሙሩ አማርኛ ከሆነ (ስለ አማርኛ መዝሙሮች ነው እየተነጋገርን ያለነው) ያ መጤን ያለበት ቃል አማርኛ ሊሆን ይችላል። አማርኛ ከሆነ ያ ቃል ጥንታዊ ወይም ዘመናዊ ሊሆን ይችላል፤ ገጠሬ ወይም ከተሜና የአራዳ ቃል ሊሆን ይችላል፤ ቀበሊኛ ወይም ፈሊጣዊ አነጋገርም ሊሆን ይችላል። መዝሙሩ በአማርኛ ሆኖ ቃሉ አማርኛ ካልሆነ ደግሞ ከሌላ ቋንቋ የተወሰደ ነው። ከሌላ ቋንቋ ከተወሰደ ለምን ተወሰደ?

ልክ አንዳንድ ሰባኪዎች [ለአድማጫቸው ደንታቢስ በመሆን] የእንግሊዝኛ ቃላት እንደ ጉራማይሌ እየዶሉ እንደሚሰብኩት ማለት ነው። ቃል ስለጠፋ ነው ወይስ ለመራቀቅ ነው?

ዓለምን ዞር ብለ ሙይልን አላልንም
ትጥቅን የሚያስፈታ

እነዚህ የአንድ ጎራ ቃላት ወይም ሐረጎች ናቸው፤ ቢሆንም ይገባሉ፤ ምንም እንኳ አሻሚ ቢመስሉም። ይህኛው ግን በጣም የቀጠነ ነው፥

ተሸዋወዱ ገና ውልደቱን የሚጠባበቁ።

[ለመዝሙር የማይመጥን ቃል ነው]

አንድ ሦስት ያህል መዝሙሮች ላይ ምስ የሚል ቃል ሰምቻለሁ። በአንዳንድ ሃይማኖቶች እንደሚደረገው ካለ አጉል ልማድና እስራት የተፈታን ሰዎች ስለሆንን መዝሙሮቻችን ውስጥ ይህ ቃል የመገኘቱ አስፈላጊነት አልታየኝም። ምስ በልማዳዊ ሃይማኖቶች ለአጋንንት የሚዳረግ መስዋእት ነው። የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ምስን እንዲህ ሲል ይፈታዋል፤ "ምስ፥ ምስህ፥ ዳረጎት፥ ጉርሻ፥ ቅምሻ፥ ለዛር፥ ለጋኔን፥ ለቡዳ የሚሰጥ የሚፈነጠቅ፤ ለብትርና ለጥፊም ይሆናል፤ 'ምሱን ስጠው' እንዲሉ" (ገጽ 611)። ምናልባት መለስ ያለውን የኋላኛውን፥ የመጨረሻውን ትርጉም ወስደው ነው እየዘመሩ ያሉት እንበል፤ ግን በአንዳንድ ሃይማኖቶች አጋንንትን ያስወጡ እየመሰላቸው የሚገብሩለትን ልማዳዊ ቋንቋ በክርስቲያናዊ መዝሙር ውስጥ መጠቀም አላስፈላጊ መልእክትን ያስተላልፋል። ይህኛው አዘማመርና አባባልስ ከቃሉ ጋር ይሄዳል?

የምሥራች ያለኝ ያለኝ ምሱን ጌታ ይክፈለው
ጌታ እኔን ሲሸልም ለርሱም አክሊል አለው።

እነዚህ የልማዳዊ ሃይማኖት ቃላት ናቸው፤ ክርስቲያናዊም መጽሐፍ ቅዱሳዊም አይደሉም።

ኮከባችን ገጥሞአል የኔና የእርሱ
ማንም አይለየኝም እኔን ከንጉሡ።

እንዲህ ያለው ቃል መጽሐፍ ገላጮች ብዙውን ጊዜ ሊጋቡ ላሉ ሰዎች ሲጠነቁሉ የሚጠቀሙበት ነው። ቃል ፍለጋ አገር ምድሩን አስሰን የጠንቋዮችን ቃላት መጠቀም ከያዝን ወይ ርቀናል ወይም ገና ኋላ ቀርተናል። የሕዝብ ቋንቋ እየተጠቀምን ከመሰለን አድማጮችን ወይም ዒላማችን የተወሰነው የሕዝብ ክፍል መሆኑን ዘንግተናል።

አንዳንዴ አማካዩ አድማጭ ብቻ ሳይሆን ዘማሪዎችም ራሳቸው የማያውቋቸውን ቃላት ትርጉማቸውን ሳያጤኑ ለመጠቀም የሚቸኩሉ ይመስላሉ። አንድ በጣም ያለቦታው እየገባ የተዘመረ ቃል፥ ብዙ ዘማሪዎች የተጠቀሙበት ቃል ጸባዖት የሚል ቃል ነው። ይህን ቃል ብዙዎች እንደ አርያም ወይም ጽርሐ አርያም፥ ወይም ሰማየ ሰማያት ወይም የእግዚአብሔር ማደሪያ መንበር አድርገው ነው የዘመሩት።

ከክብር ጸባዖቱ ገናናው ዙፋን ስር ካለው...
መልሴን ከጸባዖት ሲመጣልኝ ሳየው...
ረድኤታቸው ከተፍ ይላል ከጸባዖት...
ጸባዖት ምስጋና ይሞላ፤ ጸባዖት አምልኮ ይሞላ...
ከጸባዖት ወጣ የድል ምስጋናቸው...
አምልኮ ምስጋናችን ገብቷል ጸቦዖቱ...

እነዚህ ሰዎች ይህንን ቃል የተጠቀሙት እንደ እግዚአብሔር መኖሪያ፣ እንደ እግዚአብሔር ማደሪያ አድርገው ነው። ግን ስሕተት ነው። ጸባዖት በመጀመሪያ የዕብራይስጥ ቃል ነው። ቢሆንም እንደ አሜን ወይም ሃሌሉያ እንዳለ ወደ አማርኛም ወደ ሌሎች ቋንቋዎችም የተወሰደ ቃል ነው። ይህን ቃል በተሳሳተ ትርጉም የዘመሩት ዘማሪዎች ቢያጤኑት ወይም ትርጉሙን ቢፈልጉት ኖሮ ወይም ቃሉ የተጠቀሰበትን ቦታ፥ ቃሉ በአዲስ ኪዳን አንድ ቦታ ተጠቅሶአል በሮሜ 9፥ 29 እና ኢሣ.1፥9 ላይ ተጠቅሶአል፤ እነዚህን ሁለት ቦታዎች በጥሞና ቢያስተያዩ ቃሉ (ጸባዖት) “ሠራዊት” ማለት መሆኑን ማወቅ አይሳናቸውም ነበር። እንግዲህ እነርሱ ስተው አድማጩንም ቡቃያውንም ዘማሪ ይዘውት ሲነጉዱ ነው የሚታየው። አዲሶቹ ዘማሪዎችም ያንኑ ተከትለው፥ ያንኑ ስሕተት ሲደግሙ ነው የምንመለከተው።

አቤንኤዘርስ? እስካሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል ማለት ነው? አይደለም። አቤንኤዘር ማለት በቀጥታ ሲተረጎም የረድኤት ድንጋይ [ዕብነ ረድኤት] ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ ሲል እንዲህ አለ ብሎ የሚጽፋቸው የቃላት ወይም ሐረጎች አገብብ ምክንያቱን መናገሩ ነው እንጂ ትርጉሙን መናገሩ አይደለም። ያለበትን ምክንያት ነው እየተናገረ ያለው። ለምሳሌ፣ ርኖቦት ማለት ሰፊዎች ወይም ሰፊ ቦታዎች ማለት ነው እንጂ በቦታው እንደተጻፈው፥ “አሁን እግዚአብሔር አሰፋልን፥ በምድርም እንበዛለን” ማለት አይደለም። የተጻፈው እንዲያ የተባለበት ምክንያት እንጂ ትርጉሙ አይደለም። አቤንኤዘርም እንደዚሁ ነው።

አዶናይስ? ይህኛው ቃል በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጨርሶ የለም። ግን ሁሉም እንደሚያውቀው ሁሉ ይዘመራል።

አዶናይ ጌታ ብለው ያንግሡህ...
አዶናይ አዶናይ የለም ካንተ በላይ...
አዶናይ ነው እግዚአብሔር...
አምላኬ አዶናይ ነው የለም የሚሳነው...
አዶናይ ጌታዬ መሸሸጊያ ሆነኝ...

መደዴው [ተርታው] ክርስቲያን ይህን ቃል አያውቀውም። አዶን ወይም አዶናይ የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጌታ ተብሎ ተተርጉሞልን እያለ፥ ጌታ የሚለው ቃል ደግሞ በጣም በቂ ሆኖ እያለ አዶናይ ብለን የኋሊት መልሰን ለምን እንተረጉመዋለን? የምንዘምረው አማርኛ ቃሉ ዕብራይስጥ። አማራጭ ሳይጠፋ። አማራጭ ባይኖር [ወይም የቀደሙቱ ከመተርጎም ይልቅ ቃሉን እንዳለ ከጻፉልን] አሜን የሚለውን ቃል አሜን ወይም ሃሌሉያን ሃሌሉያ ብለን እንጠቀምበታለን። ለዚህኛው ግን ትርጉም አለን፤ የኮራ ትርጉም። ለምን ያንን አንጠቀም?

ሻሎም ለዘለዓለም...
ገና ነው ዘንድሮስ ካቦድ ነው...

ሻሎምም ዕብራይስጥ ነው። ካቦድም እንደዚያው። ምንድርነው ካቦድ? ስንትስ አድማጭ ነው የዚህን ቃል ትርጉም የሚያውቀው? አዶናይ፥ ኤሎሂም፥ ሻሎም፥ ካቦድ፥ ከሆነ ቦታ ፍንጥቅ ያለችልንን ቃል እንደምንም መዝሙራችን ውስጥ እናስገባ ካልን አጉል ጉራማይሌ መሆኑ ነው።

አንድ መዝሙር ላይ አንዱ በልዩ ልሳን ይለዋል። [ሺህ ጊዜ ሺህ] ስለ ልሳናት በጉባኤ እንዴት መሆን ጳውሎስ በ1ቆሮ. 12 እና 14 ሲናገር ግቡ ማነጽ መሆኑን ነው የጻፈው። ስለዚህም ነው መተርጎም ያለበት፤ ወይም ካልተተረጎመ መነገር የሌለበት። እዚህ ደግሞ ለገበያ የቀረበ መዝሙር ላይ ይህን መዶል ማንን እና እንዴት ለማነጽ ነው? ደግሞ ቀደም ሲል መዝሙር ተደርሶና ታይቶ፥ ታርሞና እንደገናም ታርሞ መዘጋጀት እንዳለበት ተመልክተናል። ይህ የሌላ ልሣን ዜማ የተደረሰ አለመሆኑ የታወቀ ነው። ለገበያ ሲቀረጽ ይህን ማድረግ አድማጩን መናቅና መሸንገል ነው።

## 3፥ የመዝሙር ይዘት

ይዘት ሲባል የመዝሙሩ ጭብጥ፥ መልእክት፥ ሊተላለፍ የተፈለገው የታሰበው እውነት ማለት ነው። መዝሙር መልእክት ነው፤ እንደ ስብከት፥ እንደ ትምህርት፥ እንደ ተግሣጽ፥ እንደ ምክር ይዘት ያለው መልእክት ነው። ይዘቱ ደግሞ ክርስቲያናዊ ሆኖ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ስነ መለኮታዊ መሆን አለበት።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሲባል አንድም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈውን እውነት እንዳለ በቀጥታ ማስተላለፍ ነው። ሌላም የቃሉን አሳብ ሳያዛንፉ ሳያዛቡ ማስተላለፍ ነው። እንዳለ በቀጥታ ማስተላለፍ የተጻፈውን በዜማ ማንበብ ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌዎች አሉ። መዝሙር 23 በአንድ ሁለት ዘማሪዎች እንዳለ ተዚሞአል። አንደኛው ላይ ያለው እንግሊዝኛው ለአማርኛ አድማጮች ምን ያህል እንደሚገባ ወይም እንግሊዝኛው ለእንግሊዝኛ አድማጮች ምን ያህል እንደሚጥም መለካት አይቻልም። ቢሆንም እንዳለ መዝሙሩ [የእግዚብሔር ቃል] ነው የተዘመረው። ሌላ መዝሙር፥

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ...

ይህ ምንም መከለሻ ያልገባበት ነው። ይዘቱ አልተለወጠም እንዳለ ነው የተዘመረው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሲባል ይህ ነው።

ስነ መለኮታዊ ሲባልም ከመሠረታዊው የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር የሚስማማ፥ የማይጋጭ መልእክትን ማስተላለፍ ነው። እንግዲህ ክርስቲያናዊ መዝሙር በቀጥታ ከቃሉ የተወሰደ ከሆነ ቃሉ ነው፤ ካልሆነ ደግሞ ከቃሉ ጋር መስማማት አለበት እንጂ መጣላትና መጋጨት የለበትም።

## የሰባኪ ቋንቋ በዘማሪ ላንቃ

*መጽሐፉ ምን አለ?*
*ትሸነፋለህ አላለም፥ ትዋረዳለህ አላለም፥ ትታመማለህ አላለም፥ ትደኸያለህ አላለም፥...*

*በመጀመሪያ መጽሐፉ ያለውን ትተን ያላለውን ነገር እየፈለግን እንዘምር ቢባል አይቻልም። ይህ ብቻውን ወደ መዘላበድ ይወስደናል። ምክንያቱም ያላላቸው ብዙ ነገሮች አሉ። የዚህ መዝሙር አዝማች መጽሐፉ ድል ያንተ ነው ድል ያንቺ ነው ይላል ይልና ድል ስለመንሳት ወይም ድል ስለመሆን መናገሩ ይመስላል ስለ መታመም፥ ስለ መደኸየት፥ ስለ መዋረድ ይናገራል። አሁን ይህ በሕመም ላይ ለሚገኙ፥ በተፈጥሮ አደጋም በሰው ሥራም በአሳዳጆችም ንብረታቸው በግፍ ለወደመባቸውና ይህን በመሰለ መንገድ እያለፉ ላሉ ምእመናን ምን መልእክት ያስተላልፋል? መልእክቱ ክርስቲያን መቸገር፥ መታመም ወዘተ የለበትም የሚል ነው። ወይም በተቃራኒው ከወሰድነው ባለጠጋና ሕመም የማይነካው መሆን አለበት ማለት ነው።*

*ግን ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው እውነት? መከራን ሁሉ ድል እንደመነሳት ከቆጠርን ያዕቆብ አልተሰየፈም? ዮሐንስና ጴጥሮስ አልታሰሩም? ሐዋርያትስ ብዙዎቹ፥ ሁሉም ማለት ይቻላል ሰማእታት አልሆኑም? ጳውሎስ በመከራና በመታረዝ አላገለገለም? ጢሞቴዎስ፥ አፍሮዲጡ፥ ጥሮፊሞስ እነዚህ አልታመሙም? ጳውሎስ ራሱ የሥጋው መነሰሚያ የተሰጠው ሰው አልነበረም? ይህ ሁሉ መከራ ሊባል አይችልም? ይህ ሁሉ እንግዲህ ከመስቀሉ ወዲህ ነው፤ ከአዲሱ ኪዳን ወዲህ የሆነ ነው። ይህ የ"ተናገር ይሆንልሃል" ስብከት በዜማ ከሆነ ለነዚህ ቅዱሳን አልሠራላቸውም ማለት ነው። ይህች ዘማሪ መጽሐፏን ጠንቅቃ መርምራ ወደዚህ ድምዳሜ ደርሳለች። ጌታም ሆነ ሐዋርያቱ ግን እንደዚህ አላስተማሩም። ወይስ መጽሐፉ ያለችው መጽሐፍ ቅዱስን ሳይሆን ሌላ መጽሐፍ ይሆን? ካልሆነ ይህን በተመለከተ የጌታ ትምህርት "በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ" ነው። ይህን በተመለከተ የጳውሎስ ትምህርት "በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ" ነው።*

*እንዲህ ያሉ መዝሙሮች ብዙውን ጊዜ ሰባኪን ተከትለው የሚመጡ ናቸው። ዘማሪዎች የሰባኪዎች በቀቀኖች መሆን የለባቸውም። ሰባኪ የተናገረውን ነገር ብቻ በዜማ መድገም ጥበብ አይደለም። አንድ ዘማሪ አንድ ጉባኤ ላይ ሰባኪው ሲሰብክ ይጽፋል። ማስታወሻ የሚወስድ ይመስላል። ለካስ መዝሙር እየደረሰ ነው። ኋላ እዚያው "የተሰጠው" መዝሙር መሆኑን ተናግሮ ዘመረ። ከሰባኪው ስብከት ጋር አብሮ እንዲሄድ ብሎ የሞከረው ሙከራ ነው፤ እና ዘመረው። እኛም እንዲያው በግርድፉ የተሠራውን አኘክነው ጥሬውን መዝሙር፤ ቆረጠምነው ቢባል ይሻላል።*

*አንድ [የመዝሙር ደብተር መያዝንና የመዘምራን ልብስ መልበስን የሚጸየፍ] ሰባኪ ደግሞ፥ "የዘመኑ ዎርሺፕ እስፖንቴኒየስ ዎርሺፕ ነው፤ የዘመኑ መዝሙርም እንደዚያ መሆን አለበት" አለና በቤተ ክርስቲያኒቱ ያሉትን ዘማሪዎች ወደ መድረክ ጠራና ከዚያ በፊት ያልዘመሩትንና የማያውቁትን ዜማና ቃላት እዚያው እመድረኩ ላይ ፈጥረው እንዲዘምሩ አደረገ። መዝሙር ብለው እህል ውኃ የማይል ነገር ያላዝኑ ጀመር። የአንዷ ልቅሶ ይመስላል፤ እዬዬዋን የምታስነካ ሙሾ ደርዳሪ ትመስል ነበር። የአንዱ [ከነይዘቱ] ከኧረ ጎራው ቀረርቶ ትንሽ ነው የሚለየው፤ ትንሽ። የመልእክቱ ዝባዝንኬነት አይነሣ። እንዲህም አለ። በግል በአምላካችን ፊት ሆኖ ማምለክ አንድ ነገር ነው፤ በጉባኤ ፊት ከኃላፊነት ጋር መሆን ግን ሌላ ነገር ነው። ታትሞ ገበያ ላይ ለሚውለው ደግሞ ይበልጥ ጥንቃቄ ሊበጅለት ያስፈልጋል።*

## ፉርጎውም ሐዲዱም ጤናማ መሆን አለባቸው

አንዳንድ ቃላት አሉ ለእግዚአብሔር መጠቀምም ማሰብም የሌለብን፤ ሰውን ብቻ የሚገልጡ ቃላት ናቸው። [ለምሳሌ] የሰው ዙፋንና መንግሥት ሊገረሰስ ይችላል፤ የእግዚአብሔር መንግሥትና ዙፋን ሊገረሰስ እንደማይችል መዘመር ወይም እንደሚችል ማሰብ አስፈላጊ አይደለም። ይህ ሊሆን እንደሚችል መታሰብም የለበትማ! መገርሰስ ማውደም፥ ማፈራረስ ማንኮታኮት ነው። ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ዙፋን ይህ ከቶ መታሰብም የለበትም።

*ጀግና ነህ ጀግና...*

እግዚአብሔር ጀግና ነው? ጀግና ማለት ምን ማለት ነው? ጀግና ቢያሸንፉም ባያሸንፉም ከእኩያ/አቻ ወይም ከሚበልጥ ኃይለኛ ጋር በድፍረት መጋፈጥን የሚያሳይ ቅጽል ነው። ከሚያንሰው ጋር የሚጋፈጥ ሰው ጀግና አይባልም። እንግዲህ ከማን እኩያው ወይም የሚበልጠው ጋር ነው እግዚአብሔር የተፋለመውና ጀግና የተሰኘው? እግዚአብሔርን "ጀግና" ስንል እያገነንነው፥ ከፍ እያደረግነው ያለን ይመስለን ይሆናል። ግን ወደ ሰው ተራ እኮ እያወረድነው ነን። ወደ ሰው ተራ እንኳ ባናወርደው ከእግዚአብሔርነቱ ዝቅ እያደረግነው ነን። ምክንያቱም ጀግና ከእርሱ ካነሰው ጋር ተዋግቶ ጀግና አይሰኝም። ጀግና የሰው፥ የአርበኛ ማዕረግና ቅጽል ነው። እግዚአብሔር እኩያ የለውም፤ በላጭ የለውም። ኃያል ነው? አዎን። ይህ መሆኑ የተጠቀሰበት ቅጽል ነው። ሁሉን ቻይ ነው? አዎን፤ ብቻውን ሁሉን ቻይ ነው። ጀግናስ?

*ድል ድል ይሸተኛል...*<br>
*ኧረ እኔስ ድል ነው የሚታየኝ...*<br>
*ዘመኑ የድል ነው የመከናወን...*

እውነት ይህ ዘመን፥ ዘመኑ እንዳለ በሙሉው የድልና የመከናወን ዘመን ነው? ወይስ ክርስቲያን ድል አድራጊ ኑሮን ለመኖር ማድረግ ማድረግ ያለበትና መከተል የሚጠበቅበት ነገሮች አሉ? ይህ ዘመን የጅምላ ድል፥ የጅምላ በረከት፥ የጅምላ ፈውስ አዋጅ ዘመን ነው እየሆነ የመጣው። ሰባኪዎች የሚሉትም ይህንን ነው፤ ዘማሪዎችም ይህንን ይደግማሉ። ጌታ እኮ አሸናፊዎች ብቻ ሳይሆን ከአሸናፊዎችም በላይ አድርጎናል። ግን ይህ ዘመን፥ ዘመኑ እንዳለ በሙሉው በምን ልዩ ሆነ? የትስ ነው የተጻፈው? ይህንን ዘመን ካለፈው ዘመን ልዩ የሚያደርገው ነገር ምንድርነው? ወይም ይህንን አሁን ያለንበትን ዘመን ከሚመጣው ዘመን የተለየ ያደረገው ነገር ምንድርነው?

*ኢትዮጵያ ሆይ ስሚ ትንቢት ልናገር*<br>
*ከንግዲህ አይሆንም ጭንገፋና ውርደት...*

ስለ ኢትዮጵያ የተነገረውማ ብዙ ነው። ምን ያልተነገረ፥ ምን ያልተዘመረ መልካም ትንቢት አለ? እንደ ትንቢቱ ብዛትማ ቢሆን ኢትዮጵያ እንደ ሮኬት ተተኩሳ ቀድሞውኑ እከዋክብት ጉያ በደረሰች ነበር! ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሳለች። ታሪካዊ የሆኑትን ትተን ትንቢታዊ የሆኑትን ብቻ እንኳ ብንመለከት <u>እና</u> ሁሉም ገና እንዳልተፈጸሙ ቢመስለን፥ መልካም ከሆኑት ትንቢቶች ይልቅ አስፈሪዎቹና አደጋ የተነገረባቸው እንደሚበዙ አስተውለናል? ለምሳሌ፥

እናንተም ኢትዮጵያውያን ደግሞ በሰይፌ ትገደላላችሁ። ሶፎ.2፥12
የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ አየሁ። ዕን.3፥7

እነዚህን የዘመረ/ያስጠነቀቀ ዘማሪ አላየሁም፤ አልሰማሁም። ይህ አፍራሽ ነዋ! አይዘመርም። ኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር ልክ የበኩር ልጅ እንደሆነች ያህል ሲነገረን ነው የኖርነው። ይህንን ሽንገላ አሁንም ለብሰነው እየኮራን እየኖርን ነን። በአፈ ታሪክና በሃይማኖታዊ ታሪክ ሲነገረን የኖረው እግዚአብሔር [እንዲያውም] እስራኤልን ትቶ እኛን መምረጡ ነው። ይህ ግን ተረት ብቻ ሳይሆን የተሳሳተ ተረት ነው። ቢገባን ግን [ኢትዮጵያ] ከሱዳን ወይም ከቻይና ለእግዚአብሔር የተለየች አይደለችም። እግዚአብሔር ብዚህ ዘመን አንድ ሕዝብ ብቻ ነው ያለው። ያም በክርስቶስ ደም የተዋጀው ክርስቲያን ሕዝብ ነው። እስራኤልም እንኳ በዚህ ዘመን በክርስቶስ በኩል ነው የእግዚአብሔር ወገን የሚሆኑት። አንድ ድረ ገጽ ላይ አሞጽ 9፥7 ተጠቅሶ ኢትዮጵያውያን ከእስራኤላውያን ይልቅ ለእግዚአብሔር ቅርብና የተመረጡ መሆናቸውን ጽፎ አይቼ እንዴት ከዐውዱ የወጣ አገላለጥ መሆኑ አስገረመኝ።

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ በዘመን ፍጻሜ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለሙ ሁሉ ስለሚሆነው ረሃብ፥ ቸነፈር፥ ጦርነት፥ ሁከት፥ ነውጥ የሚናገረው ሁሉ ከተጤነ አገሪቱን በራሳቸው ትንፋሽ እንደ ቂሪላ የሚፏት ሰባኪዎችና ዘማሪዎች በተጠነቀቁ ነበር። በቅርብ ያነበብኩት ስለ ኢትዮጵያ የተጻፈ አንድ የትንቢት መጽሐፍ ልክ ዱሮ በደርግ ጊዜ የወጣውን የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ ይመስላል። በአገሪቱ በየፊርጁ በየክልሉ ውስጥ የሚገነቡትን፥ የሚፈበረኩትን፥ የሚመረቱትን ሁሉ ነገሮች ያካተተ ነው። ራእየ ዮሐንስም እንደዚህ በዝርዝር አልተጻፈም። ያድርግ፤ እግዚአብሔር ከዚያም ብዙ እጥፍ ይጨምር። ግን ምኞትና ጸሎት አንድ ነገር ነው፤ በመለኮታዊ እውነት ላይ ያልተመሠረተ የተስፋ ዳቦ ግን ሌላ ነገር ነው። ዘማሪዎቻችንም እንደዚህ ያለ በነፋስ የተሠራ የተስፋ ዳቦ ነው ይህንን ሕዝብ እያስገመጡ ያሉት። ይህ ደግሞ አያጠግብም። ኢትዮጵያን ጎብኛት ማለትና መጸለይ አንድ ነገር ነው። ከእንግዲህ መከራና ችግር፥ እርዛትና ጦርነት አይሆንም፥ አይኖርም ማለት ግን በመጨረሻው ዘመን እነዚህ ነገሮች እንደሚኖሩ ከሚናገረው ቃል ጋር መጣላት ነው። የትኛው ነው ትክክል? ቃሉ ወይስ ዘማሪው? ቃሉ ነው ትክክል።

ዋጋዬ ከፍተኛ ነው ሊገዛኝ የሚችል ማነው?...

እርግጥ ቤዛው ክርስቶስ ስለሆነ የክርስቲያን ዋጋው የከበረ ነው። ዋጋ ሲባል ግን ክቡርነቱን እንጂ የገበያ ዋጋውን አይደለም። “ሊገዛኝ የሚችል ማነው?”ን ምን አመጣው? ራሱን ለሽያጭ የሚያቀርብ ነው የሚመስለው ይህ ዘማሪ። ምናልባት ሊገዛኝ የሚችል ማነው ሲል ሊያሸንፈኝ፥ ሊቆጣጠረኝ ማለቱ ይመስላል። አለመሆኑን ግን ይህ ቁጥር ያሳያል፥

ንሮ ንሮ ይህ ነው አይባልም
ተመኔ ተተምኖ አያልቅም

ዋጋው ከቀድሞ ይልቅ እየጨመረ፥ እየናረ የመጣ ገናም የሚጨምር ይመስላል። የክርስቶስ ደም ዋጋ ዝቅና ከፍ ይላል ማለት ነው? የዘማሪውስ ዋጋ እንደዚያው ነው ማለት ነው?

አትንካ ያልከውን አንዷት ቅጠል በላ...

አዳም መሆን አለበት ይህ። ደግሞ አዳም ነው እንዳይባል ቅጠል ነው የበላው። ሌላ እንዲህ የተባለ ሰው ስለሌለ አዳም ነው ብለን እንውሰድ። ቃሉ የሚለው፥ "ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው፤ እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ" ነው የሚለው ዘፍ.3። ከቶ ለምንድርነው ይህ ፍሬ ቅጠል የተባለው? ዘማሪው ይህን ቃል እያወቀ ጠምዝዞት ከሆነ ያሳዝናል። ሳያውቅ ዘምሮት ከሆነም ያሳዝናል፤ የማያውቀውን ነገር መዘመሩ የማያውቀውን ነገር ለሌሎች ማስተማሩ ነውና ያሳዝናል።

ታቦታችን የሱስ አልተማረከም...

የሚል ትንሽ ቆየት ያለ መዝሙር ሰምቼ ነበር። ጌታ ታቦት ነው? ደግሞስ የሚማረክ ነው? ነገሩ የብሉይ ኪዳኑ የእስራኤል ታቦት በፍልስጥኤማውያን ከመማረኩ ጋር ተያይቶ የተዘመረ ይመስላል። ግን እኮ ታቦት የአዲስ ኪዳን እምነት ዕቃ አይደለም። ይልቁንም ኢየሱስ ታቦት አይደለም።

አሁን አውቄአለሁ አንድ እውነት በራልኝ
አንድ ነው ታቦቴ ሌላ እኔ የለኝም

ከየት ነው እንዲህ ያለው ቃልና ትምህርት የተወሰደው? በተለይ 44 ወይም ቁጥራቸው የማይታወቅ የበዙ ታቦቶች ባሉበት ባገራችን "ታቦታችን የሱስ" ወይም "አንድ ነው ታቦቴ" ማለት በጣም አሻሚና አወዛጋቢ ሐረግ ነው። ለባለ ታቦቶች ደግሞ ኢየሱስ ከታቦታቱ አንዱ ነውና ያንን ማስመሰል ይሆናል። ኢየሱስን ከኢየሱስነቱ ቀንሰን ለሌሎች ማሳየት ተገቢ አይደለም።

የደም ላብ አላበው ብዙ ተሰቃየ... የሚል የቆየ ዝማሬ ነበረ።
ንጹህ የደም ላብ ያላበው ይህ ሁሉ ስቃይ ለኔ ነው...

በእውነት የደም ላብ አልቦታል ጌታን? ሉቃ.22፥44 እንደሚነግረን፥ "ወዙ በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ" ነው የሚለን። ወዙ እንደ ደም ነጠብጣብ። "እንደ" የሚለው ቃል አንድ ዓይነት መመሳሰልን የሚያሳይ ሲሆን የዚህ መመሳሰል አወራረዱ ነው። ኋላ መስቀሉ ላይ ኃጢአታችን የተሰረየበት ደም ፈስሶአል። ይህ እውነት ነው። ሲጸልይ ግን ደም እንዳላበው አልተጻፈም። የወንጌሉ ጸሐፊዎች ያልጻፉትን እኛ ለምን ጽፈን እንዘምራለን? አንዱ በስሕተት የዘመረበትንስ ሐረግ ለምን እንደገና እየደረስነው ቋሚ እናደርገዋለን?

ጳውሎስና ሲላስ... ጌታን ከዙፋኑ ከወንበሩ አስነሡት...

እውነት ጌታ ከዙፋኑና ከወንበሩ ተነሥቶ ነበር? ደግሞስ ወንበር ላይ ነበር የተቀመጠው? አንድ ሰባኪ፥ እነ ጳውሎስ በእስር ቤት ሲዘምሩ እግዚአብሔር በመዝሙራቸው ተመስጦ ሳያስብ እራሱን እያወዛወዘ፥ ወገቡን እየሰበቀ፥ እግሩን እያንቀሳቀሰ ነበር። እግሩን ሲያንቀሳቅስ ለካስ የእግሩ መነቃነቅ መሬትን እያናወጠ ነበር፤ ምድር የእግሩ መረገጫ አይደለች? መሬቱን ያናወጠው ያ ነው ብሎ ነበር የሰበከው። እንዲህ ያለው ስብከት የወለዳቸው መዝሙሮች ከሆኑ ስብከቶቹም መዝሙሮቹም ልብ ወለድ ናቸው። የሚዘመረውን ክፍል መመርመርና በመላ መዘመር የተለያዩ ነገሮች ናቸው።

ጌታም እኔን ዞሮ አየኝ በርቶሎሜዎስ ምን ፈለግህ አለኝ

ይህ በርጠሜዎስን መሆኑ ነው። ይቀራረባል ስማቸው ግን የትየለሌ የተራራቁ ሰዎች ናቸው። አንዱ የተፈወሰው [ዐይኖቹ የተከፈቱለት] ሰው በመንገድ ዳር የነበረው ለማኝ ነው፤ ሌላው ከ12ቱ አንዱ የሆነ ሐዋርያ ነው። ሲናገሩ መሳሳት ሊኖር ይችላል። ሲጽፉና ሲያርሙ፥ ሲለማመዱና ሲዘምሩና ሲያስቀርጹና ሲያሰራጩ በዚህ ሁሉ ውስጥ የሚያርም አልነበረም ማለት ነው? ወይስ በርጠሜዎስ በርተሎሜዎስ፥ ስልቻ ቀልቀሎ ምን ለየው ብለው ነው ያለፉት? የተለያዩ ሰዎች እኮ ናቸው እነዚህ ሁለት ሰዎች።

## የታሪክ ሻሞ፥ አጋኖ፥ የስሜት ዒላማና ማዕከለ ሰብዕና

የተደረጉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች የራስ አድርጎ መዘመር በጣም የተወደደ የዘማሪዎች ዘይቤ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሆነውን እንደሆነ መዘመር ሳይሆን፥ ወይም የራስን ታሪክ ከዚያ ታሪክ ጋር አዛምዶ መዘመር ሳይሆን ልክ ያ ታሪክ የራስ እንደሆነ ወይም ዘማሪው ዳዊትን ሆኖ ጎልያድን ሲዘርር፥ አብርሃምን ሆኖ ልጁን እንዲሰዋ ሲጠየቅ፥ 12 ዓመት ደም ሲፈሰው እንደኖረ፥ በርጠሜዎስን ሆኖ ታውሮ እንደኖረ፥ ዘሩባቤልን፥ ነህምያን፥ ኢያሱን፥ ጴጥሮስን፥ ሌሎቹንም ይሆናሉ። መምሰል አንድ ነገር ነው። እነዚያን ሰዎች ወክሎ መዘመርም አንድ ነገር ነው። እነርሱን መሆን ግን ሌላ ነው፤ በጣም ሌላ ነው።

12 ዓመት ደም ሲፈሰኝ ኖሬ...
12 ዓመት ከሰው ተለይቼ እጅግ ደም ሲፈሰኝ ሲፈሰኝ..

መዝሙሮቻችን የማጋነን ቃላትና ሐረጎች በጣም በጣም ይበዙባቸዋል። እርግጥ እግዚአብሔር መልካም አምላክና መልካም አድራጊ ነው። ግን "ለኔ ያረገው ከማንም ይበልጣል፤ ለኔ የተደረገው ከሰው ሁሉ የተለየ ነው፤ ለኔ የተደረገው ለማንም ያልተደረገ ነው፤ የእኔስ ልዩ ነው" ወዘተ ሲባል ማጋነን አይደለም? ማጋነናችን ይበልጥ ያስከብረው ይመስለን ይሆን? "የኔ ይበልጣል ከሁሉም" ሲባል እግዚአብሔር ያዳላል ማለት ነው? ወይስ ለሌላው ሁሉ የተደረገውን ማንኳሰስ ነው? ወይስ ለሌላው ሁሉ ሰው የተደረገውን ሁሉ ጨርሶ ጠንቅቆ አውቆ ከዚያ ጋር አነጻጽሮ ነው መብለጡን እየዘመረ ያለው ዘማሪው? ወይስ በመላ የኔ ሳይበልጥ አይቀርም ተብሎ ነው? "እኔ የራሴን ነው የዘመርኩት፤ ሌላው የራሱን ይዘምር" ከተባለ ታዲያ እኮ ስለራስና የራስን ለእግዚአብሔር መዘመርና ለጉባኤና ለገበያ መዘመር የተለያዩ መሆናቸውም መጤን አለበት። መልእክትና አድማጭ መገናዘብ አለባቸው እንጂ ስሜት ብቻ መዘመር የለበትም። ደግሞስ ራስን ብቻ ያማከለ መዝሙር እስከ መቼ ነው እየተዘመረ የሚኖረው? የዘመናችን መዝሙሮች እኔ፥ የኔ፥ የራሴ፥ የግሌ፥ ለኔ፥ በኔ ናቸው፤ ወይም እየሆኑ እየመጡ ያሉት። በራስ ዙሪያ እየተሽከረከሩ ናቸው [የሮሜ 11፥36 ሁሉ ከእርሱ፥ በእርሱና ለእርሱ እየጠፉ ነው]።

የስሜት ነገር ከተነሣ እጅግ ብዙዎቹ የዘመኑ መዝሙሮች ስሜትን የሚኮረኩሩ ብቻ ናቸው። ስሜት ደግሞ እንደሚታወቀው ጥልቀት የሌለው የሕይወታችን ክፍል ነው። ዘማሪ በስሜት

ተነሣስቶ የሚዘምር ከሆነ፥ የሚደርስ፥ የሚያዘጋጅ የሚያቀናብር ከሆነ የሚደርሰውና የሚነካውም የአድማጩን ስሜት ብቻ ነው። የመነጨው ከስሜት ከሆነ የሚነካውም ስሜትን ብቻ ነው። ከዚያ ጠልቆ አይሄድም። መዝሙር ግቡን መታ የሚባለው ስሜትን ሲኮረኩር ሳይሆን ጠልቆ መንፈስን ሲነካና ሲቀሰቅስ፥ ለአምልኮና ለውዳሴ አምላክ ሲያነሣሳ ነው። ከአእምሮ እንኳ ጠልቆ ዘልቆ ማለፍ አለበት። አእምሮ ከስሜት ይጠልቃል። ስሜትንማ ዘልሎ ነው ማለፍ ያለበት እንዲያውም። ብዙዎቹ ዘመነኞቹ መዝሙሮቻችን ግን ስሜት ላይ ቀሩ። እዚያ ላይ ተተክለው ቀሩ። ስለዚህ አንዴ ተሰምተው አንዴ ተደግመው ከዚያ በኋላ አይሠለሱም። የወረት ብቻ ሆነው ያልፋሉ። ልክ ገና ስጀምር፥ "ጠዋት ተነብበው ማታ እንደሚጣሉ የጎዳና ጋዜጦች እየሆኑ ናቸው" እንዳለው ወንድም አነጋገር ማለት ነው።

በቅርቡ አንድ መዝሙር በቤተ ክርስቲያናችን ዘመርንና ወድጄው ተረጎምኩት። Be Thou My Vision የሚባል መዝሙር ነው። ብዙ ጊዜ ዘምረነዋል። ከዚህ በፊት ተተርጉሞ ተዘምሮ ከሆነ አላውቅም። ከመተርጎሜ በፊት ታሪኩን ለማወቅ ስል ፈልጌ አገኘሁት። ሳነበው ገረመኝ። ከጥንታዊ የአየርላንድ (አይሪሽ) ቋንቋ ወደ እንግሊዝኛ ከተተረጎመ ወደ 100 ዓመቱ ነው፤ 103 ዓመቱ ነው፤ በፈረንጆች በ1905 ነው የተተረጎመው። የተተረጎመው ማለት ነው። በመጀመሪያ ማን እንደደረሰው በውል አይታወቅም። የተደረሰውና እየተዘመረ እየተላለፈ የኖረው ግን ከ8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ነው። ሺህ ዓመት አልፎታል ማለት ነው! እንዲያውም 1,200 ዓመት አልፎትም ተወድዶ የሚዘመር፥ አሁንም ትኩስ የሆነ መዝሙር ነው። በመቶዎች የሚቆጠሩ 300፥ 500 ዓመታት ያስቆጠሩ መዝሙሮችማ እጅግ ብዙ ናቸው። ዘመናዊ መዝሙሮች ጠፍተው ነው እነዚህ ተወዳጅ መዝሙሮች የሚዘመሩት? አይደለም። ብዙ አሉ፤ በእንግሊዝኛም [እንደሌላው ቋንቋ ሁሉ] ገለባ መዝሙሮች እልፍ ናቸው። ሆኖም ግን የዚያኑ ያህል እንደ አዕማድ ቆመው ከዘመናት ዘመናት የሚተላለፉ፥ አልፈው ዘመናትን የሚያሻግሩ ብዙ መወድሶችም አሉ።

ከመዝሙሮች ውስጥ ጠንካራና ዘመናትን ማለፍ ያለባቸው አስተምህሮዎች እየመነመኑና እየጠፉ እየመጡ ናቸው። ለምሳሌ፥ የመስቀሉ ጉዞና በአጠቃላይ መስቀል የሚባለው ቃል ለዘመነኞቹ ዘማሪዎች ነውር ሳይመስል አይቀርም። ድላችን፥ ሰላማችን፥ ደኅንነታችን፥ ዘላለማዊ ሕይወታችን የተመሠረቱትና የተጠናቀቁት እኮ መስቀሉና የመስቀሉ ገድል ላይ ነው። ደቀ መዝሙርነት እኮ መስቀል መሸከም ነው። የዛሬ መዝሙሮች ግን በአብዛኛው መስቀልን አያውቁትም። አምሬአለሁ፥ ተውቤአለሁ፥ ከብሬአለሁ፥ ኮርቻለሁ፥ ሠገነት ላይ ወጥቻለሁ፥ ከፍታ ላይ አምባ ላይ ወጥቻለሁ ናቸው። ልክ ሙሽራ ከቤት ሲወጣ የሚዘመረውን ይመስላል። እኛ የተጠራነው ለሥጋ ማማርና ውድ ልብስ ለብሶ ለመሽቀርቀር ሳይሆን ለእውነተኛ መዋብ ነው። ያም ክርስቶስን መምሰል ነው። እነዚህ ዘማሪዎች ክርስቶስን መስያለሁ እያሉ ከሆነ ድንቅ ነው፤ በጣም ድንቅ። ብቻ በዚህች ኑሮ፥ በዚህች ምድራዊ ኑሮ መስያለሁ ብለን ጨርሻለሁ ማለት አንችልም። ምድራዊ መቀማጠልና መሽቀርቀር ምርቃትና ተጨማሪ ነገር እንጂ ዋናው አለመሆኑን ቢረዱት ዋናውን ይዘምሩልን ነበር።

የሚያሳዝነው ነገር ግን ጥቂት ያልሆኑ ክርስቲያኖች ስነ መለኮታቸውን የሚያገኙት ከመጽሐፍ ቅዱሳቸው ሳይሆን ከመዝሙሮችና ከአዝማቾች ነው። በቃል ከሚያውቋቸው ግማሽ ግማሽ ጥቅሶች በቃል የሚያውቋቸው ሙሉ ሙሉ አዝማቾች እጅግ በጣም ይበዛሉ። መዝሙሮቹን ማወቃቸው መልካም ሆኖ ሳለ ቃሉን ያለማወቃቸው ግን በጣም ጥሩ ያልሆነ ነገር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብተው የእግዚአብሔርን ቃል በወጉ የተማሩ የመዝሙር አገልጋዮች እጅግ ጥቂት ናቸው። የግድ ትምህርት ቤት መግባት አይኖርባቸው ይሆናል። ዕድል ኖሮአቸው አለመማራቸው ግን ስንፍና ነው። መማርን መጥላትማ ይኼ ምስኪንነት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን የሚጠሉና የሚያጥላሉ ሰባኪዎችና ዘማሪዎችን አውቃለሁ። ቢማሩ ለሕይወትም ለአገልግሎትም ውበት ነው። አገልግሎት ከሆነ አገልግሎቱ በነሲብና በመላ ብቻ መደረግ የለበትም። አንዳንድ ዘማሪዎችማ ከአንድ አገልግሎት ወደ ሌላ እየተካለቡ እየተነዱ ስለሚኖሩ ረጋ ብለው መጽሐፍ ቅዱሳቸውን የሚያነብቡበት ጊዜ ማግኘታቸውም ያጠራጥራል። ከሰባኪ ብቻ እየሰሙ ከዛሬ ነገ የሚደርሱ ይመስላሉ። ለዚህም ሳይሆን አይቀርም የተግለበለቡ መዝሙሮች አገሩን የሞሉት።

የኩራት መዝሙሮችስ? የኩራት መዝሙሮች ልበላቸው እነዚህ አኮራኝ፥ ኩራት ኩራት አለኝ የሚሉ መዝሙሮችን ማለቴ ነው።

ትምክህቴ ኩራቴ...
አኮራኝ ጌታዬ...
ኩራት ኩራት አለኝ ብኮራስ ምናለ...

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኩራት አንዴም በመልካም አልተጻፈም፤ አንዴም። ጥቂት ጥቅሶችን እንይ፥ [ይህ አንድን ጭብጥ ከቃሉ አንጻር እንድናይ ምሳሌም የሚሆነን ነው]

- አትታበዩ በኩራትም አትናገሩ... ከአፋችሁም የኩራት ነገር አይውጣ። 1ሳሙ.2፥4 (ሐና ናት የተናገረችው)
- እኔ ኩራትህንና የልብህን ክፋት አውቃለሁ። 1ሳሙ.17፥29 (ኤልያብ ለዳዊት)
- ሕዝቅያስ ግን እንደተቀበለው ቸርነት መጠን አላደረገም፤ ልቡም ኮራ... ሕዝቅያስም ከኢየሩሳሌም ሰዎች ጋር ስለ ልቡ ኩራት ሰውነቱን አዋረደ። 2ዜና 32፥25-26
- የባሪያዎችህን ቃል አትርሳ፤ የጠላቶችህ ኩራት ሁልጊዜ ወደ አንተ ይወጣል። መዝ.74፥23 (አሳፍ የተናገረው ቃል)
- ለሰነፍ የኩራት አነጋገር አይገባውም። ምሳ.17፥7
- ትዕቢት ጥፋትን ኩሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል። ምሳ. 18፥20
- ኩሩና ተጓዳጅ ሰው ፌዘኛ ይባላል፤ እርሱም በትዕቢት ቁጣ ያደርጋል። ምሳ.21፥24
- የሰዎችም ኩራት ትወድቃለች። ኢሳ.2፥11
- የትዕቢተኞችንም ኩራት እሰብራለሁ፤ የጨካኞቹንም ኩራት አዋርዳለሁ። ኢሳ.13፤11
- ድፍረትህና የልብህ ኩራት አታልለውሃል። ኤር.49፥16 (ስለ አሞን)
- ልቡ ግን በታበየ ጊዜ፥ በኩራትም ያደርግ ዘንድ መንፈሱ በጠነከረ ጊዜ ከመንግሥቱ ዙፋን ተዋረደ። ዳን.5፥20 (ለብልጣሶር ስለ ናቡከደነፆር)
- እነሆ ነፍሱ ኮርታለች፥ በውስጡም ቅን አይደለችም፤ ጻድቅ ግን በእምነቱ በሕይወት ይኖራል። ...እርሱ አታላይና ኩሩ ሰው ነው። ዕን.2፥4-5 (ስለ ከለዳውያን)

ኩራት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዴም በመልካም አልተጠቀሰም። ሁሌም በአሉታዊና በአፍራሽ መልኩ ነው የቀረበው። ኩራት ገንቢ መልክ የለውም። መዝገበ ቃላትም ኩራትን መታበይ፥ መቆነን፥ መኳደድ ይለዋል። ኩራት ከእብሪት ትንሽ የሚያንስ ባህርይ ነው። ኩራት ትእቢት ነው። እንግዲህ ኩራት ኩራት አለኝ ሲብል መታበይ አማረኝ ማለት ነው? አኮራኝ

ሲባልስ አስታበየኝ ማለት ነው? ጌታ ያስታብያል? መመካት አንድ ነገር ነው፤ መኩራት ግን ፈጽሞ ሌላ ነገር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር እንድንመካ ወይም እንድንታመን ያስተምረናል። እንድንኮራ ግን አይነግረንም። በእግዚአብሔርም እንኳ እንድንኮራ አያደፋፍረንም። በእግዚአብሔርም እንኳ። ኩራት የትኅትና ተቃራኒ ነው። ኩራትና በትኅትና መመላለስ አብረው አይገኙም። በምንም መልክ ኩራትን ክርስትና አስነሥተን መንፈሳዊ ልናደርገው አንችልም። እንግዲህ አንድን ቃል በተለምዶ ትርጉሙ ወስደን መዘመር ይቻል ይሆናል። ግን ያ የተለምዶ ትርጉምና መጽሐፍ ቅዱስ ያንን ቃል የሚጠቀምበት አገባብ የማይስማሙ ከሆነ ልማዳዊውን ጥለን መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መውሰድ አለብን። ምክንያቱም ይህ መንፈሳዊ መዝሙር እንጂ ልማዳዊ ዘፈን አይደለም።

*የሚያኮራ ጌታ የሚያመጻድቅ...*

ኩራትን ተመልክተናል። ማመጻደቅስ? ጌታ ያመጻድቃል? መመጻደቅ ወይም ማመጻደቅ ምንድርነው? ማመጻደቅ ሌላን ሰው ማኩራራት ነው። መመጻደቅ ደግሞ በእሻል ባይነት መኩራራትና መንጠባረር ነው። ጌታ ያመጻድቃል?

የበቀልና የእርግማን መዝሙሮችስ? እርግጥ በብሉይ ኪዳን እንዲህ ያሉ መዝሙሮች ተዘምረዋል። ጠላቶቻቸው በባሕር ሲከደኑ ዘምረዋል። በብሉይ ኪዳን መዝሙሮች ውስጥም የጠላትን ውድመት ሲለምኑ እናያለን። ለምሳሌ፥ መዝ.137። ግን በአዲስ ኪዳን ስለ ጠላታችን እርግማንን እንድንዘምር ሳይሆን የሚጠሉንን እንድንወድ፥ የሚረግሙንን እንድንመርቅ፥ ስለሚያሳድዱን እንድንጸልይ ነው የተማርነው።

*የሚነሣብህ ወገቡ ይወጋ...*

ይህ እርግማን ነው። ተራጋሚ ማን አደረገን? በቀል እኮ የኛ አይደለም።

*የበቀል ጊዜ ነው...*

ይህ መዝሙር ደግሞ ጊዜው የበቀል መሆኑን ያወሳል።

*አሜን ይጎስቁሉ አሜን ይጎስቁሉ...*

በጠላቶቻችን መጎሳቆል የምንደሰት ከሆንንና የክርስቶስ ልብ አለን ካልን እነዚህ ሁለት ነገሮች አብረው አይሄዱም። ጌታ እስከመጨረሻ ድረስ ጠላቶቹን እየወደደ ነው በመስቀል ላይ የሞተው። ያስተማረንም ጠላቶቻችንን እንድንወድ ነው።

*አሳዳጆችን ሰጠመ እያየ ዐይናችን...*
*ጌታ ሆይ አንድ ሰው ስጠን... ቢረግምም የሚሆንለት...*

ሰው ስጠን ማለት መጥፎ አይደለም፤ ሰው ጠፋ፥ ሰው ባገሩ የለም ማለት ግን ያሉንን ሰዎች ማጥላላት መሆኑም መዘንጋት የለበትም። እሺ ይስጠን ሰው፤ ይስጠን ብለን እንለምን፤ ግን የሚራገም ሰው ለምን ይስጠን? እኛ እኮ ልንረግምም ልናስረግምም አልተጠራንም።

*ባመቺ ቦታ ላይ ጠላቱን አግኝቶ፤ በመልካሙ መንገድ በፍቅር ሸኝቶ፤*

በሰላም የሚሰድ ከሰው ልጆች ማነው? ዳዊት በዘመኑ ይህን አደረገው።
ጠላቶቼን እንድወድጌታ አስተማረኝ፤ በመስቀል ተቸንክሮ ፍቅሩን ገለጠልኝ፤ መልካም ፍቅር! አ መልካም ፍቅር።

የት ገቡ እንደዚህ ያሉት መዝሙሮች? የት ሄዱና በምን ተለወጡ እነዚህን የመሳሰሉት መዝሙሮች?

## የባከነ ጊዜ

አንዳንድ መዝሙሮች ካሴት ለመሙላት ብቻ ሲባል የተሠሩ ይመስላል። አንድ ካሴት 60 ደቂቃ ከያዘ፥ ከዚያ ውስጥ ስንቱ ነው መባከን ያለበት? እንዲያው በመዝሙርና በመዝሙር መሐል 10 ሰከንድ ቢኖርና በካሴቱ 10 መዝሙሮች ቢኖሩ ጠቅላላው [የሚባክን ጊዜ] ከ10 ደቂቃ ያነሰ ነው ማለት ነው። በእስፖርት ግጥሚያ የባከነ ጊዜ ተብሎ ታስቦ፥ ተሰልቶ ይጨመራል። እዚህ እንደዚያ ማድረግ አይቻልም። ስለዚህ መዝሙሮች ተሰልተው መሠራት የለባቸውም? አንድ ካሴት ላይ ኢየሱስ የሚል ሌላ ምንም ቃል የሌለበት 4 ደቂቃ ያህል የተዘመረ መዝሙር አለ። መዝሙር ከተባለ። ምንም ሌላ ቃል የለም። ምንም ሌላ መልእክት የለም። በሌላ ካሴት ደግሞ፥

ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ኃያል ኃያል እግዚአብሔር

ለ10 ሙሉ ደቂቃ ተዘምሮአል። በ11ኛዋ ደቂቃ ላይ ብቻ፥ *ቅድስና ለእግዚአብሔር በዙፋኑ ላለው።* በጠቅላላ ስድስት ወይም ሰባት ቃላት ብቻ ናቸው 11 ደቂቃ ሙሉ የተዘመሩት። የሚያንጸው የቱ ነው? ዜማው ወይስ መልእክቱና ቃሉ? ቦታስ ሊሰጠው የተገባ የቱ ነው? ወይም በዚያ ስፍራ ንባብ ቢያነብቡ ይሻል ነበር።

## ቪሲዲዎች

በመጨረሻ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደ አሸን እየፈሉ ስለመጡት VCDዎች ጥቂት ልበል። [VCDዎችን በጽሑፍ ወይም በድምጽ ብቻ ማሔስ ሙሉ ባይሆንም] የብዙዎቹ የጥራት ጉዳይ አይነካ። ይህን የአገራችን ያልዳበረ ቴክኖሎጂ ነው ልንል እንችል ይሆናል። ከመዝሙሮቹ ወይም ከዘማሪዎቹ ግለ ታሪክ ጋር እንዲሄድ ተብሎ የሚሠራው ድራማና ፊልም ድራማም ፊልምም ሳይሆን እንዲያው ስንደዶው የተመሳቀለ ጅምር ስፌት ነገር ይመስላል። የዓለም ዘፋኞች እንደሚያደርጉት ለመሆን የተደረገ ትግል ነው። በምዕራቡም ዓለም ይህንን የሚያደርጉት ዓለማውያን ዘፋኞች እንጂ ክርስቲያን ዘማሪዎች አይደሉም። ይህ እንዳለ ከዓለማውያን ዘፋኞች የተገለበጠ ዘይቤ ነው። በምዕራቡ ዓለም ዘማሪዎች የሚያስቀርጹአቸው ቪድዮዎች አሉ። እነዚህ ከመድረክ ላይ ከጉባኤ አምልኮ ጋር ከእውነተኛ አምልኮ የተቀዳ ነው እንጂ ገበያ ላይ ያወጡአቸውን መዝሙሮች ከአዲስ ውዝዋዜ ጋር ለውሰው እንደገና ለገበያ አያቀርቡትም። ሆኖም ይህ በዓለማውያን ዘፋኞች ዘንድ በጣም የተለመደና የተወደደ ነገር ነው።

ዱሮስ ሌላ ምን መዝናኛ አላቸው? የኛዎቹም ይህንን ነው እየቀዱ ያሉት። አቤት! እንዴት ስንት የተወደዱ መዝሙሮቻቸውን እጅ እጅ አሰኙአቸው።

ለባለ4 ደቂቃ መዝሙር 11 ልብስን መቀያየርን አሁን ምን ይሉታል? አንዳንዶቹማ የልብሳቸውን ብዛትና ዓይነትና ፋሽን መከተላቸውን እያሳዩ የሚሽቀረቀሩ ብቻ ናቸው። [አልጋቸው ላይ ሲንጋለሉ ሲገላበጡ የተነሣው ቀርቶ] መንበርከኩ፥ መደፋቱ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያንብቡ መምሰሉ፥ እንባው ሁሉ ሰው ሠራሽ ነው። እነዚህ ከ VCDው ሽያጭ ከሚያገኙት ሌላ በአደባባይ በሰው ታይተው ዋጋቸውን ተቀብለዋል ለማለት ያስደፍራል። ከዚህ የሚገኘው መልእክት ምን ይሆን? የዓለምን ቴክኖሎጂ አሠር ወደ እግዚአብሔር ጉባኤም አምጥተን የግድ መተግበር ወይም መቸርቸር አለብን?

ከዚህ በላይ ያሳዘነኝ ግን በጉባኤ አምልኮ ውስጥ የመዝሙር ሲዲያቸውን ከፍተው ሲዲው ወይም ቴፑ እየዘመረ lip sync ወይም lip synchronization በሚሉት ስልት አፋቸውን እያነቃነቁ ወይም በሞተ ማይክሮፎን ትንሽ ድምጽ የዘመሩ እየመሰሉ ጉባኤውን እንደ ገበቴ ውኃ ወዲያ ወዲህ ሲያደርጉት ማየት ነው። ይህንን ጉድ ደግሞ አስቀድተውና በቪሲዲ አስገልብጠውት ተመልሶ ይሸጣል። ጉባኤውስ በቅንነት ያመልካል። ግን እነዚህ ዘማሪዎች በዚያ መድረክ ላይ ይህንን ሲያደርጉ እግዚአብሔርን አይፈሩም? ሰውንስ አያፍሩም? እያመለኩ ይሆን ወይስ [ኋላ የሚሠራውን ቪሲዲ እያሰቡ] ድራማ እየሠሩ? በምዕራቡ ዓለም በጉባኤ ወይም በተመካች አድማጭ ፊት lip synchronize ማድረግ በአጭበርባሪነት የሚያስከስስ ጉዳይ ነው። እዚህ ባለሁበት አገር በአገሪቱ በጠቅላላውና በዓለምም የታወቀች አንዲት የፈረንሳይኛና የእንግሊዝኛ ዘፈን አቀንቃኝ እንዲህ አድርጋለች ተብላ ከሁለት ዓመት በፊት ትልቅ ቅሌት ያስከተለ ክስ ተከፍቶባት ነበር። አታሞ መቺዋ ነበር ያጋለጣት። እነዚህ የዓለም ሰዎች ናቸውና እንዲህ ቢያደርጉ አያስገርምም። እንዲያም ሆኖ ግን ለተመልካች ወይም ለአድማጭ ስሜት ኅሊናቸውን ሲያስገዙ ይታያል። ዓለማውያንም። እስከሠሩ ድረስ አድማጭና ተመልካችን በማክበርና ላለማታለል ራሳቸውን በተጠያቂነት አጥር ውስጥ እያቆዩ ነው የሚገኙት። ክርስቲያኖች ግን፥ ያውም በአምልኮ መድረክና ለገበያ በሚውል እቃ የተለየ መለኪያና መስፈርት ሊኖረን ለምን አይገባም?

## መደምደሚያ

ይህን መጣጥፍ መጀመሪያ ሳዘጋጅ ለመዘምራን አጫጭር ስልጠናዎች ከቡድን አሰልጣኞች አንድ ክፍል ለመውሰድ ብቻ ነው የተዘጋጀው። አንዳንዴ የራሳቸውን የመዝሙር ደብተር በመውሰድ የራሳቸውን መዝሙሮችና ድርሰቶች ነው እየተቸንና እያሔስን የምንወያየው። ሌላ ጊዜ ደግሞ የተዘመሩ መዝሙሮችን እያወሳን ነው የምንመለከተው። ከላይ የተተቹት መዝሙሮች ይዘቶችና ቃላት ሳደምጥ ያገኘኋቸው ናቸው እንጂ በማንም ዘማሪ ላይ በተለየ የተነጣጠሩ አለመሆናቸውን ላስገነዝብ እወዳለሁ። ናሙናዎቹን የወሰድኩት በእጄ ሊገኙ ከቻሉት ጥቂት የመዝሙር ካሴቶችና ሲዲዎች ነው። እኔ ባለሁበት አካባቢ መዝሙር እንደልብ ማግኘትም ቀላል አይደለም። እንግዲህ እንደልብ ከማይገኙቱ ከእነዚህ መካከል የተለቃቀሙ ናሙናዎች ብቻ ናቸው።

ብዙዎች መዝሙሮቻችን ውኃ የማያነሡ እየሆኑ ከመጡ ቆየ። ይህን ሳዘጋጅ ዘማሪዎቻችን ቆም ብለው እንዲያስተውሉ፥ ቃሉን እንዲያጠኑ፥ የሚደርሱትን እንዲያጤኑት በትንሹ ለማሳሰብና ለማስታወስ ነው። ይህ ሲዲ ለትምህርት እንጂ ለሽያጭ የተዘጋጀ አይደለም። ባለቤትነቱን የራስ ሳያደርጉ ማራባትም ሆነ ማደል፥ ካስፈለገም ወደ ጽሑፍ ቀይሮ ማተምና ማደል ይፈቀዳል። መጣጥፉን በጽሑፍ ለማግኘት የምትፈልጉ በሲዲው ላይ ባለው የኢሜል አድራሻ ብትጠይቁ በፒዲኤፍ ሰነድ የተዘጋጀ [አባሪ] በኢሜል ልልክላችሁ እችላለሁ።

(ዘላለም መንግሥቱ)

# ይድረስ ለዘማሪዎች

ቅጽ ሁለት

## ክፍል አንድ፥ ሕያሴ መዝሙራት

### በቅድሚያ

በመጀመሪያ ስለ መዝሙርና ስለ ዘማሪዎች አገልግሎት እግዚአብሔርን ላመሰግን እወዳለሁ። ስለ ቅን ዘማሪዎቻችንም ጌታን አመሰግናለሁ። ወንጌልን የሰማንባቸውን፥ የመስቀሉን ገድልና ፍቅር አትኩረን ያየንባቸውን፥ የሕይወትን ውጣ ውረድ የተማርንባቸውን፥ ተስፋችንንና መጪውን ዘላለማዊ ደስታችንን የተገነዘብንባቸውን መዝሙሮቻቸውን ብቻ ሳይሆን ሕይወታቸውንም ያካፈሉንን ያለፉትንም ያሉትንም ዘማሪዎች ሳስብ ጌታን ከልቤ አመሰግናለሁ። እነዚህ አገልጋዮች መንፈሳዊ ሕይወታችንን ያሸበረቁልንና ክርስቲያናዊ ጉዞአችንን የሚጥም ያደረጉልን ሰዎች ናቸው። አንዳንዶቹ በነፍሳቸው ተወራርደው አገልግለዋል። አንዳንዶቹ እንዲያው የተቀበሉትን በነጻ እየሰጡ አገልግለዋል። አንዳንዶቹ መከራን እየተቀበሉ ሕይወታቸውን ምስክር አድርገዋል። ብዙዎቹ ዘማሪዎች ልክ እንደ ቀስት ወደ ውስጥ ገብተው ውጡ ቢባሉ እንቢ የሚሉ ዘላለማዊ መዝሙሮች ሰጥተውናል። እነዚህ ቅርሶቻቸው ናቸው። ስለነዚህ ጌታን ባናመሰግን ጥፋተኞች ነን።

ሌላው እግዚአብሔርን ላመሰግን የምፈልገው ስላለፈው CDና ስለ ስርጭቱም ነው። በኢሜይልም በቃልም ስለደረሱኝ በጣም ብዙ የማበረታቻ አስተያየቶችም አድማጮችና አንባቢዎችን አመሰግናለሁ። ስላለፈው ለመናገር ብቻ ሳይሆን ለማመስገን ነው። ያለፈውም ይህም የCD መጣጥፍ በመዝሙሮች ይዘት ላይ ያተኮረ ነው። መዝሙር ስልም ክርስቲያናዊ የመዝሙር አገልግሎትን ሲሆን ዘማሪ ስልም እነዚህን ዝማሬዎች የሚያቀርቡ አገልጋዮችን ማለቴ ነው። ጥቂት መዝሙሮችን ስላሔስኩና አጠቃላዩን የመዝሙር አካሄድ አዝማሚያ ስለተቸሁ በዘመነኞች መዝሙሮች ላይ ለጦርነት ክተት ሠራዊት እንዳወጅኩ ወይም በዘማሪዎች ላይ ጡጫ እንደቃጣሁ የመሰላቸው አሉ። አይደለም። መዝሙር እወዳለሁ፤ መዝሙር በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ስፍራ አለው። መዝሙር ሳልሰማ ወይም ሳልዘምር ወይም ሳላንጎራጉር ውዬ አላውቅም። በመዘምራን ቡድን ውስጥ ሆኜ ያልዘመርኩባቸው ወይም የሙዚቃ መሣሪያ

ያልተጫወትኩባቸው ወይም አምልኮ ያልመራሁባቸው እሁዶች በጣም ጥቂት ናቸው። መዝሙርም መዘመርም እወዳለሁ። ባለፈው ካሔስኳቸው መዝሙሮች እንኳ አንዳንዶቹ ልነካቸው ያልፈለኳቸው ውድ መዝሙሮች አሉባቸው፤ በዚህኛውም እንዲሁ። መዝሙር በሕይወቴ ትልቅ ስፍራ ስላለው ነው ስሰማ እንዲያው ለመስማት ብቻ የማልሰማው። ለዚህም ነው ለመጠየቅና ለማሔስም የጀመርኩት። መዝሙር በጣም የምወደው አገልግሎት ነውና ለጥራቱ ከሚቆሙት ሰዎች አንዱ መሆን እፈልጋለሁ።

ዘማሪዎቻችን ሊመሰገኑ የተገባቸው መሆኑ እውነት ነው። ሆኖም ያለፈውም ሆነ የዚህ ዝግጅት ግብ ግን ማመስገን ሳይሆን ማሔስ በመሆኑ ሥራው በአንዱ ገጽታ ብቻ እንዲያተኩር አድርጎታል። በመዝሙር መስክ ባለፉት ዘመናት አስመስጋኝ አገልግሎት ታይቶአል፤ ጥረቱም ውጤቱም አመርቂ ነው። የዚህ አገልግሎት ጥራት ተጠብቆ እንዲዘልቅ ደግሞ ጎሽ ከማለት ጋር አብሮ መስፈሪያዎችና የፍተሻ ኬላዎችም መኖር አለባቸው። እኔ ላደርግ የሞከርኩት ወይም እያደረግሁ ያለሁት ይህንን ነው።

በዚህኛውና አሁን በቀረበውና ባለፈው መጣጥፍ መካከል በኢትዮጵያ በጥቅምት 2001 በዚህ አገልግሎት ላይ የተደረገ 'ወርክሾፕ' ነበረ። በዚያ እኔም ከሐተታ አቅራቢዎች አንዱ ነበርኩና እዚያ ያቀረብኳቸውን ጥቂት ነጥቦች በዚህኛው ውስጥ ላካትት እሞክራለሁ።

## ላለፈው መጣጥፍ ምላሽ

ወዳለፈው CD በመጠኑ በመመለስ ጥቂት ቃል ልናገር። በተመሳሳይ ይዘት የቀረቡ ሊኖሩ ቢችሉም ይህኛው በአቀራረቡ ስልት የመጀመሪያው ነው። ለማንበብ የማግኘቱ ዕድል የጠበበ ይሁን እንጂ በጽሑፍ ብዙ እንደተባለ እገምታለሁ። በጥቂት መጽሔቶች በጽሑፍ የቀረቡ ትችቶችን አንብቤአለሁ። ስለ መጣጥፉና ስለ CDው በጥቂት የቃልና የኢሜይል አስተያየቶች ውስጥ አሉታዊ መልእክቶች አግኝቻለሁ። የስሚ ስሚ ያገኘኋቸውን በቀጥታ ስላልተነገሩኝና ከእጅ ወደ እጅ ሲተላለፉ ቃናቸው ስለሚቀየር ልለፋቸውና የተቀሩት በርካታ አስተያየቶች በመላው እሰይ አበጀህ የሚሉ የምስጋና ናቸው። አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ እንዲያውም የቤተ ክርስቲያኒቱ መዘምራን ካሴት የማስቀረጽ ቀጠሮ ይዘው ሳሉ ይህን በማግኘታቸው ቀረጻው ተላልፎ ከዚያ በፊት መዝሙሮቹን በሙሉ በመከለስና በመፈተሽ ላይ መሆናቸውን ከምስጋና ጋር ጽፎልኛል። አልሆነም እንጂ ከምስጋናው ይበልጥ ነቀፌታውን ነበር ብዙ የጠበቅኩት። የጠበቅኩትም ባለአድራሻዎቹ ዘማሪዎቹ ስለሆኑና ወቀሳ ደግሞ በባህላችን ከቶም ያልተለመደና የማይወደድ ስለሆነ ነው። አሉታዊ ያልኳቸውን አስተያየቶች በሦስት ፈርጅ ቋንቋ፥ አቀራረብና ይዘት ብዬ ሳቀርባቸው የሚከተሉትን የያዙ ናቸው፤

- ቋንቋው፥ ቋንቋው ጠንካራ ነው። አንዳንድ ቦታም ተራ ነው። ዲፕሎማሲ ያንሰዋል። ለምሳሌ፥ እንደ ፌንጣ እየተፈናጠሩ፥ ሳር ሳር የሚል መዝሙር፥ መደዴ፥ ወዘተ ስድብ ይመስላሉ።
- አቀራረቡ፥ አቀራረቡ ወራሪና አስበርጋጊ ነው። ገና ሲጀምር በቡጢ መደባብደቢያ መድረክ እና በቡጢ ነው የሚጀምረው። የቀደሙትን አገልጋዮችና የአሁኖቹንም በማመስገንና ጠንካራ ጎናቸውን በማሞገስ አልጀመረም። የዮሐንስ ራእይ እንኳ የሚነቅፍባቸውን ነገር ሲናገር የሚመሰገኑበትን ዝርዝር በማስቀደም ነው የጀመረው። ያንተ ግን ጀምሮ እስኪጨርስ የወቀሳ ናዳ ነው።
- ይዘቱ፥ ይዘቱ ስሕተት መጠቆም ብቻ ነው። ማስተማር ላይ ሳይሆን ግድፈት ማሳየት ብቻ ነው የሚሉ ናቸው።

አስተያየቶቹን ስፈርጃቸው ነው ሦስት ቦታ የወደቁት እንጂ በቁጥር ሦስት ብቻ አይደሉም። ሦስቱም ፈርጆች ግን ትልልቅና በጣም ጥሩ አሳቦች የያዙ ናቸው። ስለነዚህ ሦስት ነጥቦች ይህን ማለት እፈልጋለሁ።

<u>አቀራረቡ፤</u> አቀራረቡ አስበርጋጊ ሊመስል ወይም ሊሆን ይችላል። ይህ የሆነው በመስኩ ብዙ ልምድ ስለሌለንና መተቸት ኃጢአት ስለሚመስለን ነው። አንድ ወንድም በቃል፥ ሌላ ወንድም ደግሞ በመጽሔት ላይ በተጻፈ መጣጥፍ፥ 'ስንተች ወይም ስንወቅስ ጌታን መምሰል አለብን፤ በተለይም በራእይ 2 እና 3 የተናገረውን' ብለዋል። እርግጥ በራእይ መጽሐፍ ከ7ቱ አብያተ ክርስቲያናት ሁለቱ መልካም ብቻ፥ ሦስቱ መልካምና መጥፎ፥ እና አንዱ ወይም ሁለቱ መጥፎ ብቻ የተጻፈባቸው ናቸው። [ሰምርኔስና ፊላደልፍያ - ምስጋና / ሰርዴስና ሎዶቅያ - ወቀሳ / ኤፌሶን፥ ጴርጋሞን፥ ትያጥሮን - ሁለቱም] የሚመሰገን ነገር ለሌላት ቤተ ክርስቲያን ወቀሳውን ለማለዘብ ተብሎ የሙገሳ ቃል አልተፈለገላትም። ይህ እንግዲህ ራእይ 2 እና 3ን ብቻ ካየን ነው። የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ከአንዷ ወደ ሌላዋ እንደሚለያይ፥ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥም ብዙ ዓይነት ሰዎች መኖራቸውንና አንክድም። በነገራችን ላይ፥ የራእይ መልእክት በተቀባዩ ሰው (ነጠላ ሰው - መልአክ ይለዋል፥ መሪ፥ መጋቢ) ላይ ያነጣጠረ ነው። ለዚህም ነው 'እናንተ' ሳይሆን 'አንተ' እያለ የሚናገረው። አንዲትን ቤተ ክርስቲያን ነጥለን ብንወስድ ጥሩም መጥፎም፥ ፍሬም ገለባም እንደሚወሳ ሁሉ አንድ ዘማሪ ወይም ዘማሪት ላይ ብናተኩር ይህንን ማድረግ ግዴታ ነው። ማለት፥ በአንድ ዘማሪ ሥራ ላይ ብናተኩር እንደ ገለባው ሁሉ ፍሬውንም ማውሳት ተገቢ ነው። አስተያየቱ ቀና ቢሆንም የኔ የመዝሙሮች ሒስ አቀራረብና የራእይ መጽሐፍ ደብዳቤዎች ለየቅል ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ በሌሎች ቦታዎች ሳያመሰግን የወቀሰባቸውን ጊዜዎችም አንዘንጋ።

የተመሰገነ ሕይወትና አገልግሎት ያላቸው ዘማሪዎች መኖራቸውና ምስጋናም መገባቱ እውነት ነው። በእውነቱ እንዲህ ያሉቱ ዘማሪዎች ምስጋናና ውዳሴ ለማካበት የሚስገበገቡ ባይመስለኝም አስመስጋኝ አገልግሎት መኖሩን ሁላችንም እናውቃለን፤ እኔም አልክድም። በአንድ ዘማሪ ብቻ

ላይ አትኩሬ ኖሮ ቢሆን ይህን አደርግ ነበር። የኔ ጽሑፍ ግን ሒስ ወይም ሕያሴ ነው፤ ትችት ነው። ደግሞም በአንድ ዘማሪ ላይ ወይም በመዝሙሮቹ ላይ የተሠራ ሳይሆን በተለያዩ ዘማሪዎች የተሳሳቱና የሚያሳስቱ አንዳንድ ስንኞች ወይም አካሄዶች ላይ ያተኮረና የተሰነዘረ ፍተሻና ማበራየት ነው። ደግሞም አሳሳቢ አዝማሚያና አቅጣጫዎችን ጠቋሚ ነው። ስለነዚህ ነጥቦች በኋላ የማወሳው ይኖረኛል።

<u>ቋንቋው፤</u> ቋንቋው መጠንከሩን ወይም መለስለሱን ከጸሐፊው ይልቅ አንባቢ ነው የሚያውቀው። እኔ ለማጠንከርም ለማለስለስም ሳልሞክር በምናገርበት ቋንቋ ነው የጻፍኩት። ልዩነቱና ጥንቃቄ ያደረግኩበት ነገር ቢኖር እንደመጣልኝ ወዲያው የተናገርኩት ሳይሆን ያሰብኩበትና የጻፍኩት ወይም የተጻፈውን መጣጥፍ ያነበብኩት መሆኑ ነው። ገላጭ ሐረጎችንና ምሳሌዎችን መጠቀም ያልተለመደና አዲስ ነገር አይደለም። ስድብ ግን ዓላማዬም ግቤም አልነበረም፤ አሁንም ወደፊትም አይደለም። የስድብ ቃል አልተናገርኩም። መጽሐፍ ቅዱስ የስድብ ቃል ከአፋችን እንዳይወጣ ያስጠነቅቀናል። መደዴ ስድብ አይደለም፤ መደዳው፥ ተርታው፥ ተራው፥ ሰፊው ማለት ነው። ቃላት በዘመናት ውስጥ ትርጉማቸው ሊቀየጥ ወይም ሊቀየር ይችላልና ዘንድሮ ስድብ ከሆነ በዚያ መልኩ አለመጠቀሜን ልገልጥ እወዳለሁ። መደዴን በሁለት ቦታዎች ነው የተጠቀምኩት፤ እነዚያም ተርታ የመዝሙር ቃላትንና ሰፊውን አድማጭ ለመግለጥ ነው።

<u>ይዘቱ፤</u> ይዘቱ ማስተማር ሳይሆን ስሕተት መጠቆም እና ግድፈት ማሳየት ብቻ ነው የተባለው ከፊል እውነት ከፊል ውሸት ነው። ስሕተትን መጠቆሙና ግድፈትን ማሳየቱ እውነት ሲሆን “ብቻ” ግን አይደለም። የተዘነጋው ከፊል ማስተማር የሚለው አሳብ ነው። ስሕተትን ማሳወቅ እኮ ማስተማር ነው፤ ስሕተትን ማወቅም መማር ነው። መሳሳትና መሳሳትን መረዳት መማርና የማወቅ ሂደት መሆናቸውን ትምህርት ቤት ወረቀቶችና ፈተናዎቻችን ሲታረሙ ያገኘናቸው ‘ኤክሶች’ ይመሰክሩ። እርግጥ ነው፤ ለኤክሶቹ ትኩረት የማይሰጡት ተማሪዎች አይማሩባቸውም። የሚሰጡቱ ግን በድንቅ ይማሩባቸዋል። ይልቅስ ስሕተትን መጠቆምና ግድፈትን ማሳየት የማስተማር ሂደት መሆኑን አለማወቅ በራሱ ስሕተት ነው። አስተማሪዎቻችን የተሳሳትናቸውን ነገሮች ሳይነግሩን ወይም የኤክስ ምልክት ሳያደርጉ ቢተዉ ወይም የማድረጉ አሳብ ባይኖራቸውና ባያርሙን ኖሮ፥ እኛም ስህተታችንን መርምረን፥ ‘ለካ እንዲህ ማድረግ ወይም ማለት ነበረብኝ’ ባንል ኖሮ ተማርን ማለት ይቻላል? አይቻልም።

ቶማስ ኤዲሰን የኤሌክትሪክ መብራትን ለማግኘት ይሞክር በነበረበት ጊዜ አንዴ በሽቦው ላይ፥ ሌላ ጊዜ በአምፖሉ ክር ወይም ፊላመንት ላይ፥ ሌላ ጊዜ በአምፖሉ ሽፋን መስታወት ላይ፥ ሌላ ጊዜ በዲናሞው ላይ ብዙ ለውጦች እያደረገ እየሞከረ ያልሰመሩትን ነገሮች ሁሉ እየመዘገበ ያልሞከራቸውን ነገሮች ይሞክሩ ነበር። ተስፋ የቆረጠ ረዳቱ፥ “እነዚህን ሁሉ ሞክረን አልሠራልንምና ይህ የመብራት ነገር የሚሆን አይመስለኝም” አለው። ኤዲሰንም፥ “አየህ እነዚህን በመቶ የሚቆጠሩ ያልሠሩ ሙከራዎች እየጻፍኩት ያለሁት እንዳንደግማቸው ነው። ሌላው ነገር ደግሞ ከዚህ በኋላ ትንሽ ብንሳሳት ነው እንጂ የሚሠራውን ዘዴ ለማግኘት በጣም ቀርበናል

ማለት ነው" አለው። እውነትም እንዳለው በጥቂት ቀናት ውስጥ የኤሌክትሪክ መብራቱ ነገር ተከናወነ። እንዲህ ኤዲሰን መሳሳቱና መሳሳቱን ራሱ እየታዘበ ማረሙ አልረዳውም? ከስህተቱስ አልተማረም? መሳሳት ነውር አይደለም። ስሕተትን አለማወቅና አለማረም ወይም አለመታረም ግን ጉዳት አለው። ስላለፈው መጣጥፍና CD እዚህ ላይ ላብቃ።

ባለፈው CD ተቸሁ ወይም አሔስኩ እንጂ የሒስን፥ በተለይም የሕያሴ መዝሙራትን ምንነት አልገለጽኩም። በነገራችን ላይ የማሔሰው ዘማሪዎችን ብቻ አይደለም። ከዚህ በፊት በጻፍኩት አንድ መጽሐፍ በጸጋ ስጦታ አካባቢ የሚታዩ ቀውሶችን፥ ለምሳሌ ውሸታም ፈውሶችን፥ ሐሳዊ ትንቢቶችን፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ያፈነገጡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትና ብቃት የሌላቸውን ልምምዶች በግልጽ ወቅሻለሁ። በቅርቡ በታተመ ሌላ መጽሐፍ ደግሞ ሰባኪዎችንና በስብከት ዙሪያ የሚታዩ ፈር የጣሱ አተረጓጎሞችን በማሔስና ለናሙናም ሁለት ሰባኪዎችንና ስብከቶቻቸውን ወስጄ ጠለቅ ያለ ብርበራ አድርጌአለሁ። ከመጽሐፉ መታተም በፊትም ለሰባኪዎቹ ሊታተም ያለውን የነሱን ግድፈቶች ልኬ ነበር። የአንዱ ምላሽ ዝምታ ሲሆን ሁለተኛው አቋሙን የሚመከት ሙግት አቅርቦአል። ይህኛው ታናሽ ሥራ በመዝሙርና በዘማሪዎች ላይ ስላተኮረ ጉድ ሊሰኝ አይገባም። የእያንዳንዱን ዘማሪ ሥራ በነጠላ ለማሔስ ጥልቅም ባይሆን ሰፊ ጊዜና ጉልበት ይጠይቃል። ዘማሪዎች በነጠላ ከታዩ ፍሬም ገለባም አብሮ ይነሣል። ይህም እንግዲህ እንዳለፈው ሁሉ ጠቅለል ያለ የሒስ ሥራ ነው የሚያተኩረውም ግድፈቶች ብቻ ላይ ነው።

## ሒስና ሕያሴ መዝሙራት

ሒስ/ግለ-ሒስ የሚሉ ቃላትን ሲባል ሰምተን እናውቅ ይሆናል፤ በተለይም በደርግ ዘመነ ገዥነት። ስለመጽሐፍ ቅዱስና የአፈታት ስሕተቶች በጻፍኩት መጽሐፍ ላይ ሰለ ሒስ ምንነት ያሰፈርኩትን ጥቂት ቃል እንዳለ ላቅርበው። ይህ በመጽሐፉ አራተኛ ምዕራፍ [ሐያስያንን መጥላት በሚል ንዑስ ርእስ ስር] ከቀረበው [ገጽ 196-198] የተወሰደ ነው።

*በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አገልጋዮች አይሳሳቱም ማለት የዋኅነት ነው። እነ ሙሴን፥ አሮንን፥ ዳዊትን፥ ጴጥሮስን የመሰሉ ብርቱ መሪ አገልጋዮች ተሳስተዋል። ስሕተትን የሚያጎላው ሌላ ስሕተት የሳቱትን ዝም ማለት ነው። አንዳንድ አገልጋዮች ሲወቅሱአቸው አይወዱም። ያደረጉትን፥ ያስተማሩትን፥ የጻፉትን፥ የሰበኩትን አንስተው አስተያየት ሲሰነዝሩባቸው አይወዱም። ሒስ የስነ ጽሑፍ ቋንቋ ብቻ ወይም ኮሚኒዝም የቸረን ቃል አይደለም። ነባር ቃል ነው። አሳቡም ለማፍረስ መተቸት ወይም መተረብ ሳይሆን ገንቢ ለሆነ እርምትና ለማስተካከል መውቀስ፥ መንቀፍ፥ ጥፋትን ማሳየት፥ የማረሚያ ነጥቦችንም ማቅረብ ማለት ነው።*

*በአማርኛ መዝገበ ቃላት ትርጉም የሄድን እንደሆነ በጥሬ ትርጉሙ ሒስ በደል፥ ገመና፥ የሚያስነቅፍ ነገር፥ ነቀፋ ማለት ነው። ሐያሲም ነቃፊ፥ ከሳሽ፥ ወቃሽ ማለት ነው። ሌላው*

*ትርጉሙ ማሸት፥ ማፍተልተል፥ ማበራየት፥ መርገፕ፥ ማልፋት፥ ማፍረጥረጥ ማለት ነው። ደግሞም የሉታ አንቀጽ ሆኖ አንድ ነገር ትክክል አለመሆኑን መናገር ማረጋገጥ ነው። (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ገጽ 443 እና 465-466) ሒስ በዘመናዊና ሰፊ ትርጉሙ ስሕተትን ማሳየትንና ማስረዳትን የያዘ ነው። በዘመናዊ የትምህርት መስኮች ከአፍራሽነት ይልቅ ገንቢ በሆነ ሁኔታ በማናቸውም ሁኔታዎች የሚገለገሉበት የግምገማና የእርማት ሂደት ነው። ማሔስ፥ መውቀስ፥ ጥፋትን ማሳየት በየትኛውም ባሕል ጤናማ ነገር ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎችና በተለይም በኢትዮጵያውያን ልማድና ባህል እንደ አፍራሽ ተደርጎ ይቆጠራልና ገንቢው ገጽታው ብዙም አድናቆት አያገኝም። . .*

*ስሕተትን መጠቆም የግድ ከዚያ ከተሳሳተው ሰው የተሻሉ ሆኖ የመገኘት ምልክት አይደለም። እርሱ ካላየው አቅጣጫ ነገሩን ማስተዋል እንጂ መመጻደቅ አይደለም። አለማወቅ ነውር አይደለም፤ ያለማወቅን አለማወቅ ግን ስንፍና ነው። ማንም ሰው ፍጹም አይደለም። በድፍረትም ይሁን ግድ ለሽነት ወይም ባለማወቅ የተደረገ ስሕተትን ማወቅ ግን ለማደግ የሚረዳ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው። ለማደግ የምንመኝና የምንተጋ ሁላችን ስለ ሥራችንም ሆነ ስለ ራሳችን የሚሰነዘሩትን አስተያየቶች በሙሉ ድፍረትና በቅንነት ለመጋፈጥ ዝግጁ መሆን አለብን እንጂ “እርሱን ብሎ ተቺ” ማለት የለብንም። እንዲህ እንባላለን ብለንም ከመናገርና ከመሥራት ማፈግፈግ የለብንም። ያ [የተወቀሰው] ሰው ያልተሳሳተ ከሆነና ለዚያ የተሳሳተ መሆኑን ለነገረው [ወቃሽ] ሰው በግልጽ ሁኔታውን ማሳየት ቢችል ያንንም [ወቃሹን] ሰው መልሶ ያርመዋል። ስለዚህ ማንም አገልጋይ ለመፈተሽ ፈቃደኛ ሆኖ ቢገኝ ይህ የመብሰሉና ሌሎችንም ለመርዳት የመዘጋቱ ምልክት ነው። አገልጋይ ደግሞ ለመፈተሽ ፈቃደኛ መሆን ግዴታው ነው። ቢቻል ግን ማሔስ ከሌሎች ከመምጣቱ በፊት ከራስ ሲመነጭ ስሜታዊና ኀሊናዊ ብቻ ሳይሆን ሚዛናዊ በሆነና በቃሉ በተመሠረተ ሁኔታ አገልግሎትና ድርጊት ሲመረመር ውብ ነው። እንዲህ ከሆነ ያልተፈጸመ ስሕተት አይፈጸምም፤ የተፈጸመም አይደገምም። ስሕተት [እና ሒስ] በራስ መጥፎ ፍርድን መፍረጃ ሳይሆን መስተካከያና ሌሎች ያንን ጥፋት እንዳይደግሙ መከላከያ መሆን አለበት።*

ይህ ከመጽሐፉ የተወሰደ ነው። የመጽሐፉ ዓላማ ቃሉን በወጉ መፍታት ካለመቻል የተነሣ የሚመጡ የስሕተት ትምህርቶችና ልምምዶችን የሚፈትሽ ቢሆንም የሒስ ምንነት ዝማሬንም ጨምሮ በሌሎችም ዘርፎች የሚተገበር በመሆኑ ነው ይህን ክፍል የወሰድኩት። እንግዲህ ምንም ሙያና ማንም ባለሙያ ሒስ ይደረግበታል ማለት ነው፤ ይወቀሳል። የዚህ ግቡ እርማት ነው፤ መስተካከል ነው። እርማት ካስፈለገ ስሕተት ነበረ ማለት ነው። አንድ ሰው ከጓዳው ወጥቶ ወደ መድረክና ወደ አደባባይ ሲዘልቅ የሕዝብ ንብረትም እየሆነ መምጣቱን መቀበል አለበት። እንደ ዕቃ ያለ ንብረት ብቻ ማለቴ ሳይሆን፥ ያም በመጠኑ ሳይቀርለት፥ “እገሌ የኛ ነው፤ አስተማሪያችን፥ ሰባኪያችን፥ ዘማሪያችን፥ አገልጋያችን ነው” የሚል የሕዝብ ክፍል ይኖራል። በዚያ ወገን ታሳቢ ነው፤ ለዚያ ወገን ተጠያቂ ነው። ፍጹም የሆነ ማንም ሰው የለም። ሊፈተሽና ሊጠየቅ ግን ዝግጁም ፈቃደኛም ሊሆን አልፈልግም ካለ ይህ አስቸጋሪ ነገር ነው። ፍተሻ መለመድና መዳበር የሚያስፈልገው ባህል መሆኑን ለማሳሰብ ነው እዚህ ላይ ስለ ሒስ ጠንከር ያለ ትኩረት የሰጠሁት።

ማሔስ ብርቱ ነውር፥ ክፉ ወንጀል፥ ኃጢአትም እየመሰለን ለብዙ ዘመናት ኖረናል። የምንሰማውን ሁሉ እውነት ነው እያልንና እርስ በርሱ የሚጋጨውንም ሁሉ እንኳ እንደምንም እያዋሃድንና እያስታረቅን፥ አልዋሃድ ካለም በግድ እየበየድንና እያጣበቅን ስንቀበል ኖረናል። 'ይህ ነገር ከየት የተገኘ ትምህርት ነው?' ብሎ መጠየቅ የተለመደ ቢሆን ኖሮ ምንኛ ብዙ ሰዎች ከመወናበድ በተረፉ ነበር። ሒስ (Critique) ስሕተትና ጥራት ላይ የሚያተኩር የሥራ ሂደት ነው። ጥራትና ከጥራት ጋር አብሮ ስሕተት ላይ ማተኮሩ ነው ሒስን አሉታዊ ያደረገው እንጂ ግቡ ከታየ ሒስ ከቶም አሉታዊ አይደለም። ይህ የሒስ ነገር አሁን መነሣቱ በአንድ ወገን በጣም የዘገየ ነገር ነው። በሺህ የሚቆጠሩ አልበሞች ያለምንም መለኪያ ከታተሙ በኋላ ከእንቅልፍ እንደሚነቃ መንቃት ስንፍና ነው። ይሁን እንጂ ማለፊያ እርምጃ ነው። ከሚቀር ቢዘገይ ይሻላል (Better late than never) የሚል የእንግሊዞች ተረት አለ። ቀድሞም መደብ መኖር ነበረበት፤ አልነበረም ማለት አይደለም። የተመደበ መለኪያ ግን አልነበረም። ከሰው ወደ ሰው የሚለያይና ስሕተቶችን የሚያሾልክ ወንፊት ነው የነበረው። ስሕተቶች እየበዙ መጥተው እውነት መምሰል ሲጀምሩና የመደብ እና የመመዘኛ አስፈላጊነት በሚታወቅበት ጊዜ መለኪያው መኖር አለበት። ወርቁ ቢበዛም ባይበዛም ሚዛኑ ግን ሁሌም መኖር አለበት።

ሒስ መንደርደሪያ ወይም መነሻ አለው። በኔ ግምት ከሁለት ወይም ሦስት መነሻዎች መንደርደር እንችላለን። የመጀመሪያው ነባራዊ እውነታዎች ናቸው። እየሆነ ስላለው የቤተ ክርስቲያን የዘመኑ መልክ የሚለው አለው ይህ መዝሙር? መልእክት አለው ወይስ ቃላት ብቻ የተሰባሰቡበት ክምችት ነው? ሁለተኛ፥ አሁን ያለውን ለማሄስ የቀደሙት የሄዱበትን መንገድ ማየት ያንደረድራል። ይህ ማለት የቀድሞዎቹ ዘማሪዎች በሙሉ ልክ የአሁኖቹ በሙሉ ልክ ያልሆኑ ማለት ከቶም አይደለም። ቢሆንም ማስተያየትና ማነጻጸር፥ ግዴታ ነው። የምናስተያየው ማስተያያ ሲኖር ነው። ቀድሞ መዝሙሮች ከውጪ ቋንቋ እየተተረጎሙ፥ ባሕላዊዎቹ መዝሙሮች ደግሞ በባሕሉ ፈር እየተቀደደላቸው ነበር የተዘመሩት። ሆኖም ዘመናዊዎቹ መዝሙሮች ከትርጉም ወደ አገረ ገብ ሲለወጡ ፈር ቀዳጅና ፋና ወጊ የሆኑት ዘማሪዎቻችን ደማቅና አስመስጋኝ ሥራ ሠርተዋልና ከዚያ መነሻ መንደርደርና ማስተያየት ይቻላል። በዜማ ብንሄድ፥ በመልእክት ቢባል፥ በቅንብርና በመሳሪያ ቢኬድ አሻራ ጥለዋል፤ የግዝፈታቸውን ጥላ አጥልተዋል። ይህ ነጠላ ዘማሪዎችን ብቻ ሳይሆን የቡድን መዝሙር ደራሲዎችና አቀናባሪዎችንም ይመለከታል፤ በአንክሮ። ሦስተኛው መሠረት የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ነው። መንፈሳዊ ወይም ክርስቲያናዊ መዝሙር እንደስሙ ክርስቲያናዊ ነውና መነሻው መሠረቱ ቃሉ መሆን አለበት። "ይህ መዝሙር የክርስትና መሠረት ከሆነው ከቅዱስ ቃሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይስማማል ወይስ ይጋጫል?" የሚለው አሳብ የሒስ ትክክለኛና ትልቁ መንደርደሪያ ነው። የመዝሙሮች ክምችት የሆኑትን የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ብቻ እንኳ ተመልክተን የዘመናችንን መዝሙሮች ከነዚያ ጋር ማነጻጸር አይከብድም። መዝሙረ ዳዊት ልክ እንደ ብፌ ዓይነት ነው። ሁሉ አለበት፤ ድል፥ ሽንፈት፥ ብርታት፥ ገመና፥ ጠንካራ ትምህርት፥ በልምድ የተለወሰ ምክር፥ ከውስጥ ፈንቅሎ የወጣ ስሜትም አለበት። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ መዝሙራት ለዘማሪዎች ጥሩ ምሳሌና ሁነኛ አብነት ቢሆኑም እነዚያ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት

የተጻፉና የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው። ሆኖም ይዘታቸው የበረከትና የመሳካት ብቻ አይደለም።

ሒስ ሌላው ነጥቡ የቅርብና የሩቅ ግቦች አሉት። የቅርብና የፍጥነት ግቡ ጥፋትንና ስሕተትን መንቀስ ነው። የሩቅና ዘላቂ ግቡ ደግሞ የጠራና የጸዳ ውጤትንና ምርትን ማቅረብ ነው። ማሞካሸትና ማሞገስ ዋና ተግባሩ አይደለም። ሒስ በአመዛኙ 'እንዲህ ይሁን' የሚል አስተያየት ሰንዛሪ ሳይሆን 'እንዲህ አይሁን፥ ይህን አይምሰል፥ ይህን አዝማሚያ አይከተል' ባይ ነው። ያኛው በእግረ መንገድ ቢደረግም እንኳ ከተደረገ የሩቅ ግቡን ለመምታት የታለመውን ዒላማ ለመድረስ ነው። ልክ እንደ መፈብረኪያ ኩባንያ የጥራት ቁጥጥር (Quality Control) ዓይነት ሥራ ነው። የQC ሠራተኞች ጥሩ ጥሩውንና ትክክል የተሠራውን እያሳለፉ ስሕተት፥ ጉድለት፥ ግድፈትና ጉድፍ ያለበትን ግን ያስቆሙና ከመስመር ያስወጡታል። የዕቃ ኢንዱስትሪው ከመዝሙር ኢንዱስትሪ ምርቶቻችን ልዩነቱ ይህ ከመመረቱና ለተጠቃሚው ከመቅረቡ በፊት መሆኑ ነው። እንዲህም ሆኖ፥ የተበላሹ ዕቃዎች ወደ ሸማቹና ተጠቃሚው እጅ የሚገቡባቸው ብዙ አጋጣሚዎች አሉ። 'የተሸጠ እቃ አይመለስም' እየተባለ መለጠፍ በተለመደበት በአገራችን እምብዛም አይደረግም እንጂ፥ በሰለጠለው ዓለም ይህ ከተከሰተ ሸማቹ ዕቃውን ሊመልሰው መብት አለው፤ ሻጩም ሊቀበለው ግዴታ አለበት። ለምን ሊመለስ በቃ? ጉድለት ስላለበት። ለምን ጉድለት ኖረው? በጥንቃቄ እጦት። ለምን ጥንቃቄ ጠፋ? በቁጥጥርና በፍተሻ አለመኖር።

ከጥራት ቁጥጥር አምልጠው የተመረቱ አንዳንድ የተበላሹ ምርቶች እንዲያውም በአምራቹ ኩባንያ በራሱ እንዲመለሱ ይደረጋሉ። በሰለጠነው ዓለም፥ 'በዚህና በዚህ ዓመተ ምሕረት የተሠሩት እንዲህና እንዲህ የሚባሉ መኪናዎች ይህ ችግር አለባቸውና ወደ ኩባንያው ጣቢያ እየወሰዳችሁ እቃው ይለወጥላችሁ' ወይም 'ይህ መድኃኒት እንዲህ ያለ የጎንዮሽ መዘዝ አስከትሎአልና ያልተሸጠው ከየሱቁ መደርደሪያ እንዲመለስ/እንዲወገድ፤ የገዛችሁም እንዳትጠቀሙ' ይባልና ይመለሳል። የኛዎቹ መዝሙሮች ግን፥ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጅምላ እየተመረቱ ያሉት ብዙዎቹ፥ የጥራት ቁጥጥር ቀርቶ ሙከራውም ያልዳሰሳቸው፥ ሽታውም ያልነካቸው ናቸው። ግድፈት ያለባቸው መዝሙሮች ይመለሱ ቢባል ከብዙዎቹ CDዎች አንድ ሁለት መዝሙሮች ብቻ እየቀረ የቀሩት ለዘማሪዎቹ ይመለሱ ነበር። ባለፈው ስርጭትና በዚህም ስለመዝሙሮቻችን እየተደረገ ያለው ይህ ልክ እንደ QC ሥራ ያለ ነገር ነው። ሊደረግ የተሞከረው ምንም ምርቱ ቀድሞውኑ ገበያ ላይ ቢውልም እንኳ የጥራት ቁጥጥር ሥራ ዓይነት ነው። ግቡም ይህን መሳይ ስሕተቶች እንዳይደገሙ ነው። ማመስገንና ማበረታታት መልካም ቢሆንም የጥራት ተቆጣጣሪዎች ሥራ ማመስገን ሳይሆን ጉድፍና እንከንን ማጥራት ነው። ማመስገንና ደመወዝ መጨመር፥ እድገት መስጠትና እርከን ማስረገጥ፥ መሾምና መሸለም የአለቃውና የአስተዳዳሪው ሥራ ነው። የማመስገንን ተገቢነት ሳልዘነጋ ይህ ዓይነቱ ሥራ የጥራት ፍተሻና የሒስ መሆኑን እንደገና ላሳስብ እወዳለሁ። ስለዚህ አድማጮችም ዘማሪዎችም ይህንን እንድትገነዘቡልኝ እወዳለሁ።

ሒስ በባህርይው እንዲህ ያለውን የስሕተት አካሄድና አዝማሚያ የማረም ሒደት በመሆኑ መታረምን የማይፈልጉ ሰዎችን የሚያስቆጣ ተፈጥሮ አለው። አንድ ወጣት የአምልኮ መሪ ያለፈውን CD ካዳመጠ በኋላ አስተያየቱ፥ "ይህ ያስደነብረኛል እንጂ አያርመኝም፥ አይመልሰኝም" የሚል ነበር። የሚያስደነብር ነገር ከኖረ መደንበር አስፈላጊና ትክክለኛ ነገር ነው። መደንበር ብዙ ጊዜ ከብቶች እንግዳ ነገር ሲያዩ የሚያደርጉት ምላሽ ነው። አውሬ ካዩ ወይም ሞተር ቢስኪሌት ሲያዩ አውሬ ይመስላቸውና በርግገው ራቅ ይሉና ቆም ብለው ሰላም ከሆነ ወደ ተግባራቸው፥ ወደ ግጦሻቸው ይመለሳሉ፤ ሽብር ከሆነም ራሳቸውን ለመጠበቅ ሽሽታቸውን ይቀጥላሉ። የሚያስደነብር ነገር ከኖረ መደንበር ተገቢና ጤናማ ነገር ነው። CDው አስደንብሮ ከሆነ ጥሩ ነው፤ ያስደነበረው ነገር ወይ አውሬ ነው፤ ወይም ቢስኪሌት ነው። "አይመልሰኝም" ላለው ግን የምለው የለኝም። መመለስ ወይም መፈርጠጥ የአድማጩ ምርጫና ውሳኔ ነው። ይህ ወጣት ላለመታረም ወይም ላለመመለስ ወስኖና አምርሮ በዚያ መንገድ ቀጥሎ ከሆነ እስኪመለስ መጠበቅ ነው። ግን ከዚህ በኋላ በርጠሜዎስን በርተሎሜዎስ፤ ወይም አርያምን ጸባዖት እያለ የሚዘምር አይመስለኝም። ይህን ካደረገም በቂ ነው። የዚያ [CD] ዝግጅት ግብም ይኸው ነበር።

## የመዝሙር ምንነት

ከሒስ ምንነት ጋር ተያይዞ ሳይነሣ መቅረት የሌለበት ሌላ ነጥብ የራሱ የመዝሙር ምንነት ነው። መዝሙር ምንድርነው? መዝሙር ጥበብ ወይም ኪነ ጥበብ ነው? ሙያና ሥራ ነው? ንግድና ገንዘብ ማግኛ ነው? ወይስ አገልግሎት ነው? ወይስ ከተጠቀሱት የጥቂቱ ቅይጥ ነው? ከነዚህ ከተጠቀሱት ነገሮች በአንዱ ወይም በሌላው መፈረጁ የምንሰጠውን ትርጓሜ ማቅለም ብቻ ሳይሆን የይዘቱንም ምንነት ይወስነዋል ወይም ይለውጠዋል። ከመዝሙር ጋር የጠበቀ ቁርኝት ያላቸው ሰዎች መዝሙርን ከእነዚህ በአንዱ ቅይድ ውስጥ ያስቀምጡታል። እኔም እንደ ሕያሴዎች ጸሐፊ በአንዱ ማስቀመጥ ይጠበቅብኛል። መዝሙር፥ ማለትም ክርስቲያናዊ መዝሙር በአጭር ቋንቋ <u>አገልግሎት</u> ነው። ዓላማ ያለው ግብ ያለው አገልግሎት ነው። ወደ እግዚአብሔር (በውዳሴ)፥ ወደ ሰዎች (በማነጽና በመጥራት)፥ ወደ ራስ ውስጥም (በአምልኮና በጸሎት) የሚያመለክት አገልግሎት ነው። መዝሙር አገልግሎት ነው። አገልግሎቱ መጽሐፍ ቅዱስንና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስነ መለኮትን የተንተራሰ የማነጽ አገልግሎት ነው። ስሜትን ማሟሟቅ አይደለም። ያላመኑትን ወደ ክርስቶስ የሚጠራና የሚጋብዝ፥ ያመኑትን እንደ ስብከት፥ ትምህርት፥ ትንቢት፥ ተግሳጽ፥ ምክር አገልግሎት ሁሉ የሚያንጽ፥ ከጌታ ጋር ያለንን ግንኙነትን የሚያጠነክር አገልግሎት ነው። መሠረቱ ቃሉ ነውና ከቃሉ ጋር መጋጨት የለበትም። ማእከሉና ትኩረቱ ጊዜአዊው ሳይሆን ዘላለማዊው መሆን አለበት።

ከዚህ በቀጠለ ደረጃ መዝሙር ኪነ ጥበብም ነው። ይህ ግን አገልግሎትነቱን ሳይጥል መሆን አለበት። ከጣለና እንደ ጥበብ ብቻ ከተወሰደ ከማዝናኛና ከኪነት ወይም ከጎብረ ትርዒት የተለየ ላይሆን ነው። ጥበብነቱ ደግሞ የጠራና የሰከነ፥ የላቀና የጠለቀ መሆን አለበት። ይህ መሣሪያንም፥ ቅላጼንም፥ ዜማንና ቅንብርንም፥ ስንኞችንም፥ ይዘቱንና መልእክቱንም የተመለከተ ነው። የግጥማችን ቤት አመታት ኢየሱስ ካለ ንጉሥ ወይም ጌታ ካለ መከታ ብሎ መጨረስ ደንብ እየመሰለ መጣ። የመዝሙር ግጥሞችና ቃላት ተደጋጋሚና አሰልቺ እየሆኑ መጥተዋል። ለዚህ ሳይሆን አይቀርም ብዙ ዘማሪዎች ቃላት ባገኘሁና፥ እልፍ ልሳን በኖረኝና፥ ማመስገኛ ቃላት አጣሁ ወዘተ፥ እያሉ የሚዘምሩት። ቃላት አጥተው ግን መዘመር አልተዉም። እውነት ቃላት አጡ ወይስ ጥረትና ጊዜ አጡ? ጥበብ ጥረት ይጠይቃል፤ ጊዜ ይጠይቃል። ያንጎራጎርነው ሁሉ መዝሙር ሆኖ መታተም አይገባውም። አቅሙ የለውማ! ይህ ቃላትን ብቻ ሳይሆን የሙዚቃ ቅንብርንና ዜማንም፥ ድምጽንም ይመለከታል።

## የመዝሙሮች ይዘት መውረድ መንስኤዎች

መዝሙር ሙያና ሥራ፥ ንግድና የንዋይ መሰብሰቢያ አይደለም። አሰምርበታለሁ፤ አይደለም። በዚህ ከጥቂት ዘማሪዎች ጋር አንስማማ ይሆናል። በተለይም በመዝሙር እንዱስትሪና ንግድ ዘርፍ ከተሰማሩት ጋር አንስማማም። ላለመስማማት እስማማለሁ ወይም አለመስማማትን እመርጣለሁ። በድምጽና በሙዚቃ ትምህርት ቤት አልፈው የሰለጠኑቱ እንደሙያ ቢሠሩበት የሚሠሩትን ያውቃሉና እንደ ባለሙያ በማሰልጠንም፥ በማስተማርም፥ አቅጣጫ በማሳየትም፥ ቢሰለፉ ተገቢ ነው። ይህ ኑሮአቸው ነውና መኖሪያቸው ሊሆን ደግሞ ግድ ነው። ደግሞም ቤተ ክርስቲያን የዘማሪዎችን ስጦታ፥ ችሎታ፥ ዝንባሌና ጸጋ አስተውላ እንደ አገልጋይ ብታሰማራቸውና የሚያስፈልጋቸውንም ብታደርግላቸው ይህ ተገቢ ነው። እንደ ሙሉ ጊዜ አገልጋዮች አሰማርታቸው ከሆነ ደግሞ የሚያስፈልጋቸው ብቻ ሳይሆን የሚገባቸውም መደረግ አለበት። በተረፈ ግን፥ ገንዘብን ዒላማ አድርጎ ወደ ብር እየተዘረጉ መምዘግዘግ አገልግሎቱ አሁን እየወደቀ ወዳለበት እየገፋ ይጥለዋል፤ በወደቀበትም ይረጋግጠዋል። የበርካታ ዘማሪዎች ከመጀመሪያ አልበም በኋላ የሚከተል ማዘቅዘቅ ከገንዘብም ጋር የተያያዘ ነው። የመጀመሪያው በጸሎት ተለውሶ ይወለድና ቀጣዮቹ የገንዘብ መሥሪያ ይሆናሉ። የሚሠራው ገንዘብ ደግሞ ትንሽ ስላልሆነ ቀያይጦም፥ አቀጣጥኖም፥ ቶሎ ቶሎ ብሎም ይመረታል። የጥራቱ ጉድለት ከቃሉ ጋር መጣረስን ሲያስከትል የፈዘዘው አድማጭ ‘ምን እየሆነ ነው?’ እንዲል የማንቂያ ደወል ማሰማት አስፈላጊ ነው።

ከዚህ ተያይዞ የሚወሳው አሳብ መዝሙር መዝናኛና መስተንግዶ ነው ወይስ አምልኮ? የሚለው ነው። ዛሬ ዛሬ መዝሙሮችና ዘማሪዎች እንደ ኪነትና ኀብረ ትርዒት ያለ መልክ እየያዙ እየመጡ ነው። ይህ በሠርግና በልደትና በመሳሰሉት በዓላት የሚደረጉትንም ይጨምራል። አምልኮና

ስብከተ ወንጌል ግቡ ከሆነ ምንም ችግር የለበትም። እንዲያውም በአጋጣሚው ሁሉ ወንጌሉ እንዲተላለፍ ሊበረታታም ይገባል። ከዚህ ሌላ ከሆነ ግን ችግር አለበት። በሌላኛው ገጽታው ግን ድግስ እየተደገሰና ገንዘብ እየተከፈለበት፥ አምልኮ እየመሰለ ነገር ግን ቅርፊቱ ብቻ አምልኮ እየሆነ እየመጣ ነው። አንዳንዶቹ ከነስሙ የመዝሙር ድግስ ይሉታል። እነዚያ የሙዚቃ ድግስ የሚሉት ክርስትና ተቀብቶ ማለት ነው። ይህ አዝማሚያ ለብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሳሳቢ እየሆነ ነው። ስብሰባ፥ ድግስ፥ ኮንሰርት፥ ወዘተ እየተባለ ዓላማውም ግቡም ከቤተ ክርስቲያን ተልእኮ የወጣ ነገር እየተደረገ ነው። አንዳንድ ቦታ ዓለማዊ ባለሙያዎችም ከቴክኒክ እስከ ሙዚቃ መሣሪያ ጨዋታ እየተቀጠሩ የሠሩባቸው ጊዜዎች አሉ። እንዲያውም አምልኮውን አለመምራታቸው ሊያስመሰግን ሳይገባ አይቀርም። በዚህ ዙሪያ የታዘብኳቸውን ጥቂት ነጥቦች ላንሣ፤

- በመልካም ጎኑ ለአምልኮና ወንጌልን ለማሰራጨት ሊሆን ይችላል። አንድ ወንድም፥ ‘ዓለማውያንን ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ ቤተ ክርስቲያን ወዳልሆነ ቦታ መጥራት ቀላል ስለሚሆን ነው ይህ ያስፈለገው’ አለ። ይህ ምናልባት የሚቀልል ይመስላል። ከሆነም በጣም ጥሩ አገልግሎት ነው። ግን ካየኋቸው ጥቂት ድግስና ኮንሰርቶች በአንዱም ወንጌልን ላልሰሙ ያሰራጨና ለደኅንነት የጋበዘ አላየሁም። ስብከት የለም፤ ቢኖርም መሟሟቂያ እንጂ የደኅንነት ወንጌል አይደለም።
- አንዳንዱ ከትልቅና ከሚያምር መድረክ ላይ ሆኖ በምስል ለመቀረጽና በኋላ ያንን ከሌላ ነገር ጋር ቀይጦ ወይም ሳይቀይጡ ለገበያ ለማዋል የተደረገ ሙከራ ነው። ይህ በስፋት ተደርጎአል።
- አንዳንዱ እንዲያውም ለመታወቅና ለመተዋወቅ ብቻ ተብሎ የተደረገ መሰናዶ ነው። አምልኮውን የሚመራው ወይም የሚያስተዋውቀው ሰው ያንን ዘማሪ ሲያስተዋውቅ ወደ መድረክ የምትመጣው ወይም የሚመጣው ዘማሪ የእሴይ ልጅ ዳዊትን ወይም ሐዋርያው ጳውሎስን ነው የሚያስመስሉት።
- ሌላው ለገንዘብ መሰብሰቢያ ነው። ይህ ከመግቢያ ቲኬትም ከሚሰበሰብ መባም ወይም የፈቃድና የፍቅር ስጦታም ሊሆን ይችላል። ገንዘብ ካስገኘ፣ ገንዘብ ካወጣ፥ ካዋጣ፥ ጸጋም ቢሆን ይዋል ገበያ ላይ እንደማለት ነው። ጸጋ በገበያ መቸብቸብ የለበትም።

ከተሰጡኝ አስተያየቶች አንዱ አንድ የማደንቀው የመዝሙር ቅኔና ዜማ ደራሲ ያለው ቃል ነው፤ “ይህን የመሰለው ሒስ በዓለማዊው ስነ ጥበብ ተደርጎ ቢሆን የተሻለ ውጤት ይኖረው ነበር” የሚል ነበር። አሳቡ የሒስን ተቀባይነትና የታራሚነትን ፍላጎት ለማመልከት ነው። በነዚያ ዘንድ ሕያሴ ኪነ ጥበብ ጉልህ ስፍራ ስላለው አሳቡ ትክክል ሊሆን ይችላል፤ ውጤቱም አመርቂ ሊሆን ይችላል። እኔ የዓለማውያንን ሥራ ለማሔስ ጥልቅ እውቀትና ሰፊ ጊዜ የለኝም። ዓለማውያን ከያኒዎች በኔ እምነት ከክርስቲያናዊ ሒስ በፊት ክርስቶስ ራሱ ነው የሚያስፈልጋቸው። ጉዳዩ ከኔ መስክና ሙያ የራቀ ቢሆንም ይህ አስተያየት ግን በዓለማዊውም ዘፈን በኩል ያለውን ዝቅጠት እየታዘብኩ የኛዎቹን ዘማሪዎች አረማመድ እንድዳስስ

አድርጎኛል። አንዳንዴ ዘፈኖችን ሳናስብም ሳንፈልግም እንሰማለን። ዱሮ እሰማ የነበረው ወይም እየሰማሁ ያደግኩት ዓለማዊ ሙዚቃ ምንጭ ሬድዮ ነው፤ እና እሰማ የነበረው አድማጮች የሚመርጡትንና የሬድዮ አዘጋጆቹ የሚያቀርቡት ነው። ታዲያ የዚያኔዎቹ ዘፈኖች ቁም ነገር የያዙ ነበሩ። ክርስቲያናዊ መዝሙሮችን እያሔስኩ ዘፈኖችን መጥቀስ ነውር ቢመስልም እየሰማሁ ካደግኋቸው ጥቂቶቹን ልጥቀስ፤ ተማር ልጄ ሌት ፀሐይ ነው ላልተማረ ሰው ግን ቀኑ ጨለማ ነው፥ ውሸት ለመናገር አትሻም ምላሴ ለእውነት እሞታለሁ አልሳሳም ለነፍሴ፥ አክብር አለቃህን በስነ ሥርዓቱ ሸር ጉድ ሊታብዛ በየምክንያቱ፥ ኑኑዬ ጨቅላዋ ሳይሽ ደስ ይለኛል ከመጥፎው አሳቤ ፍቅርሽ ይገታኛል፥ ሊያጠፋ የለም ሁሉም በየቤቱ የኔስ የብቻው ነው ኧረ ስንቱ ስንቱ፥ አርቆ ማሰቢያ እያለን አይምሮ እንደምን ተሳነን ለማክበር ቀጠሮ፥ ጋብቻ ክቡር ነው ወረት ያልዳሰሰው፥ የእናት ውለታዋን ባወሳ ወዳለሁ፥ ማየት መልካም ሁሉን እዩ ግን በትዳር ቀልዱን ተይ፥ መሃይም ኢያሉ ሰው እንዴት ይናቃል ያልተማረ አዋቂ ሲጠይቅ ይጨንቃል፤ ወዘተ ወዘተ። መልእክት አላቸው፤ እውነትንና ቁምነገርን ነው የሚናገሩት፤ ቃል ኪዳን መጠበቅን፥ ወሽካታ አለመሆንን፥ አክብሮትን፥ ታማኝነትን፥ ቅንነትን አለመናቅን ነው የሚናገሩት። ጥቂቶቹማ መንፈሳዊ መዝሙር ለመምሰል ማዘንበል ይታይባቸዋል። እየቆዩ ግን እየዘቀጡ የመጡ ይመስላል።

ከ10 ዓመታት በፊት በሰማሁት አንድ የኢትዮጵያ ሬድዮ ዝግጅት የዝግጅቱ አቅራቢ የጥንቱን ሙዚቃና የዘመኑን እያነጻጸረ ሲተነትን፥ “የኢትዮጵያ የሙዚቃ ጎማም ከአብዮቱ ፍንዳታ ጋር አብሮ ፈነዳ” በማለት ይጀምርና የይዘቱን፥ የቋንቋውን፥ የጭብጡን እየተንደረደሩ መውረድና መውደቅ አቅርቦ ነበር። ከማነብባቸው ጽሑፎች እንደታዘብኩት የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የየአገሩ ሁሉ የዘፈን ይዘት እየተቀየረ መጥቶአል። በምዕራቡ ዓለም ከ60ዎቹ በፊት ታማኝነት፥ ሥራ ወዳድነት፥ ቤተ ሰባዊ ፍቅር፥ ሃይማኖተኝነት ነበሩ ጭብጦቹ፤ በአመዛኙ። የ60ዎቹ የሮክ ሙዚቃ ንቅናቄ የጭብጡን አትኩረት ወደ ወሲብ ቀየረው። ይህ በከፊል የወጣቱ ትውልድ እስካሁንም የቀጠለ ሆኖ እስከ 70ዎቹ ዘለቀ። በ70ዎቹና 80ዎቹ ደግሞ አመላካች ቀስቱ አቅጣጫውን አዙሮ አዝማሚያው የሃሺሽ፥ ጠፍቶ የማጥፋት፥ አጥፍቶ የመጥፋት፥ የወንጀልና የማሸበር፥ ለሕግ፥ ለደንብ፥ ለስርዓት አለመገዛት አለመታዘዝ ሆነ። በ80ዎቹና 90ዎቹ መልኩ በፍጥነት እየተቀየረ የአምልኮና ሰይጣናዊ ሃይማኖት ማስተላለፊያ ሆኗል። በአገራችንም ከዚህ የተለየ አይደለም። የቀድሞዎቹ ቁም ነገሮች በርካሽ ወሲባዊ ዘፈኖች ተተኩ። ተረከዟ፥ ባቷ፥ ዳሌዋ፥ ከሷ ጋር ተኝቼ ሲነጋ ልሙት፥ ወዘተ ሆኑ። ሰይጣናዊ አምልኮውም አልቀረም፤ “ጃህ ያስተሰርያል” የሚል ዘፈን በቅርብ ሰምቼ ነበር። ጃህ ሲል ዘፋኙ ምናልባት ይሆዋን ወይም እግዚአብሔርን ማለቱ ይሆን? ግን ዘፈኑ እግዚአብሔር ስለሚያስተሰርይበት በመስቀል ላይ ስለፈሰሰው የክርስቶስ ደም ሳይሆን ስለ ኃይለ ሥላሴ ነው። ራስታዎች ጃህ ወይም አምላክ የሚሉት ደግሞ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ነው። ሊያሳዝንም የክርስቶስን አዳኝነት በሚችና በሞተ ንጉሥ መተካቱ? በአገራችንም ሳይቀር ዘፈኖችም አምልኮ እየመሰሉ እየሄዱ ናቸው።

መዝሙሮቻችንም ከዚያ ባልተናነሰ፥ ምናልባትም በፈጠነ አወራረድ እየወረዱ መሆናቸውን እናስብ። ይህ አዝማሚያ ዝም ከተባለ መውረዱ ወደ መውደቅ እንደሚያደርሰው መገመት አይከብድም። በቅርብ ባነበብኩት እንዳለ በሽር በጻፈው አንድ መጣጥፍ ዘፋኞች መጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሽ ዘይቤን እየተከተሉ መንፈሳዊ ሳይሆኑ ግን እየመሰሉ ሲሄዱ በአንጻሩ ጥቂት ያልሆኑ ዘማሪዎች ደግሞ አዝማሪ ቤት መጎብኘትና ማዘውተርን መጀመራቸውን አውስቶአል። ይህ ከሆነ አገልግሎትን የሚያዘቅጥ ብቻ ሳይሆን ሕይወትንም የሚበክል በሽታ ነው። እንዲህ የሚያደርጉት "ዘማሪዎች" ከየት የተለቀመ ገፈፍ ሊያበሉን እንደሚጥሩ መገመት አይከብድም። ቀደም ሲል ከጠቀስኩት መጽሐፍ በዝርዝር ሳይሆን በነጥብ ልወስድ የምፈልገውን ሌላ አንድ አሳብ ላክል። ይህም ከስሕተቶች ጀርባ ያሉት ነገሮች ምንነት ነው። [ከገጽ 171-173 ባለው ክፍል] ከስሕተቶቹ ጀርባ በአጠቃላይ እይታ ሦስት የተለያዩ ግፊቶች መኖራቸውን ጠቁሜአለሁ። እዚያ የተብራራው ከሐሰት አስተማሪዎችና ከስሕተት ትምህርቶችና ልምምዶች ጀርባ ያሉ ግፊቶች ቢሆንም ይዘቱ እንጂ አሠራሩ ያው አንድ ነውና እዚህም እንየው። እነዚህ ሦስት ግፊቶች፥ <u>ንጹሕ ኀሊና፥ ጥቅም፥ እና ሰይጣናዊ አሠራር</u> ናቸው።

ከኋላ ጀምረን ወደ መጀመሪያው ለመሄድ <u>ሰይጣናዊ አሠራር</u> ጭልጥ ያለ ሰይጣን ሰዎችን ከጌታና ከእውነት መንገድ ሊለይ የተገለገለበት መሣሪያ ነው። እነዚህ ግፊቶች በመዝሙሮች ውስጥም አይተላለፉም ማለት የዋህነት ነው። ሊተላለፉ ይችላሉ። መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በማንበብ ፈንታ መዝሙር የሚያኙኩ ክርስቲያኖች ጥቂት አይደሉም፤ ዘማሪዎቹ ዋና ምንጫቸው ቃሉ ካልሆነ እነዚህ መዝሙር ቀለቡዎች በተሳሳቱ መዝሙሮች በቀላሉ ሊወናበዱ ይችላሉ። ሰይጣን ደግሞ እውነትን አጣምሞ ማቅረብ ሥራው ነው።

<u>ሁለተኛው ጥቅም ነው።</u> ጥቅም ፈርጁ የበዛ ነው። መታወቅና ዝና ሊሆን ይችላል፤ ሥልጣንና የበላይነትን መቆናጠጥ ሊሆን ይችላል፤ ንዋይና ብልጽግናም ሊሆን ይችላል። የዝማሬ አገልግሎት በእነዚህ ገመዶች አይወሳሰብም፥ አይጠፈርም ማለት አንችልም። ጎላ ያለው የጥቅም ፈርጅ ገንዘብ ነው። ከገንዘብ ጋር ስለሚያያዝበት ገጽታው በቀደመው ስርጭት በመጠኑ ተገልጦአል። አሁን አሁንማ የመዝሙር ካሴቶችና CDዎች ሽያጭ ዋጋ እስኪያንገደግድ ድረስ ትልቅ ነው። አንድ ካሴት ወይም CD በማሳተም በአቋራጭ የገንዘብ ቆጥ ላይ መውጣትም አለ ለካ እያሉ በሰው ሠራሽ ችሎታ ሊዘምሩ የጣሩ ጥቂት አይደሉም። ስለዚህ ድምጽ ያላቸውም የሌላቸውም፤ ቅኔ መቀኘት የሚችሉትም የማይችሉትም እየዘመሩ ይገኛሉ። ምንም መለኪያ የለማ! ቢኖርም እንኳ መለካትና መሰፈር፥ መጠየቅና መፈተሽ አይፈልጉም። ይህ የገንዘብ መጠን የንዋይ ፍቅር የሌላቸውን እንዲኖራቸው፥ ያላቸውንም እንዲገፉበት አያደርግም ማለት አሁንም የዋህነት ነው። ከገንዘብ ጋር በተያያዘ መልኩ አንዳንድ ዘማሪዎች አገልጋይ ሳይሆን ባለሙያ እስኪመስሉ ድረስ የሚያስተዛዝቡ ሁኔታዎችም እየታዩ ናቸው። በድግስ ቤትና በሠርግ ቦታዎች የአዝማሪ ሙያ መተኪያ እየሆኑ ናቸው። ማምለክና ማስመለክ ተገቢነቱ አልጠፋኝም፤ ግን ጫን ያለ ገንዘብ ቀብድ ካልተያዘ ወይም እጅ በእጅ ካልተከፈለ አገልግሎቱ [ሥራው ቢባል ይሻላል ወይም ሙያው] አይፈጸምም።

<u>ሦስተኛው ንጹሕ ኅሊና ነው።</u> ይህ ካለማወቅ የተነሣ መሳሳት ነው። እንደሚታወቀው ኅሊናችን ቀድሞ የተማርነውን ነገር እውነትነት ወይም ስሕተትነት ያረጋግጥልናል እንጂ አዲስ ነገር አያስተምረንም። ስሕተቱን እውነት ነው ብለን ተምረን ከሆነ እውነት መሆኑን ያስታውሰናል እንጂ ስሕተት ነው ብሎ አይወቅሰንም። ይህ የየዋኅነትና የብስለት እጦት ስሕተት ነው። በኔ ግምት በመዝሙሮች የተሳሳቱ ስንኞች ውስጥ የሚታዩት አብዛኞቹ ስሕተቶች ከዚህ ክፍል የሚወድቁ ሊሆኑ ይችላሉ። አንድ ዘማሪ አንድን ስሕተት የተሳሳተው ባለማወቅና ባለማስተዋል እንደሆነ ሊናገር ይችላል። እውነትም ሊሆን ይችላል። ይህ አዝማሚያ ግን እንዲቀጥል መተው የለበትም። ዘማሪውም በስሕተቱ መግፋት የለበትም።

ከጥቂት ዓመታት በፊት በአንድ መጽሐፍ ውስጥ፥ "ዛሬ ቤተ ክርስቲያንን ለከፍተኛ አደጋ እያጋለጠ ያለው ከተኩላዎች ተኩላነት ይልቅ የበጎቹ በግነት ነው" የሚል ቃል አንብቤ ነበር። እውነት ነው። ምእመናን በቀላሉ አማኞችና በቀላሉ የሚሸነገሉ ከሆኑ፥ የሚነገራቸውንም ሆነ የሚዘመረውን ሳያጤኑና ሳያበጥሩ የሚቀበሉ ከሆኑ ስሕተቱ ይባዛል እንጂ አይቀረፍም፤ አይቀነስም። እንደ ቤርያ ክርስቲያኖች ልበ ሰፊዎችና መርማሪዎች መሆንን ማወቅ አለብን። መዝሙሮችን እንደ መዝናኛና መስተናገጃ ብቻ መቁጠር አንድ ነገር ነው። የምናመልክበት፥ ትምህርት የምንቀስምበትና ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረንን ግንኙነት የምናጠናክርበትና የምናስውብበት መሣሪያ ነው የምንል ከሆነ ግን ይዘቱን ማጤን አለብን እንጂ በየዋኅነት ሳር መስሎን ከሳር በታች የሆነ ነገር መብላት በግነት ሳይሆን ከበግም በታች መሆን ነው። ቃሉ በማስተዋል እንድንዘምር ያሳስበናል። በማስተዋል ማድመጥም አለብን።

ሌላው የበጎች በግነት ገጽታ ዘማሪዎችን ያለ አገባብ ማሞካሸትና የሌላቸውን ከአገልግሎታቸውና ከአቅማቸው የበለጠ ስፍራና አገልግሎት መስጠት ነው። በአንዳንድ ጉባኤ ለመዘመር የመጣ ዘማሪ መዝሙሩን መንደርደሪያ ብቻ አድርጎ ሰባኪ መሆን ሲቃጣው ይታያል። አንዳንዱ ሰባኪ ደግሞ ከመስበኩ በፊት መዝሙርን አስታኮ አምልኮ በማስመሰል ጉባኤውን በሽብር ሲሞላ በጥቂት ቦታዎች ታዝቤአለሁ። እነዚህ ሁለት ዓይነት ሰዎች አገልግሎታቸውን ቢለዋወጡ ይሻል ነበር። ይህ የአጋጣሚና የአንድ ጊዜ ክስተት ሳይሆን በጥቂት ቦታዎች የተለምዶ አገልግሎት ይመስላል። የታዘብኳቸው አንዳንድ ዘማሪዎች ከመዝሙር አገልግሎታቸው ጋር አዋህደው "ሊሰብኩ" የሚሞክሩት የተዘጋጁበትን ሳይሆን በጊዜው የመጣላቸውን ነገር በመሆኑ አንዳንዴ ሊያነቡ የፈለጉት ምንባብ ክፍል እንኳ እየጠፋባቸው ያላሰቡትንና እያሉና ያልተጻፈውን እንደተጻፈ አስመስለው ሲዘላብዱ ይሰማሉ። ይህን ሲያደርጉ የኃፍረት ምልክት አይታይባቸውም። ይህን ሁሉ ያልተዘጋጁበትን ድንገተኛ ነገር የሚያደርጉት ደግሞ ጉባኤው ለረጅም ሰዓት እንዲቆምና ዓይን እንዲጨፍን ገዝተው ነው። አንዳንዶቹ እንዲያውም ቁሙ፥ ጨፍኑ፥ እጆቻችሁን ዘርጉ ሲሉ የተቆጣጣሪነት ባህርይ ይታይባቸዋል። ይህ ከዚያ በፊት ወይም በዚያ ሰዓት የሚያደርጉትን የሚያውቁትን ሰዎች ሳይሆን በስሜት ብቻ ተነድተው ያላሰቡትንና ያልተዘጋጁበትን ግብታዊ ነገር የሚሠሩትን ነው።

# ክፍል ሁለት፥ ሕጸጾች

## ሀ) የመዝሙሮች እድሳት

ለአንዳንድ ዘማሪዎች የሰነበቱ መዝሙሮቻቸውን እንደገና አድሰው ማውጣት አዲስ ባህል እየሆነም ነው። እርግጥ አንዳንድ መዝሙሮች የትዝታ መግነጢሶች ናቸው። ወደ ኋላ ወስደው ከጌታና ከሕዝቡ ጋር ያሳለፍነውን የቀደመ የሚጥም ዘመን ቃና ያመጣሉ። ትዝታ ብቻ ሳይሆን ታሪክና ሐውልትነት ያላቸው ናቸው። እንደገና ባይዘመሩም እየታወሱና ጉልበታሞች እንደሆኑ የሚኖሩ ናቸው። በቀድሞው ዘማሪም ይሁን በሌላ ዘማሪም ቢደገሙም ይጥማሉ። እርግጥ ነው፤ የቀድሞዎቹ የተቀረጹ ካሴቶች ከምችቶች እየጠፉ መምጣታቸው አሳሳቢ ነው። ጥያቄው ግን መዝሙሮቹ ላይ ሳይሆን እንደገና መዘመራቸው ላይ ነው። አዲሱ ትውልድ ስለማያውቃቸው ለማስተዋወቅ ይሆን እንደገና መዘመር ያስፈለጋቸው? አንድ ዘማሪ ምክንያቱ አድርጎ የተናገረው ይህንን ነው። የመዝሙር አካሄድ በማሽቆልቆሉ የአሁኑን ከቀደመው ጋር ለማነጻጸር መንገድ ለመመንጠር ይሆን? ይህ ሊሆን ይችላል ግን፥ የቀድሞዎቹ ብቻ ሳይሆኑ የቅርቦቹም የሙዚቃ መሣሪያውን ብቻ ቀየር አድርገው መልሰው እያወጡ ናቸው። ወይም መሳ ለመሳ አዲስና ከቀድሞዎቹ ከፊሉን እየዘመሩ ካሴቱን ይሸጡታል። እውነተኛው ጥያቄ ግን፥ መዝሙርም ነጠፈና ነው መደገም ያስፈለጋቸው? ወይስ ይህም የካሴት ምርትና የገበያ ሽሚያ ነው? የሚለው ነው። እነዚህን ጥያቄዎች ጠያቂዎቹ ሳይሆን ተጠያቂዎቹ ቢመልሱት ያምራል።

ከመዝሙሮቻችን ፈር ቀዳጅነትና የአዲስ ነገር ጀማሪነት (originality) እየጠፋ መምጣቱ ሳያንስ ያንኑ እንዳለ የመድገሙ አስፈላጊነት አልታየኝም። ዘማሪ ገዛኸኝ ሙሴ ስለ ዘማሪ ደረጃ ከበደ ቁጥር 9 አልበም በጻፈው መጣጥፍ፥ *"ተባርኬያለሁ! ጥሻለሁ! ጠርምሻለሁ፤ በእጥፍ ቅባት ተቀብቻለሁ፤ ለየት ያለ መንፈስ ወርዶብኛል፣ ከፍታ የኔ ነው፣ ዘመኑ የኔ ነው፣ ዘወር በሉልኝ፣ ከፍታ ላይ ወጥቻለሁ፣ አመዴ ተራገፈ፣ ጌታ ለኔ አደላልኝ፣ የእኔ ከማንኛችሁም ይበልጣል ልዩ ነው . . . ወዘተ የጠገብናቸው ድግምቶች ናቸው:: ታዲያ ደረጀ እነዚህን እኔ፣ እኔ፣ እኔና እኔ ብቻ የሚሉ ጆሮ አታካች "ክሊሼዎቻችንን"፣ እንዲደግምልን ይሆን የምንጠብቀው?"* ብሎአል። ክሊሼ አዲስነት የጎደለው ድግግሞሽ ወይም ድግምት ነው። አዲስነት ቀድሞውኑ አልቆ መዝሙሩን በቁሙ እንዳለ መድገሙ ደግሞ ቡትቶ መጎተት እንዳይመስል።

ከፈር ቀዳጅነት መጥፋት ጋር የአዲስ ዘይቤ ወይም አዲስ ስልት ጀማሪነት እጦትም ይያያዛል። የይዘት ቅለትና ግድፈትም በጉልህ ይታያል። የይዘትን ግድፈቶች ኋላ አነሳለሁ፤ የይዘቱን ቀላልነት በመሣሪያ ድምጽ ጉልህነትና ብዛት ለመሸፈን የሚደረግ ግብግብም ቀላል አለመሆኑ ሊወሳ ይገባል። 10 በ20 ሜትር መሰብሰቢያ ውስጥ ለትልቅ እስቴዲየም የሚበቃ ድምጽ ማጉያ እስከ ክፈፉ ተከፍቶ የጆሮ ታምቡር መጠለዙና መልእክቱ በጩኸት መጀቦኑ በአብዛኛው የሚያመለክተው በዝማሬው ውስጥ መልእክት አለመኖሩን ነው። ቢኖርና እንዲተላለፍ

የተፈለገው ያ ቢሆንማ ኖሮ ሙሉው ጉልበት በስሜት ላይ ከሚፈስስበት ከመሣሪያው፥ ከጩኸትና ዝላዩ፥ ከመጨፈርና ከመጎድፈሩ ቀነስ አድርጎ ወደ ልብ ለሚገባው ቦታ በተሰጠው ነበር!

## ለ) የዜማ ድግግሞሽ

በዚህም ዝግጅት እንዳለፈው ጥቂት ናሙና መዝሙሮችን ስሕተቶች ለማየትና ለማሳየት እፈልጋለሁ። በጣም ጥቃቅን የሚመስሉ ስሕተቶች ናቸው በጣም ውብ የሆኑ መዝሙሮችን እንዲወርዱ የሚያደርጉት። አንርሳ፤ አንድ ትንሽ ትል ነው ትልቁን ዱባ የሚያበላሸው። መዝሙሮቹን በተመለከተ በዘማሪዎቹ ላይ የሚያያተኩሩ ሳይሆኑ እንዳለፈው ሁሉ በአጋጣሚ ሳደምጣቸው ያገኘኋቸውና የሰበሰብኳቸው ናቸው። በቃል የጠቀስኳቸውም ስጽፍ ያስታወስኳቸው ናቸው። ባለፈው ስርጭት እንዳወሳሁት አንዳንድ ዜማዎች መቀራረብ ይታይባቸዋል። የማጀቢያው መሳሪያ ዜማማ በጣም ይመሳሰላል። ያ የመሳሪያና የአጨዋወት መወራረስ ነውና ይሁን እንበል፤ ግን የአዝማች ወይም የቁጥሮች ወይም የሁለቱም መመሳሰል ለሰሚው ጥያቄ ይፈጥራል። ጥያቄው በጎሊና ውስጥ ተቀመጥ ቢሉት እሺ የማይል ሊሆን ይችላል። የተተረጎመ መዝሙር ከሆነና አንዱ መተርጎምና መዘመሩን ሌላው ሳያውቅ ዘምሮ አሳትሞ ከሆነ ደህና፤ ሳያውቅ ነው ይባላል። ካልሆነ ግን የአድማጩ ጥያቄ እየተንቀዋለለ ሊኖር ነው። ከሰማኋቸው የተወሰኑ መዝሙሮች ያደመጥኳቸውን ሁለት ተመሳሳይ ዜማዎች እነሆ፤

ይክበር እንላለን ለዘላለም እና አ ፍቅሩ ሁል ጊዜ፤

እንቅልፍ ወስዶኝ አንድ ሌሊት እና ጌታ የሱስ ትዝ አልከኝ

ዜማቸው አንድ ነው። በአንድ ዜማ ሁለት መዝሙር መዘመር በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ መግደል አይመስለኝም። እንዲያውም በሁለት ድንጋይ አንድዋን ወፍ መጨፍለቅ ሳይሆን አይቀርም።

የአንዳንድ መዝሙሮች ዜማ ጭራሽ ከዘፈን የተወሰደ ነው ተብሎ የቀረቡ ሂሶችን አንብቤአለሁ። ተደርጎ ከሆነ ይህ ነውር ነው። ምነው? የዜማ ምንጭ ነጠፈ? ደረቀ? ለምን ከዘፈን? ለምንስ ለተረብ መጋለጥ ተፈለገ? አንድ ቀን ታክሲ ውስጥ ሆኜ አንድ ዘፈን ሰማሁ፤ የአገኘሁ

አንድ ቀን ጌታዬን አየዋለሁ

መዝሙር ዜማ በዘፈን ሆኖ ነው። ዘፋኙ የአዝማቹንም የቁጥሩንም ዜማ ሳይለውጥ፥

አንድ ቀን ባካል ባይነ ሥጋ አየሁኝ አብረን ስናወጋ

እያለ ዘፈነ። ዘፋኙ እንደኮረጀ መረጋገጡን ሰምቻለሁ። ዱሮ ዩኒቨርሲቲ (አሥመራ) ሳለሁ በተማሪዎች መኖሪያ ግቢያችን አጠገብ ካለ አንድ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በድምጽ ማጉያ መዝሙር ሰማሁ። ዜማው ምንም ሳይለወጥ የዘሚል ጎራዴው ዜማ ነው። አንድ አብረን የምንማር ጓደኛዬን ጠራሁና፥ "ስማ ይህን መዝሙር፤ ዜማውን ከዘፈን ነው የወሰዱት" አልኩት። እርሱም፥ " ዘፈኑ ይሆናል የወሰደው እንጂ ይህ መዝሙር ከኔ መወለድ በፊትም የነበረ ነው" አለኝ። እንደዚያ ከሆነ እውነትም ዘፈኑ ነበር የወሰደው። ዘፋኞች ወይም ዓለማውያን ቢሰርቁ አይገርመን ይሆናል፤ ቢሆንም ነውር ነው። የመዝሙሮች ዜማ መወራረስና መቀያየጥ አሁን አሁን ከሚወጡት አዳዲስ መዝሙሮች ጥቂት ያልሆኑትን ለመጀመሪያ ጊዜ ስንሰማ ለመጀመሪያ ጊዜ እየሰማን እንደሆነ እያወቅንም፥ "ይህን መዝሙር የት ነው የሰማሁት?" ብለን እንጠይቃለን። የሚከፋው ደግሞ የተሰማው ዜማ የመዝሙር ሳይሆን የዘፈን ሲሆን ነው።

ተዉኝማ የሚለው መዝሙርና ማን እንደናት፤ የሚለው ዘፈን እንዲሁም

ወደሚረዳኝ አምላክ የሚለው መዝሙርና ኡኡታ አያስከፋም የሚለው ዘፈን

ዜማዎች ተቀራራቢ ሳይሆኑ ተመሳሳይ ናቸው። ይህ የሚያመለክተው ዘማሪዎች ዜማቸውን ለመቅዳት ወደ ዘፈን ወንዝ መውረዳቸውን ነው። ቀጥሎ ቃላቱንም እንዳይቀዱ ይህ አዝማሚያ መቀጨት አለበት። እነዚህ ሲዲዎች ላይ ከናሙናዎቹ በላይ ነው የዘፈን ዜማ ያላቸው መዝሙሮች የተደመጡት። ሆን ተብሎ ከዘፈን ተወስዶ ከሆነ አሳፋሪ ነው። ካልሆነ ደግሞ አእምሮአችን የሰማውን ዜማም ይሁን ሌላ ነገር ደብቆ የማስቀመጥ ተፈጥሮ አለው። ታዲያ መዝሙር ስንደርስ ያ የተደበቀ ዜማ ብቅ ካለ እኛ የደረስነው ይመስለናል። አንዴ አንድ መዝሙር ለመዘምራን ቡድናችን አቅርቤ ተለማምደን ከጨረስን በኋላ አንዲት እኅት ያ መዝሙር ከአንድ የወላይታ ዜማ ጋር ፍጹም አንድ መሆኑን ነገረችኝ። መዝሙር ይሁን ዘፈን አላስታውስም። እኔ ሳዘጋጅ በጣም እርግጠኛ ነበርኩ የራሴ ለመሆኑ። ግን አልነበረም ማለት ነው። በስንፍና ወይም በድርቅና "የራሴ ነው ደርሼዋለሁ እንዘምረዋለን" ብል ቅሌት ይሆን ነበር።

## ሐ) የንባብ ግድፈቶች

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ያለባቸው መዝሙሮች የሚያነብቡትን ክፍል በጥንቃቄ ማንበብ ይገባቸዋል። ከዓመታት በፊት የሰማሁት አንድ የመዝሙር ካሴት ላይ የሚነበቡ ምንባቦች አሉበት። አንዱ ክፍለ ምንባብ ማቴ.7፥21-23 ሲሆን መጨረሻው ላይ ያለው ጥቅስ፥

*የዚያን ጊዜም ከቶ አላውቃችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ*

ተብሎ ነበር የተነበበው። ቃሉ የሚለው ግን፥ የዚያን ጊዜም፥ ከቶ አላወቅኋችሁም ነው። አላውቃችሁምና አላወቅኋችሁም የተለያዩ ናቸው። አላውቃችሁም በዚያን ጊዜ ነው። አላወቅኋችሁም ግን ቀድሞም ነው። የተለያዩ ባይሆኑስ እንኳ ለምን ይለወጣል? የሚነበበው የተደረሰ ከሆነ ደህና፤ ካልሆነ ግን ቃሉን ገምዶ ማንበብ ተገቢ አይደለም።

አንድ መዝሙር ላይ ደግሞ ማቴ. 11፥28

እናንት ደካሞች ሸክም የከበዳችሁ

ተብሎ ተነብቦአል። ይህ መዝሙር ልነካቸው ከማልፈልጋቸው መዝሙሮች አንዱና ግሩም የመስቀሉ መወድስ ነው፤ ግን መነካት ኖረበት። ቃሉ ግን እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ይላል። እንዲሁ ስንገረምመው ምንም ልዩነት የሌለው ይመስላል። ስናጤነውና ስናጠናው ግን ሸክም የከበዳችሁ እና ሸክማችሁ የከበደ ልዩነት አላቸው። እንዲያው ባይኖረውስ? የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል በአንድ አንባቢ ንባብ ለምን ይለወጣል?

## መ) የይዘት ግድፈቶች

የተጻፈውን አጣምሞ ወይም አወላግዶ ማንበብ ብቻ ሳይሆን ያልተጻፈውንና ጌታ ያላለውን "አለ" ብሎ መዘመርም በበርካታ ዘማሪዎች ተሰምቶአል። ለምሳሌ፥

አለሁ አለ ጌታ አለሁ አለ. . .

ዘማሪው አንድ ቦታ "እኔን የጨነቀኝ ኢየሱስ ምን አለ?" ይላል። ኢየሱስ ምን እንዳለ ሳያውቅ ቀርቶ የሚጠይቅ ይመስላል። ግን ምን እንዳለ ደግሞ አውቆአልና በአዝማቹ ውስጥ ደጋግሞ ኢየሱስ "አለሁ አለ" ይላል። በአዝማቹ ውስጥ ደግሞ ኢየሱስ የሚለው ነገር በየዓመቱ የሚለያይ ይመስል፥ "ዘንድሮስ ምን አለ?" ብሎ ይጠይቃል። እርሱ ኢየሱስ ያላለውን እንደዘመረ ሌላውም ያላለውን ሌላ ነገር እንዲዘምር የሚጋብዝ ይመስላል። "እርሱ ያላለውን እንደዘመረ" ያልኩት ኢየሱስ አለሁ ስላላለ ወይም ብሎ ስላልተናገረ ነው። እዚህ መዝሙር ውስጥ ዘማሪውና አጃቢዋ ከ60 ጊዜ በላይ የተደጋገመ "አለሁ አለ" የሚል ሐረግ ዘምረዋል። ጌታ በዮሐ. 8 "አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ" ያለበት አንድ ስፍራ አለ። ይህ ከአብርሃም በፊት የነበረ ከጥንት ዘላለማዊ መሆኑን ነው እንጂ እግዚአብሔር የለም ለሚል ክህደት የሰጠው ምላሽ አይደለም። "አለ" ማለት ተናገረ ማለት ነው። እንደምገምተው ዘማሪው መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን ሰባኪ ወይም ነቢይ ነኝ ባይ የተናገረውን መዘመሩ ካልሆነ በቀር ጌታ ኀልውናውን ማሳወቁን ወይም "የለም" ሲባል አሁንም መኖሩን ማሳየቱን መዘመሩ ይመስለኛል። ግን ያንን ለማድረግ ጌታ ያልተናገረውንና በቃሉ ያልተጻፈውን "እንዲህ ተናገረ፤ እንዲህ አለ" ብሎ

መዘመር አግባብ ነው? ያላለውን "አለ" ብሎ ከሚዘምር ያንን ሳይል ጎልውናውን ማረጋገጡን፥ በቃልም በተግባርም ማሳየቱን መዘመር አይችልም ኖሮአል? የዘመረው አሳብ ያ መሆኑ ይታያል።

አንዳንድ መዝሙሮችን ከሰው ወይም ከጉባኤ ስሰማ "መጀመሪያ ከዘማሪው ወይም ከካሴቱ ሲሰሙ ተሳስተው ሰምተው ያንን እየደገሙ መሆን አለበት እንጂ እንደዚህ ተብሎስ አይዘመርም" ብሎ መወራረድ ያምረኛል። አንድ ጓደኛዬ፥ ዛሬማ ሰው ሆኜ ቀስት እገትራለሁ / ዛሬማ ሰው ሆኜ ገስ ገስ እላለሁ ብሎ ነበር። ያው ጓደኛዬ ኮሌጅ በነበርን ጊዜ የአንድ ቡድን መዘምራንን የመዝሙር ደብተር ወስዶ ሲያገላብጥ፥ ይመጣል ጌታችን ካገልጋዮች ጋራ የሚለውን ይመጣል ጌታችን ካድር ባዮች ጋራ፤ መሠረቴ ጠብቆ ብጓዝ እወዳለሁ የሚለውን መሠረቴ ጠልቆ ጉድጓድ እወርዳለሁ፤ ከፈርዖን ጮማ ለኔስ መናህ ይጥመኛል የሚለውን ከበሬውም ጮማ እያሉ ጽፈዋል። እነዚህ ልጆች አማርኛ የመጀመሪያ ቋንቋቸው ስላልሆነ ሲሰሙ ነው ለማጤን የተቸገሩት፤ አንዳንድ መዝሙሮች ግን ሲደመጡ ብቻ ሳይሆን በእርግጥም የተሳሳቱ ናቸው።

እድለኛ ነኝ. . . በመስቀል ላይ ሆኖ ስለኔ አልቅሶ አድኖኛል ጌታ ዕዳዬን ሰርዞ

ጌታ በመስቀል ላይ ሆኖ ኃጢአታችንን ተሸክሞ ስቃይን ስለኛ መቀበሉ እውነት ነው። ግን አልቅሶ ነበር? በሥጋው ወራት ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን ማቅረቡ ተጽፎአል። በመስቀል ላይ ማልቀሱ ግን አልተጻፈም። ይልቅስ በመስቀል ላይ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ ተብሎ ነው የተጻፈልን። ለምንድርነው በዘማሪው ያልተጻፈው እንደተጻፈ ተደርጎ የተዘመረው? አልቅሶስ ቢሆን? ያዳነን ልቅሶው ነው? ይህ ያልተጻፈውን እንደተጻፈና የተጻፈውን እንደወደዱ ጠምዝዞ መዘመርና ማንበብ በዝምታ ከታለፈ መድረሻው እምን ይሆን? እድለኛ ነኝ ማለትስ መዳናችንን ሎተሪ አያስመስለውም? ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በፍቅር መመረጣችንና የማያምኑ ሰዎች እድል፥ እድለኛ፥ የታደለ የሚሉት ነገሮች የተለያዩ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እድል ወይም ፈንታ ሲል ድርሻንና በረከትን መናገሩ እንጂ ለማንም ሊደርስ እንደሚችል እንደ ዕጣ ወይም ሎተሪ ያለ ነገር አይደለም።

የሲዖል ደጅ በርሱ ተዘግቷል

መቼ ነው የሲዖል ደጅ የተዘጋው? ይህ ከየት የመጣ ትምህርት ነው? ከሆነ ሰው ወደ ሲዖል መሄዱ አብቅቷላ! እንዲህ የመሰለው መዝሙርና ትምህርት ተግባራዊ ተጽእኖም አለው። ለምሳሌ፥ እንደዚያ ከሆነ፥ ማለትም፥ የሲዖል ደጅ ከተዘጋ ማንም ወደዚያ የሚሄድ የለምና ወንጌል መስበክና ስለ ጌታ መመስከር አያስፈልግማ?! ሌላ ምሳሌ ብንወስድ

ተባረረ ካገር ተባረረ

ካልን ሰይጣን ተባርሮአልና፥ በአገር ውስጥ የለምና እርሱ ከእኛ እንዲርቅ ሰይጣንን መቃወም የለብንማ! በክፉው ቀን ፈጽመን ለመቆም እንድንችል ዕቃ ጦራችንን ማንሣት የለብንማ! በኤፌ.6 በኃይሉና በችሎቱ እንድንበረታና እንድንጋደል እንጂ አባርረነው ጋሻ ጦራችንን ሰቅለን እንድንቀመጥ አልተነገረንም። ሰይጣን እንኳን እኛን ቀላል ዒላማዎቹን ይቅርና ቃሉ እንደሚለው ጌታችንንም እንኳ ፈትኖ "ፈተናውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ እስከ ጊዜው ከእርሱ ተለየ" ነው የሚለው። በማባረር መገላገል ካለማ እጥግ ድረስ አብርሮ በሰላም መኖር ለምን አልተቻለም? መዝሙሮችን እንዲያው በሸፋናቸው ብቻ ከተቀበልናቸው እንወናበዳለን።

እጅና እግሩን ጎኑን በጦር የተወጋው እጅና እግሬ ሰውነቴ ጤነኛ እንዲሆን ነው

እውነት ኢየሱስ እጅና እግሩን ጎኑን በጦር ተወግቶ ነበር? ቃሉ እንደሚለው ጎኑ ነው በጦር የተወጋው፤ ለዚያውም ከሞተ በኋላና መሞቱ የተረጋገጠበትን መወጋት ነው የተወጋው። ደግሞስ የተወጋው እጅና እግራችን እና ሰውነታችን ጤነኛ እንዲሆን ነው? እጅና እግራችንና ሰውነታችን ጤነኛ እንዲሆን እኮ ኢየሱስ በመስቀል ላይ መዋል አልነበረበትም። በመስቀል ላይ ሳይውልም ቀድሞ ፈውሶአል፥ ጤና መልሶአል፥ ከሞትም ሳይቀር አስነስቶአል። እነዚህን ነገሮች ለማድረግ በመስቀል ላይ መዋል አላስፈለገውም። አንድ ነገር ለማድረግ ግን በመስቀል ላይ መሞት ነበረበት። የመጣውም ያንን ለመፈጸም ነው። ያም፥ የኛን ኃጢአት በመስቀሉ ላይ መሸከምና ቤዛነታችንን መክፈል ነው። የመስቀሉን ገድል ከዚያ ላነሰ ነገር መለወጥ እውነትን በርካሽ መመንዘርና ቃሉን መሸቃቀጥ ነው። ይህ ፈጽሞ መታለፍ የሌለበት የስሕተት ትምህርት ነው።

የሰማይ የምድሩ ፈጠራ ባለቤት የፈጠራ ሥራው

ይህ ዘማሪ የእግዚአብሔርን የፍጥረት ወይም የፈጣሪነት ሥራ የፈጠራ ሥራ ይለዋል። ዘማሪ የሆነ ሰው ከስነ ጽሑፍና ከዚያ ከተያያዘው ከባቢ ደብዛው የራቀ መሆን የለበትም። ፈጠራ ማለት አፈጣጠር ወይም ፍጥረት ሳይሆን ውሸት ማለት ነው፤ የተሻለውና ከስነ ጽሑፍ ሥራ ጋር የተያያዘ ትርጉሙ ደግሞ ልብ ወለድ ማለት ነው። በዘፍ. 1 የሚታየው ፈጠራ ሳይሆን ፍጥረት ነው። ከነስሙም መጽሐፉ ራሱ ኦሪት ዘፍጥረት ነው እንጂ ኦሪት ዘፈጠራ አይደለም።

ጌታ እኮ ነው የሚያሸልለኝ፥ የሚያዘንጠኝ፥ ያንቀባረረኝ ላመስግነው ለቀቅ አድርጉኝ

ቋንቋና ቃላት መዝሙሮቻችንን ከቡራን የሚያደርጉትን ያህል ቀላልና ገለባም ያደርጓቸዋል። ደግሞ የዘማሪውን ሕይወትም የሚያንጸባርቁ ናቸው። መሸለል፥ መዘነጥ፥ መንቀባረር የልብስና የጌጣ ጌጥ፥ የአዱኛ ቃላት ናቸው። ደግሞም ከትኅትና የራቀ ባህርይ ቃላት ናቸው። ትሑት ሰው አይንቀባረርማ። የሚያሳዝነው ይህንን የሚያደርገው ጌታ እንደሆነ ሲነገር ነው። በእውነቱ ክርስቲያን ሊለብስ መጣር ያለበት ሌላ ልብስ ነው፤ *እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ፥ ምሕረትን፥ ርኅራኄን፥ ቸርነትን፥ ትህትናን፥ የዋህነትን፥ ትዕግሥትን ልበሱ። በእነዚህም ሁሉ ላይ የፍጻሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን*

ልበሱት። ይላል ቃሉ፤ ቆላ. 3፥12፥14። በአምባርና በጉትቻ፥ በጫማና በከረባት ዘንጠን ጌታ አንቀባረረኝ ማለት ጌታን ከማወደስ ይልቅ ቀብራራነታችንን በአደባባይ ማወጃችን ነው። ጌታ ከመልካም ነገር ልጆቹን አያጎድልም፤ መልካም ነገር ደግሞ በመሸለልና በመዘነጥ አይሰፈርም። ክርስትና በልብስና በንብረት ተለክቶ መነሣትም መውደቅም የለበትም። ብዙ ዘማሪዎች ጌታ አከበረኝ፥ አኮራኝ፥ ሰው አደረገኝ ሲሉ ያንን ማለታቸው ነው። ጌታ ሲያድነን ሰው አይደለም ያደረገን፤ ሰውማ ነበርን፤ ከእጦት ወደ አዱኛ መምጣታቸውን መዘመራቸው ካልሆነ በቀር። ከሆነ ደግሞ ሰው መሆንን በመልበስና በገንዘብ ብቻ ከለኩ መሠረታዊ የአመለካከት ሽንቁር አለባቸው። ጌታ ሲያድነን ሰው ሳይሆን ልጆቹ ነው ያደረገን፤ ያ ልጅነትና የልጅነት ሥልጣን ቢዘመር ውብ ነበር። ያ የልጅነት ሥልጣን መንቀባረርና መዘነጥና መሸለል አይደለም። መልበስ ተገቢ ነው እንጂ ልብሳችን መታወቂያችን መሆን የለበትም። ለኛ እውነተኛ በላጭነታችን ክርስቶስን መልበሳችን ነው። ያለዚያማ ከኛ የተሻለ የሚለብሱት ሊበልጡን ነው ማለት! ወይም እንደነሱ እስክንሸቆጠቆጥ ድረስ ገና ቀረኝ ልንልና ባለን ከማመስገን ይልቅ በሌለን ልናጉረመርም ነው!

ማዕረጌ ነህ

ማዕረግ ማለት እንደ ባላምባራስ ወይም ደጃዝማች ወይም እንደ ሻምበል ወይም ኮሎኔል ያለ ከበላይ የሚለገስ ወይም በጀብድና በአገልግሎት የሚያገኙት ክብርና ሥልጣን ነው። ኢየሱስ እንዴት ሆኖ ነው ማዕረግነቱ? አሁን አሁን ኢየሱስ የሚሆነው ሳይሆን የማይሆነው ነገር እየጠፋ ነው የመጣው። በቃሉ ውስጥ የማናገኛቸው አዛውንቶች ልጆቻቸውን የሚመርቁባቸው ወይም ጓደኞች አድናቆታቸውን የሚገልጡባቸው ቃላት በኢየሱስ ላይ እየተለጠፉ ናቸው።

መልኬ ደም ግባቴ ጌጤ ነህ ውበቴ

ወጌ፥ ማዕረጌ፥ ሹመቴ፥ ውበቴ፥ መደምደሚያዬ፥ ደስታዬ፥ ኩራቴ፥ ትምክህቴ፥ ወንድም ጋሼ፥ ምስጢረኛዬ፥ ምስጋናዬ፥ ወዘተ፥ እነዚህ እኛ የፈጠርናቸው ቅጥያዎች ናቸው እንጂ በቃሉ ውስጥ የምናገኛቸው አይደሉም። ይህንን ቅጥያ ለመጨመር ሥልጣኑ አለን? ደግሞም እነዚህ ሁሉ ነገሮች እንኳን በነጠላ አንድ ላይ ቢጨፈለቁም አንዱን የጌታን ማዕረግ አይተኩም። ባለፈው ስርጭት ለሰው የሚሆኑ ማሞገሻዎችን ለጌታ መጠቀም፥ ለምሳሌ፥ ጌታን ጀግና ማለት፥ ጌታን ከፍ ሳይሆን ዝቅ ማድረግ መሆኑን አውስቼ ነበር። ለሰው የሚሆኑ ማቆላመጫዎችንም ለጌታ መጠቀም ከውዳሴ የወረደ እንጂ የተስተካከለ አይደለም። አንዳንድ መዝሙሮች በእውነቱ አዝማሪ በፌውዳል ወይም ከበርቴ ፊት ቆሞ የሚያዜመው ነው የሚመስሉት። በልማዳዊው አባባል ከሄድን የምናቆላምጠው እኩያና ጓደኞቻችንን ነው። የሚበልጡንን በአክብሮት ነው የምንቀርበው፤ ካቆላመጥናቸው የሸነገልናቸው ብቻ ሳይሆን እንዲያውም እኩያ አድርገን ያዋረድናቸው ነው የሚመስለው፤ ለራሳቸውም ለሰሚዎችም። እስኪ የምናውቀውን አንድ መሪ የሆነ ሰው በምናባችን እንደምናነጋግረው አስበን የዚያ ዓይነት ቃል እንጠቀም። አይመችም። አንቀጥልም። በየትኛውም ወግም ሆነ ግንኙነት ይህ አይደረግም።

ውድዬ ይክበር፥ ጌትዬ ይክበር

ካህንዬ፥ ንጉሥዬ፥ አባብዬ፥ ጌትዬ፥ ኢየሱስዬ፥ ወዘተ፥ ስንል ያንን ማድረጋችን ነው። ጌትዬኮ የጌታቸው፥ የጌታሁን ወይም የጌታ መሳይ ማቆላመጫ ነው፤ የጌታ አይደለም። ካደረግነው ጌታ ማዕረጉ ነው እንጂ ስሙ አይደለም፤ ማዕረግ ደግሞ አይቆላመጥም። በኔ ግምት እነዚህ ዘማሪዎች የተለመዱ ቃላትን ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ጋር ይስማሙም ይጣሉም ስለተለመዱ ብቻ የሚጠቀሙባቸው ይመስለኛል። ለምሳሌ፥ ጣልቃ መግባት ምንድርነው?

ጣልቃ እየገባ

እግዚአብሔር እኛ ወገኑ፥ ልጆቹ ከሆንን በኋላ ጥበቃና ክብካቤ ያደርግልናል እንጂ ጣልቃ አይገባም። ጣልቃ መግባትና ጥበቃና ምሪት አንድ አይደሉም። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ጣልቃ መግባቱ አልተጻፈም፤ አንዴም። ጣልቃ መግባት ወይም ጣልቃ ገብነት በወጥ ትርጉሙ በሁለት ችግር በሌለባቸው ወገኖች መካከል ሳይፈለጉና ሳይጋበዙ ጥሩ ላልሆነ ግብ ጥልቅ ማለት ነው። እግዚአብሔር ይህን አያደርግም። ዘማሪዎች ቃልን ከተጠቀሙና ቃል ደግሞ ትርጉም ከኖረው ትክክለኛና ተገቢውን ትርጉም ሊመርጡ ግዴታ አለባቸው።

ዘማሪዎቻችን አሁን ባወጡት ካሴት ኢየሱስዬ፥ ካህንዬ፥ አባብዬ፥ ጌትዬ ካሉ በቀጣዩ ኢየሱስሻ ወይም ጌትሽ እንዳይሉ ያስፈራል። የዚህ ችግር ቃሉ ብቻ አይደለም። ግንኙነቱም ነው። አንዳንዶች ጌታን የቆሎ ጓደኛና የችርቻሮአቸው ሸርክ የሚያደርጉት ከሚሰጡት ስፍራና ከግምታቸው ካላቸው ግንኙነት የተነሣ ነው። አጠራራችን ግንኙነታችንን እንደሚገልጠው ወይም ቀረቤታችንን እንደሚመድበው የታወቀ ነው። ይህንን አንዘንጋ። ለምሳሌ ጌታ ማዕረጋችን ከሆነ ማዕረጉ ከባለማዕረጉ እንደማይበልጥ የታወቀ ነው። ዝርግፍ ጌጤ ነው ኢየሱስ ካለ፤ ዘማሪው ባለጌጡ ኢየሱስ ጌጡ ናቸው። እኛን ባለጌጥ ኢየሱስን ጌጥ፥ እኛን ባለማዕረግ፥ ኢየሱስን ማዕረግ አድርጎ መዘመር ራስን ማግዘፍ ነው፤ ነውር ነው። ስለዚህ ቋንቋችን መደብና ደረጃ ሊኖረው ይገባል።

ካህኔ እንደ መልከ ጼዴቅ

ክርስቶስ ካህን ነው? እርግጥ ዕብ. 7 ውስጥ ከመልከ ጼዴቅ ጋር ሲያነጻጽረው አሮናዊ ያልሆነና ዘላለማዊ የሆነ ክህነቱን ይናገራል፤ ግን ከካህናት ተርታ የሆነ ካህን መሆኑን ሳይሆን የክህነቱን ዓይነት ለመናገር ነው ካህን ያለው። በዚያው መጽሐፍና በሌሎችም ስፍራዎች በግልጽ የሚያስተምረው ዋና ትምህርት ግን ኢየሱስ ካህን ሳይሆን ሊቀ ካህናት መሆኑን ነው። እኛ ነን ካህናት፤ የንጉሥ ካህናት። ከሆነው ኹነት፥ ከእርሱነቱ የገለጥነው እየመሰለን ለምን እናውርደው?

የቅርብ ዘመዴ ነው ለኔ የሞተልኝ ዋርሳዬ የምለው

በመዝገበ ቃላት ትርጉሙ ዋርሳ ወራሲ፥ ወራሽ፥ የሚወርስ ማለት ነው [ኪወክ ገጽ 405]። በዘዳ. 25 እና በመጽሐፈ ሩትም እንደተጠቀሰው ትርጉሙ ያው ሆኖ የባል ወንድም ወይም የባል የቅርብ ዘመድ፥ ባሏ የሞተባትን ሚስት የሚወርስ ማለት ነው። ዘዳ. 25፥7-9 ሴቲቱንም ዋርሳ ያሰኛል፤ ይህኛው ቃል በአማርኛው እንጂ በዕብራይስጡ ዋርሳ ሳይሆን የወንድም ሚስት ማለት ነው። በሩት መጽሐፍ ያለው ቃል ቃሉ የወጣው መቤዠት ወይም መታደግ ከሚለው ግስ ቢሆንም የወንድሙን ንብረት የሚከላከል የሚቤዥ የባል የቅርብ ዘመድና ወራሽ ማለት ነው። ይህ ዘማሪ ኢየሱስን ነው ዋርሳዬ የሚለው። እንዴት ሆኖና በምን በኩል ኢየሱስ ዋርሳው ወይም ወራሹ የሆነው? እንዴትስ ነው እርሱ አውራሽ የሚሆነው? የምናወርሰውስ የትኛው ጢንጦአችንን ይሆን? ይህ የማይገባና ግራ የሆነ ነገር ነው። ጌታችን ኢየሱስ ቤዛችንና ታዳጊያችን ስለሆነ ዋርሳችን ማለት አለብን? አንድ ዘማሪ ኢየሱስን የጦር አበጋዝ ያደርገዋል።

የጦር አበጋዜን የሱሴን ሾሜአለሁ

በልማዳዊ ትርጉሙ የጦር አበጋዝ ማለት ከዋና የጦር አዛዥና ከአዝማች በታች የሆነ የጦር አለቃ ነው። ኢየሱስ ይህ የበታች አለቃ ነው ማለቱ ይሆን ይህ ዘማሪ? ከሆነ ኢየሱስ ከየትኛው አዛዥና አዝማች በታች ያለ አበጋዝ ይሆን? ዘማሪዎች የሚዘምሩበትን ቃል እርግጠኛ ሆነው ሳያውቁት ለምን እንደሚዘምሩበት ወይም ለምን ሊያውቁት እንደማይሞክሩ አይገባኝም። ቢሞክሩ እኮ ያገኙት ነበር ትርጉሙን።

መሰለውና ተንጎራደደ እኔ ነኝ ብቁ ብሎ ፈረደ

ስለ ሳኦል የተዘመረ ነው። ግን አሳቡ ከየት እንደተገኘ አይታወቅም። ግምት ይሆን? ከሲኒማ የታየ ይሆን? አንድ ፊልም ላይ ሳኦል ሊነግሥ መንጎራደድ ብቻ ሳይሆን ከዚያም ያለፈ አድርጎ ነበር፤ ይህ ግን በሰው የተደረሰ ፊልም እንጂ በመንፈስ ቅዱስ የተጻፈ ቃሉ አይደለም። በቃሉ እንደተጻፈው ግን ሳኦል እንኳን ሊንጎራደድ በዕቃ መካከል ከተሸሸገበት ነው ተፈልጎ ወጥቶ የመጣው።

አንድ መዝሙር ውስጥ

ሚሊኒየም፥ የሉሲ ልደት፥ ካላንደር፥ አጎዝ፥ አቡጊዳ ሄውዞ

የሚሉ ቃላት ተዘምረዋል። ስለ 2ሺህ ዓመተ ምሕረት የተዘመረ ነው ግን ቃላቱ የመዝሙር ሳይሆኑ የተራ ጨዋታና የወሬ ናቸው። ኢየሱስና ኢትዮጵያ ሊተላለፉ እንደሆነ አስቦ ፈርቶአል ዘማሪው። ሚሌኒየምና መድኃኔዓለምና ኢትዮጵያ መቼ ነው ቀጠሮ የያዙት? ሉሲ ማንናት? 2ሺህ ዓመቷ ነው? የሉሲ ልደት ነው ተብሎ ኖሯል? ቢባልስ? አንዳንድ መዝሙሮች ከይዘታቸው አንጻር ሲታዩ መደረሳቸው ይገርማል። መዘመራቸው ደግሞ ጉድ ነው። አንድ መጽሔት ላይ ቃላት አጣን፥ ቃላት ባገኙሁና፥ ወዘተ፥ ለሚሉ ዘማሪዎች ጳውሎስ ፈቃዱ፥ "ቃል

ካለቀባችሁ ወይ በቁጥር ዘምሩዋ!" ብሎ ነበር። አቡጊዳሄውዘና ሉሲም ቃላት ሆነው ከተዘመሩ ቃላት አያልቁም ማለት ነው፤ መልእክት የለም እንጂ!

አንድ ሁለት መዝሙሮች ውስጥ

*አማኑኤል አማኑኤል ሆይ፥ የክንፍህ መዘርጋት የአገሪቱ ስፋት ትሞላለች*

ተብሎ ተዘምሮአል። እዚህ የክንፉ መዘርጋት የተባለው የኢየሱስን ነው። ቃሉ በተጻፈበት ስፍራ ግን የአማኑኤልን ክንፍ ሳይሆን ለአማኑኤል ነው። የክንፉ መዘርጋት የተባለው የአሦርን ንጉሥና ሠራዊቱን ነው። ሠራዊቱ ጎርፎ በፍጥነት መምጣቱን፥ ብዛቱ አገሪቱን መሙላቱን ነው። *እየጐረፈም ወደ ይሁዳ ይገባል እያጥለቀለቀም ያልፋል፥ እስከ አንገትም ይደርሳል፤ አማኑኤል ሆይ፥ የክንፉ መዘርጋት የአገርህን ስፋት ትሞላለች፤* ኢሳ. 8፥8።

*የኢየሱስ ቁንጅና፥ የውዴ ጠረን፥ መዓዛህን እወደዋለሁ፥ ወዘተ፥*

ዘማሪዎቻችን የኢየሱስን አካላዊ የቁንጅና መግለጫዎችን ሲጽፉ ሰዓሊ ሆነው እፊታቸው የተቀመጠ ያስመስሉታል። ምን እያዩ ይሆን ቁንጅናውን የደረሱት? ሰዓሊዎች የሳሉትን? ወይስ በምናባቸው ያዩትን? ወይስ በወንጌላት የተጻፈውን? በመዝሙረ ዳዊት መሢሐዊ መዝሙሮች የተሰኙ ጥቂት ምዕራፎች አሉ፤ ከዚያ? ለምሳሌ፥ መዝ. 45 ከክርስቶስ ማንነት ጋር ሊገናዘብ ይችል ይሆናል፤ በአዲስ ኪዳንም ከዚህ መዝሙር ስለ ክርስቶስ ዘላለማዊ መንግሥት የተመለከተ ሐረግ ተመዝዞአል። አካላዊ ቁንጅናን ግን አይደለም። ከነቢያትም ስለ መልክ ትንሽ ኢሳይያስ ነው የጻፈልን፤ እርሱም፥ ባየነውም ጊዜ መልክና ውበት የለውም ነው ያለን። በወንጌላት ውስጥ በዓይን ያዩትም ሲተርኩልን ምንም አልጻፉም ስለ ቁንጅናው። በራእይም ውበትና ቁንጅናው አልተጻፈም ክብርና ግርማው እንጂ። ዘማሪዎቹ ምን እያዩ ይሆን ቁንጅናውን የደረሱት? ጠረኑንስ ከየት አሽትተው ይሆን የዘመሩት? እንደ አገልጋይ መርሳት ከሌለብን ነገሮች አንዱ መጽሐፍ ቅዱስ ዝም ባለባቸው ቦታዎችና ጉዳዮች ዝምታውን ማክበርን ነው። ዝምታውን በራሳችን ምናብ እየጠቀጠቅን መሙላት ነውር ብቻ አይደለም፤ ኃጢአት ነው። ይህ በቃሉ ውስጥ የሌለ ሌላ ነገር መጨመር ነው። በዜማ መቅረቡ በስብከት ከመተላለፉ ቀላል አያደርገውም።

ኤልዛቤልን ውሾች ይበሏታል፤ ደሊላ ትዋረዳለች

ኤልዛቤልን ውሾች በልተዋታል ወይስ ገና ይበሏታል? ገና ሊበሏት ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ መታረም አለበት። ደሊላስ? እሷም ገና ወደፊት የምትመጣ ናት ወይስ የሳምሶን ደሊላ? ደግሞስ በዚያ ታሪክ የተዋረደች ደሊላ ናት? ካልተዋረደችው ደሊላ ይልቅስ ያለቦታው ገብቶ የተዋረደው ሳምሶን ቢጠቀስ አይሻልም ኖሯል? ትምህርት የሚሆነን ይልቅስ እርሱ ነበር።

አንዳንድ ዘማሪዎች አዳዲስና እንግዳ ትምህርት ያስደምጡናል።

### ይህም አነሰብህ፥ አነሰ ምስጋና

አነሰ፥ ወዘተ፥ ማነስ የብዛትን ነገር በንጽጽር መናገር ነው። እግዚአብሔር ደግሞ የልብንና የጥራትን ነገር እንጂ የብዛትን ነገር አልፈለገም፤ ፈልጎም አያውቅ። ደግሞም አነሰብኝ አላለም፤ ብሎም አያውቅም። እኛ አነሰበት እያልን በሰዎች ውስጥ የበደለኝነትና የወንጀለኝነት ስሜት ማሳደርን ብንተውና ልብና ጥራት ላይ ብናተኩር ጥሩ ይሆን ነበር።

### ከቅባቱ የተነሣ ቀንበሬ ተሰባበረ

ይህ ብዙ ሰባኪዎችም ቅባቱ እያሉ ለአዲስ የቅባት ትምህርታቸው ማቆንጃ የሚጠቀሙበት ቃል ነው። ኢሳ. 10፥27 ላይ ያለ፥ "በዚያም ቀን ሸክሙ ከጫንቃህ ቀንበሩም ከአንገትህ ላይ ይወርዳል ቀንበሩም ከውፍረት የተነሣ ይሰበራል" የሚል ቃል ነው። ቃሉ ውፍረት ብሎ ስለውፍረት ሲናገር ሰባኪዎቹ ከሌላ ትርጉም ወስደው ቅባት ብለው ተርጉመው ስለ ቅባት የተዛባና በአዲስ ኪዳን ያልተደገፈ ትምህርት ያስተምራሉ። በዕብራይስጥ ቅባት፥ ስብ ወይም ስባት፥ ውፍረት ተለዋዋጭ ቃላት ናቸው። በዚህ ስፍራ ያለው ቃል ግን ከበሬው አንገት ውፍረት የተነሣ የቀንበሩ ቅትር እንደሚሰበር እስራኤልም ከመሰልሰልና ከጉስቁልና ባሻገር ተመችቶአቸውና ብርቱ ሆነው ሲስፋፉ መናገሩ እንጂ ቅባት አይልም። ቅባትን ካወሳን ሌላ አንድ እንይ፤

### የበቀል ቅባት በላዬ ፈሷል

ምንድርነው የበቀል ቅባት? አለ ለመሆኑ የበቀል ቅባት የሚባል ነገር? ቁጥሩ የበዛ የቅባት ዓይነት በዘመናችን ሰባኪዎችና ዘማሪዎች አንደበት እንጂ በቃሉ ውስጥ የለም። ይልቁንም የበቀል ቅባት የሚባል ነገር የለም። ምናልባት በኢሳ. 61 የተጻፈው አሳብ ተወስዶ የግል ተደርጎ ይሆን? ስለ በቀልና የአዲስ ኪዳን ትምህርት ባለፈው ስላተትሁ ብዙ አልልም። ግን በቀል የእግዚአብሔር መሆኑ የቀረበት ዘመን መጣ ይሆን? በሚጠሉን ላይ ሰይፍ መምዘዝ ጽድቅ ሆኖ ሊቆጠር ይሆን?

## መደምደሚያ ቃል

በመደምደሚያ ቃል ልል የምፈልገው መልእክት ይህ ነው። ይህ እና ያለፈውም ሒስ አትኩረት በዘማሪዎች አገልግሎት በተለይም በመዝሙሮቹ ቅርጽና ይዘት ላይ ነው። ትልቁና በምንም ነገር መለወጥ የሌለበት ነገር ከዘማሪዎቹ አንደበት የሚወጣው ቃል ንጽሕና ብቻ ሳይሆን የዘማሪዎቹ የራሳቸው አንደበትም ሆነ ራሳቸው በጌታ ውስጥ መሆናቸው ነው። በጌታ ውስጥ መሆን ማለት

በተግባራዊ ረገድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሆን ማለት ነው። ይህን ስል አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ማለቴ ነው።

አንዳንድ ዘማሪዎች በቤተ ክርስቲያን ወይም ራሳቸውም ሌላም ባዘጋጁአቸው ስብሰባዎች ላይ ስለተገኙና ስለዘመሩ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ይመስላቸዋል። ቤተ ክርስቲያን አካል ናት። እኛም እያንዳንዳችን ብልቶች ነን። ከመዝሙሮች ጋር የተያያዙ ጥቂት የጠቀስኳቸው ጥቂቶች እና ያልተጠቀሱም ሌሎች ችግሮች መመንጨትም መንጠባጠብም የሚጀምሩት ዘማሪዎቹ ከኃላፊነትም ከተጠያቂነትም መራቅ ሲጀምሩ ነው። እግዚአብሔር ጸጋን የሰጠው ለአካል ነው ወይም አካልን ለማነጽ ነው እንጂ ለገበያ አይደለም። አንድ ብልት አካልን የሚያንጸው በአካል ውስጥ ሲገኝ፤ ከአካልም ደግሞ በስፍራው፥ በመደቡ ሲገኝ ነው።

ዘማሪዎቹ በቤ/ክ የተተከሉ ናቸው ወይስ ዘዋሪ ዙረታም ናቸው? ስላልተተከሉና ቃሉን ስለማያጠኑ ነው በፍሬ ፈንታ ቅጠል የሚያበሉን ብዙዎቹ። ለሚያመልኩባት አጥቢያ ተጠያቂ ናቸው ወይስ ሚኒስትሪ ምናምን እያሉ ዝና የሚያካብቱና ገንዘብ የሚሰበስቡ ከበርቴዎች ናቸው? ከባለ ሚኒስትሪዎቹ አንዳንዶቹ ወይም ብዙዎቹ ከተጠያቂነት ነፃ ለመሆን ነው ይህን የሚያደርጉት።

ዶ/ር ደረጀ ከበደ በቅርብ [በ2000 መጨረሻ] በአንድ መጽሔት በተደረገለት ቃለ ምልልስ ዘማሪዎችንና ቤተ ክርስቲያንን ጎን ለጎን የሚሄዱ አቻ ድርጅት መሰል ነገሮች ለማድረግ ሞክሮአል። ዘማሪዎች ለቤተ ክርስቲያን ተጠያቂ መሆን የሌለባቸውና ዝማሬም ሙያ ብቻ እንደሆነ የሚያመለክት አቀራረብና ይዘት ያለው አስተያየት ሰጥቶ ነበር። ይህ ዘማሪ ለዘማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያንና ለመሪዎቿም አርዓያ መሆን የሚችልበትን የአስተያየት መድረክ ካለፈበት ምናልባት ጎርበጥባጣ መንገድና ከተሞክሮው የተነሣ ቤተ ክርስቲያንን የተደራጀ ሃይማኖት ብሎ በመዘንጠል ዘማሪዎችም ከቤተ ክርስቲያን ጠለላ እንዲርቁ የመከረና የሚመክር ይመስላል። የክርስቶስ አካል መሆኗ በግልጽ በተነገረላት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቤተ ክርስቲያንና በተደራጁ ሃይማኖቶች መካከል ልዩነት አለ። የዝማሬ አገልጋዮች የዚህች አካል ብልት መሆናቸውን ካልካዱ በቀር የእነርሱም ሆነ የአገልግሎታቸው ጎልውናና መገኛ ስፍራ ቤተ ክርስቲያን ናት። “እኔ ለኅብረት የሚሆን ተፈጥሮ የለኝም” የሚል አገልጋይ በአካል ውስጥ ብልት ሆኖ መኖር ይኮሰኩሰዋል። ዘማሪ ሁሉ እንደዚያ እንዲሆን አበረታች ምልክት መሆን ግን ተገቢ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን በተፈጥሮዋ ጉባኤ ወይም ማኅበርም ናት። ፍጹም ያልሆነች የቅዱሳን ኅብረት ናት። ዝማሬንና ዘማሪን በተመለከተ አገልግሎቱም አገልጋዩም ከዚህ ኅብረት ውጪ ስፍራ የላቸውም። እንደባለሙያ የራሳቸውን መደብ የሚፈጥሩ ከኖሩ ይህ የፈጠሩት ነገር መደብ እንጂ አካል አለመሆኑ መታወቅ አለበት። በተለይ የአገርን የዝማሬ አገልግሎት የፊት ቀስት አቅጣጫ የማስያዝ ችሎታ ያለው እንደ ዶ/ር ደረጀ የመሰለ ጉምቱ ዘማሪ በአተያዩ የዘማሪና የቤተ ክርስቲያን ግንኙነት ምሳሌ ሊሆን በቻለም ነበር። የዚህ ዘማሪ ጠቅላላ ትኩታው የዝማሬ ሙያነት ላይ ነውና ይህ ከሆነ ዘማሪዎቹም ሞያተኞች ብቻ ሊሆኑ ነው። ዝማሬ ግን በዐውዱ ሙያ ሳይሆን አገልግሎት ነው።

ኤፌ. 5፥19፤ ቆላ. 3፥16፤ 1ቆሮ. 14፥26 መንፈሳዊ ወይም ክርስቲያናዊ መዝሙር እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመን ሁሉ በአዲስ ኪዳንም እግዚአብሔርን በማምለክና ቅዱሳንን በማነጽ የጎላ ስፍራ እንዳለው ያሳያሉ። ከግልና ከእልፍኝ እስከ ጉባኤና አደባባይ ድረስ ጌታ ይመለከበታል፤ ክርስቲያኖች ይታነጹበታል። ይህ እውነት ነው። የዚያኑ ያህል ደግሞ ከሁለቱም አቅጣጫ፥ ከአገልጋዩም ከተገልጋዩም ኃላፊነት አለበት። ምክንያቱም መዝሙር አገልግሎት ነው። መዝሙር ችሎታና ዝንባሌ ብቻ አይደለም። መዝሙር ስጦታ ነው። ከጸጋ ስጦታዎች ጋር ባይዘረዘርና የተፈጥሮ ዝንባሌና ተሰጥዖም ሊሆን ቢችልም በ1ቆሮ.14 ከአምልኮ ጋር ተጠቅሶአልና ከክርስቲያናዊ ይዘቱ አንጻር ስጦታና የእግዚአብሔር ሀብት ወይም ጸጋ ነው። ይህ አጠቃቀስ ለማነጽ የተሰጠ ጸጋ መሆኑን ያሳያል። ስጦታው ለዘማሪዎቹ የተሰጠ ነው። ዘማሪዎቹ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ስጦታዎች፥ ሽልማቶች፥ ጌጦች ናቸው። ቤተ ክርስቲያንም የክርስቶስ አካል ናት። በምድር አካልነቷ ደግሞ ከሥልጣን ጋር ነው። የክርስቶስ ወኪሉ ናት። ቤተ ክርስቲያንን እያንኳሰሱ ክርስቶስን ማወደስ እውነት አይደለም።

ስጦታ ግብና ዓላማ አለው። ግቡ የቤተ ክርስቲያን መታነጽ ነው። ዓላማው የእግዚአብሔር ክብር ነው። መንፈስ ቅዱስ ስጦታን ያለቦታው አይሰጥም። የትኛውም ስጦታ የሚያገለግለውን ያህል ያለአግባብ  በመስከ ላይ ሊውልም ይችላል። ያለአግባብ የሚውለው ከስሕተቶች የተነሣ ነው። ከስሕተቶቹ ጀርባ ሆነው ለስሕተቶቹ መኖርና መቀጠል ሚና የሚጫወቱ ሦስት ዋና ዋና ነገሮች ቀደም ሲል ተጠቅሰዋል። ከነዚህ ጋር አብሮ መወሳት ያለበት ይህ የባለቤትነት ጉዳይ ነው። የዚህች ወይም የዚያች ቤተ ክርስቲያን ዘማሪ ካልን [አሁን አሁን አንዳንዶቹ ታዋቂዎች ስለሆኑ ይህን መታወቂያ ቀርፈው እየጣሉት ነው] ያቺ ቤተ ክርስቲያን በዘማሪው ሕይወትና አገልግሎት እንዲሁም በአገልግሎቱ ጥራትና ልቀት ላይ ካነሰ የምታሳድረው ተጋቦት አላት፤ ከዚህ ካለፈም ኃላፊነት ይኖራታል።

በዚህ ረገድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ኃላፊነት አለባቸው። ቤ/ክንን ወይም የቤተ ክርስቲያንን ሥልጣን የማያከብሩ ሰዎችን እየጋበዙ እያሞጋገሱ አሜሪካ አውሮጳ ይዘው እየዞሩ፥ እየኳሉ እየዳሩ፥ ከአሜሪካ ኢትዮጵያ እየጋበዙ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የት ቦታ መሆናቸውን ሳያውቁ፥ አንዳንዶቹንም ጭራሽ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖራቸውንም እንኳ ሳያውቁና ሳያረጋግጡ መድረክ ላይ ጉብ ያደርጓቸዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉቱም ከቤ/ክ ጠፍተው ኖረው ሊያሳትሙ ሲሉ ቤ/ክ ብቅ ይሉና አንድ እሁድ አስዘምረው፥ አስመልክተው "ጳጉሌኝ ደብዳቤ ለማስታወቂያ ሚኒስቴር" ይላሉ። አንዳንድ መሪዎች ይጽፋሉ። ለመሆኑ መዝሙሮቻቸውን መርምረው ነው የሚጽፉት? ወይስ የገንዘቡ ፍርፋሪ ስለሚደርሳቸው? ይህ ሁሉንም መሪዎች የሚመለከት እንዳልሆነም መታወቅ አለበት። ግን ከዚህ ዳፋ እጃቸውን መታጠብ የማይችሉ መሪዎችም እንዳሉ ሳይጠቀስ መታለፍ የለበትም።

ይህ ሲባል የሳንቲሙ ሁለተኛ ገጽታ ደግሞ ከቶም መረሳት የለበትም፤ ያም ቤተ ክርስቲያን ዘማሪዎችዋን በአግባቡ ትይዛለች? ትንከባከባለች? የሚለው ነው። ስጦታውና ጸጋው እንዳላቸው እርግጠኛ የሆነችባቸውን ዘማሪዎችዋን ሌላ የተሰማሩበትና መኖሪያ ብለው የያዙት

ነገር ከሌላቸውና በቤተ ክርስቲያን ድጋፍ ማገልገል እንዳለባቸው ካመነች ማስማራት ኃላፊነቷ ነው። በዘማሪዎቿ ላይ ምንም መዋዕል የማታፈስ ቤተ ክርስቲያን፥ በኑሮአቸውና በክርስትና ሕይወታቸው፥ በትምህርታቸውና በአገልግሎታቸው፥ ምንም ሚና ሳይኖራት እመር ብለው ሲወጡና ሲደምቁ የይገባኛል ጦር ማስፈር አያስከብራትም። ዘማሪ ሁሉ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ አይሆንም። ቢሆኑና ከሌላ ጸጋቸው ጋር ቢሰማሩ ግን ይበልጥ ፍሬያማ አገልጋዮች የሚወጣቸው እንዳሉ መረሳት የለበትም።

ለመደምደም ቀደም ሲል በጠቀስኩት ባለፈው ዎርክሾፕ ላይ 'ታዲያ ምን ይደረግ?' ለሚለው የመደምደሚያ ጥያቄ በበኩሌ የጠቀስኳቸውን ሦስት ነጥቦች በመዘርዘር እጨርሳለሁ።

1. ዘማሪዎች ጠንቃቃ ይሁኑ። በሕይወትና አመላለስ ጠንቃቃ ይሁኑ፤ የመድረክና የአደባባይ አገልጋዮች ናቸው። በጥቂት ወይም በብዙ የቤተ ክርስቲያንና የጌታም ተጠሪዎችና ወኪሎች ናቸው። ሲደርሱ፥ ሲያርሙ፥ ሲያገለግሉና ሲያሳትሙም ጠንቃቃ ይሁኑ፤ የጥበብ ሰዎችና ባለሙያዎችም ናቸው። እነዚህን ጥንቃቄዎች በተመለከተ ዘማሪዎቹ ሌሎችንም ጠያቂና ፈታሽ በማድረግ ማሳተፍ አለባቸው፤ እነዚህ ሌሎችም ተሳታፊ በመሆን መትጋት አለባቸው።
2. የሕያሴ መዝሙራት ባህል መዳበር አለበት። ሒስ ወይም ገንቢ ትችት መፈራት የለበትም፤ ከፊቱም መሸሽ የለብንም። ይልቁንም የኪነጥበብ ሰዎች ሆን ብለው ሒስን መፈለግ አለባቸው። በተለይም መንፈሳዊ ሕይወትን የሚገነባ ወይም የስሕተት አስተምህሮ ሊተላለፍበት የሚችል ይህ የመዝሙር አገልግሎት ለመፈተሽ መውደድ አለበት። በየተወሰነ ጊዜ የሚደረጉ ዐውደ ጥናቶችና የውይይትና የትምህርት መድረኮችም መበረታታት አለባቸው።
3. ቢቻል ደረጃ አስጠባቂ አካል ቢኖር መልካም ነው። ይህ በሙያና በትምህርትም፥ በጸጋና በአገልግሎትም የበሰሉ ሰዎች ያሉበት በፈቃደኝነት የተመሠረተ ማኅበር ወይም በአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ውስጥ የሚገኝ የቢሮ ቅርንጫፍ ሊሆን ይችላል።

ይህ CD የሚሸጥ ሳይሆን በነጻ የሚታደል ነው። ማንም ሰው ባለቤትነቱን ሳይወስድ ሊያባዛና ሊያድል ይችላል። ጽሑፉንም ማባዛትም ማደልም የተፈቀደ ነው። ጽሑፉን ወይም በድምጽ የተቀረጸውን በኢሜይል ማግኘት የምትፈልጉ በCDው ወይም በመጣትፉ ላይ ባለው አድራሻ (ezralit@gmail.com) ብትጠይቁ በሚነበብ ወይም በሚታተም ሰነድ ወይም ወደ ኮምፒዩተር በሚጫን ኦዲዮ መልኩ ልልክላችሁ እችላለሁ። እግዚአብሔር ከአርያም ይባርካችሁ።

© ዕዝራ የስነ ጽሑፍ አገልግሎት /